# ትግላችን ዜና

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

P.O. Box 3198 STOCKHOLM SCHWEDEN ልዩ እትም ቁጥር1

- የአ.ኢ.ተ.ማ. አቋም መግለጫ
- ከአ.ኢ.ተ.ማ. መጽሔት ቦርድ
  ለ፪ኛው የአ.አ.ኢ.ተ.ፌ. ጉባኤ የተሰጠ መግለጫ
- እኛ እንዳየነው (ስለ አ.አ.ኢ.ተ.ፌ. ጉባኤ)

ጥቅምት 1967, October, 1974

## መግቢያ

ውድ አንባቢያች:

በዚህ ልዩ እትም የምናቀርብላችሁ በመስከረም ቴምበር 1 እስከ 7 በተደረገው የፌዴሬሽኑ ሁለተኛ ጉባዔ ላይ የቀረቡ ናቸው:: እነሱም:—

1ኛ:— ጉባዔው እንደተከፈተ በአውሮፓ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የተነበበ የአቋም መግለጫ

2ኛ:— በዚሁ ጉባዔ ላይ ያውሮፓ መልዕክተኞች አበል በሆነው የመስሴት ቦርድ የተዘጋጀ ግን በባለጉባዔያቸ እንዳይነበብ የተከለከለ የአቋም መግለጫ

3ኛ:— ከአውሮፓው ዴሌጌሽን በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው በኩል የቀረበ የመደምደሚያ መግለጫ

4ኛ:— 'እኛ እንዳየነው ስለፌዴሬሽኑ ጉባዔ አንዳንድ አስተያየት' /በአንድ ጓድ ለሥ.አ.ኮ የተዘጋጀ ጽሁፍ::ጽሁፎቹ በፖለቲካ ጥያቄያችና የኢት.ተማ.ማህበራትን የትግል አንድነት በሚመለከተው በኩል ማህበራችን ያለውን አቋም በሚገባ ይገልጻሉ::

አንባቢ ከጽሑፎቹ ሊረዳ እንደሚችለው ፣ በዚህ 2ኛ የፌዴሬሽኑ ስብሰባ ላይ የተገኘነው ከብዙ ጊዜ ጀምረን እንደታገልንለት ሁሉ፣ የኢትዮጵያን ተማሪዎች አንድነት በዲስ መንፈስና በከፍተኛ ደረጃ ለመመስረት ካለን ጽኑ ፍላጐት የተነሳ ነበር::ነገር ግን ስስት ሰዎች ከባቨች እነዚሁ ስስት ሰዎች ፈሬቨች የነበሩበት ይህ የፌዴሬሽኑ 'ታሪካዊ' ስብሰባ ያንድነት መመስረቻ ሳይሆን የአውሮፓ ማህበር ማውገዣ ሆኖ አልፏል:: በዚህም መሰረት ማህበራችን በስድስቱ ቀን ስብሰባ ከስድስት ጊዜ በላይ ተወግዟል::

በጉባዔው መጨረሻ ላይ ያቀረብናቸው የመተባበሪያ ድርድሮች በነሱ በኩል ተቀባይነት አላገኙም:: እነሱም :—

1—በሁዳን አንድ ስም ያላቸው አብዛኛውን እንወክላለን የሚሉ ሁለት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ስለሚገኙ በመጀመሪያ አንድ የሚሆኑበት መንገድ እንዲፈለግ ይህ ካልተሳካ ተጠንቶ አብዛኛውን የሚወክለው ወገን እንዲታወቅ

2—እንደዚሁም በመካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አፍሪካ በተፈጠሩት ሁለት የአካባቢ ማህበራትም ላይ ተመሳሳይ አቋም እንዲኖረን

3—ዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ቢሮች የጥናት ክበብ ሁለት አባሎች —የሰሜን አሜሪካውና የአውሮፓው— በፌዴሬሽን አባልነት ላይ ያልተስማሙ ስለሆነ ለችግሩ ዲሞክራሲያዊ መፍትሄ ማግኘት የሚገባቸው እራሳቸው መሆን ስላለባቸው በውስጥ ጉዳያቸው ማንም ጣልቃ እንዳይገባ

ፌዴሬሽኑ ከላይ ያሰብነውን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን ከነዚህ ከተበነጣጠሉ ድርጅቶች አየመረጠ አንደኛውን ወገን አባሌ ነው ማለትንመርጧል::ለምሳሌ ያህል "አብዛኛውን በሁዳን ያሉትን ተማሪዎች እወክላለሁ የፌዴሬሽን አባል ነኝ ባዩ የስድስት ሰዎች ወኪል ነው"በማለት ለማህበራችን የ31 ኢትዮጵያውያን የእጅ ፊርማ የሰጠውንና"ያገር ቤቱን ማህበር በመወከል ተገኝተው የነበሩት ጓዶች ሁዳን አገሩ መንግዳቸውን ደርሰው ሁለቱም ወገኖች ስብሰባ ጠርተው የትኛው ወገን አብዛኛውን እንደሚወክል ያረጋግጡ"ያለው ጓድ የመናገር መብት ተነፍጉት ይህ ስድስት ሰው ይወክላል የተባለው ከጉባዔው ውሳኔ ሰጪ ስስት ሰዎች አንደኛው ነበር::



ወጣም ወረደ ስሬው የአውሮፓ ማህበር የታገሉለትን ዲሞክራቲክ ሕገ ማህበር በመጨረሻ እንዲቀበሉ ስለተገደዱና በዚህም ሕገ ማህበር ላይ ከሞላ ጎደል ስምምነት ስለተገኘ ማህበራችን ከነገዲህ ከነዚህ ሰዎች ጋር ድርጅት—ነክ ንትርክ ውስጥ ሊገባ አይፈልግም::

ከላይ በደረደርናቸው ነጥቦች ላይ ስምምነት ባለመደረሱ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው እነዚህ ማህበራት የሚስማሙበትን መንገድ ከመፈለግ አይቆጠብም:: ይህ ካልተሳካ የምናገኘውን ማስረጃ ሁሉ ለ15ኛው ጉባዔያችን በማቅረብ በዲሞክራሲያዊ መንገድ አቋም እንዲወሰድበት እናደርጋለን::

የሊባኖስን ማህበር ሊቀ መንበር ተስፋዬ ታደሰን በሚመለከተው በኩል እኛም ሆነን አብዛኞቹ የማህበራችን አባላት ፌዴሬሽን ከሚባል ድርጅት ቡለቲን ከሚባል ጋዜጣ እውነትን ስምተውና አንብበው ስለማያውቁ ይህ ሰው ሰላይ ነው በማለት በፌዴሬሽኑ በኩል የተሰረጠውን ክስ ባለመቀበል በ14ኛው ጉባዔያችን ላይ ውሳኔ አሳልፈዋል:: በፌዴሬሽኑ ጉባዔ ላይ የሀገር ቤቱን ማህበር በመወከል የተገኙት ሁለት ጓዶች "ተስፋዬ ታደሰ ሰላይ መሆኑንና ይህንን እንድናብራራ የተለየ ማንዴት ተሰጥቶናል:: በገር ቤት ነቅናቂ ስም እንፋረደዋለን ሰቡ ሰላይነት ማስረጃ የምንጠየቅ ስላልመሰለን ይዘን አልመጣንም ነገር ግን ይህ ከሰፈለገ አገር ከተመለስን በኋላ ሰብስበን ለመላክ ዝግጁ ነን" ባሉት መሰረት ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው እነሱና ከሌላም ቦታ የሚያገኛቸውን መረጃዎች በመሰብሰብ ማህበራችን ተገቢውን አቋም እንዲወስድበት ለ15ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል::

በመጨረሻም ፣ በድርጅት ጥያቄ ላይ ከነዚህ ሰዎች ጋር ከነገዲህ ምንም ዓይነት ውዝግብ ውስጥ ባንገባም በርዕዮተ ዓለምና በፖለቲካ ልዩነቶቻችን ላይ የምናደርገውን ትግል ከመቸውም በበለጠ እንቀጥላለን:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ የትግል ደረጃ ላይ ደርሶ የሕዝቡን ትግል ወደፊት ለማራመድ ትልቅ ሃላፊነት እያሰብን ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ የራሱን ትግል ትቶ ለስልጣን የጓጓውን መለዮ- የለሽ ንዑስ ከበርቴ ከስልጣን ለማድረስ እንዲታገል የሚጠሩትን እነዚህን ሰዎች ከመቸውም ይበልጥ ለረጅም የነጻነት ትግል ለታጠቁትና ለሰፊው የተማሪ ማህበራት አባላት እንዲሁም በሰፊው ሕዝብ ሸማጋለጥ በንቅናቄው ውስጥ ሊያስፋፉ የሚፈልጉትን የተሳሳተ የጆለ_ተካ መስመርና የርዕዮተ ዓለም ወቸንበር መታገል ከጊዜያዊ ተግባሮቻችን አንዱ ነው::

## በ2ኛው ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ስብሰባ ላይ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የቀረበ ያቋም መግለጫ መልእክት

ውድ ጓደኞች:

ዛሬ ይህ ጉባኤያችሁ በሚደረግበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አዳዲስና አኩሪ የታሪክ ገጾች በመጻፍ ላይ ይገኛል::ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ ቁጣ የገነፈለበት ትግሉ ገዢዎችን ያርበደበደበትና አንዲያሸገሽጉ ያስገደደበት ታሪካዊ ወቅት ነው:: በዚህም በዘመናት መስዋእትነትና ቆራጥ ትግል በደረሰበት አጅግ ከፍተኛ የሆነ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደነጻነት በሚያደርገው ረዥም ጉዞ አዲስና አኩሪ ምእራፍ ከፍቷል::በኢትዮጵያ ሕዝብ መጠቆን ስንገበገብና ፋሽስታዊውን አገዛዝ ስንቋቋም የኖርን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ያለን እምነት ከመቼውም ይበልጥ ዳብሮ እናየዋለን::በዚህም አኳያ ተጋዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈተው አዲስ የትግል ምእራፍ ለኛ ለተራማጆች ከመቸውም የከበደ ሃላፊነት በትከሻችን ላይ ጥሎብናል::ከነገዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዢም ጊዜ መራራ ትግሉ የከፈታቸው አዲስ የታሪክ ገጾች ድልን በተጎናፀፉ ቀለማት የሚጻፉት፣የሕዝቡ የተበታተነ ትግል መልክ ይዞና ተደራጅቶ ወደፊት ሲገፋ ብቻ ነው::

ይህ አኩሪ የታሪክ ምእራፍ፣ ይህ የአዲስ ትግልና የአዲስ አደራ ዘመን አንዲከፈት በተደረገው ተጋድሎ ትሙራዳችን በብዙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ንፁህ ደም፣የስደት መከራ፣የእስራትና የግርፋት ስቃይ የከፈለው ታላቅና አኩሪ አስተዋጽኦ አለው:: ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰልፎ የሚንቀሳቀስባቸው ሬቮሉሽናዊ ዓላማዎች በሃገራችን ተዘርተውና ስር ሰደው የማይበገሩ የለውጥ ኃይሎች እስኪሆኑ ድረስ በለጋ ትከሻው ተሸክሞ እዚህ ያደረሰው ወጣቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ነው::ባለፉት አስር ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቼውም ይበልጥ የተደፈረው ብሔራዊና ሰብዐዊ መብቱ ወርሶ አንዳይደመሰስ በነገበር ቀደምትነትና በአስደናቂ ጀግንነት ሲከላከል የኖረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ነቅናቄ ነው::ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም የተጫነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ጠርሶ አንዳይታፈን ያልተሰጣቸውን ነጻነት በፋሺስቱ አገዛዝ በመቀማት የሕዝቡን ድምጽ ሲያስተጋቡ የኖሩት 'ታገል'፣'ስትራገል'፣ 'ትገላችን'፣'ታጠቅ'ና'ቻሌንጅ'ናቸው::መጪው ትውልድ ይህን የትግል ዘመን በጠቃላይ አየመረመረ በሚተነትንበት ጊዜ ይህ የኢትዮጵያ ወጣቶች በመራራ ትግላቸው የጻፉት ገጽ በኢትዮጵያ ሕዝብ የረዢም የትግል ታሪክ ውስጥ አሸብርቀው ከሚታዩት አንዱ አንደሚሆን አንጠራጠርም::

ጓደኞች:— ዛሬ በዚህች ታሪካዊ ወቅት ይህንን ሁሉ ስናስታውስ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ነቅናቄ ተገቢ ኩራት ይሰማናል::በዚህም ትግል ለጋ ሕይወታቸውን ሳይሰሱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳልፈው የሰጡትን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በሙሉ እናስታውሳቸዋለን::በነዚህ ወገኖቻችን ንፁህ ደም የሚያስተጋባውን የትግል ጥሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰምቶ እነሱ ለወደቁለት የነጻነት ትግል ተነስቷልና 'በገፍ ተጠፈጠፉችሁ አንጂ በከንቱ አልሞታችሁም'እንላቸዋለን:: እኛ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ከቆራጥነታቸው አርአያነት ወስደናልና ከትግላቸው



ትምህርት ቀስመናልና የነጻነቱ ትግል ይቀጥላል::

ይህ ጉባኤ ካለንበት ታሪካዊ ወቅት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን የሚችለው ጊዜው የጣለብንን አደራ ተገንዝበን ተግባራችንን በተጣራ ሁኔታ ስንቀይስና ይህንንም ከስራ ላይ አውለን የነጻነት ትግላችንን ወደፊት በማራመድ አንድነታችንን አጠንክረን የወጣን አንደሆነ ብቻ ነው::

በአውሮፓ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ታሪክ ከሚጥልብን አደራና በየጊዜው ከሚወድቅብን ከባድ ኃላፊነት ወደኋላ ያልነበት ጊዜ የለም:: ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንዲህ ከፍ ያለ ደረጃ ደርሶ አዲስ የትግል ጥሪዎች በሚያስተጋቡበት ታሪካዊ ወቅት በአውሮፓ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለነጻነቱ ትግል የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ከማድረግ ፈጽሞ አይቆጠቡም::ለዚህም ማህበራችን በንቅናቄያችን ውስጥ የሚያንዣብበው ውዥንብር ጠፍቶ የተጣራ የፖለቲካ መስመር አንዲያዝ፣ መከፋፈልና መዳከም ቀርቶ በዴሞክራሲ ላይ የተገነባ የጠነከረ አንድነት አንዲሰፍን የቆየ ትግሉን በአዲስ መንፈስ ይቀጥላል::

ጓደኞች : ዛሬ በዚህ ጉባኤ ልዩነቶቻችንን ሁሉ ከመቅጽበት አፍታን አንድነት ለመመስረት አልመጣንም::ወይም ደግሞ ማጥፋት ያልቻልናቸውን ልዩነቶች ሸፋፍነን በተዳበሰበሰ መሠረት ላይ አንድነት ለመገንባት አልመጣንም::በኢትዮጵያ ተማሪዎች ነቅናቄ ውስጥ ሥር አየሰደዱ የሄዱ የፖለቲካ ልዩነቶች ከተፈጠሩ ቆይተዋል:: በአጠቃላይ 'ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል'ከምንልበት ዝቅተኛ የትግል ደረጃ አልፈን የነጻነቱ ትግል አንዴት ይመራ?ዛሬ ምን አንስራ? የሚቀጥለውስ ተግባራችን ምንድን ነው? እያልን በየጊዜው ለሚፈልቁት አጣዳፊ ጉዳዮች መልስ አየሰጠን ወደፊት ለመራመድ ስንፈልግ የአስተሳሰብ ልዩነቶች መፍለቃቸው ፈጽሞ እንግዳ ነገር ሊሆንብን አይገባም::በኛ ግምት እንዲያውም ይህ የእድገታችን ምልክት ነው::እንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ መስመር ልዩነቶች አሁንም አሉ ወደፊትም ይኖራሉ:: ነገር ግን በምንም ዓይነት በፀረ— ፊውዳልና ፀረ— ኢምፔሪያሊስት የጋራ ፕላትፎርም ላይ የተገነባውን ድርጅታዊ አንድነት ሊያናጉት አይገባም::

ዛሬ በንቅናቄያችን ውስጥ በተለይ በኢሱናና በኛ ማህበር መሃል ስር ሰዶ የሚገኘው የፖለቲካ መስመር ልዩነት በመጽሔቶቻችን ብቅ ማለትና መልክ መያዝ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት ሆኖታል::

የማህበራችን መሠረታዊ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ ደህንነቱን የሚያረጋግጠው፣ዘላቂ ሰላም ነጻነትና ብልጽግናን የሚጎናፀፈው፣ በረዢም ጊዜ የፖለቲካ ቅስቀሳ ነቅቶና ተደራጅቶ በሕዝባዊ አመጽ አድሃሪዎችን ሲደመስስ ብቻ ነው::ይህን ሬቮሉሽናዊ አቋም የሚቃወመው ወገን በየጊዜው የተሰበጣጠሩ መስመሮች ቢከተልም፣አንዳንዴ እንዲያውም የሚያቀርባቸው መስመሮች እርስበርስ የሚቃረኑ ቢሆኑም፣ በመሠረቱ የሚያያይዛቸው አንድ ነገር አለ::ይኸውም አስፈላጊ የሆነውን የፕሮፓጋንዳ የአጂቴሽንና የማደራጀትን ተግባር ችላ በማለት ሬቮሉሽኑን በቋራጭ ለመስራት በየጊዜው ከሰፊው ሕዝብ ተነጥሎ አቋራጭ የሚፈልግ አቋም መሆኑ ነው::ስለዚህም ከመጀመሪያውም ጀምሮ አስከ ዛሬ ድረስ በንቅናቄያችን ውስጥ ያለው ልዩነት የሚፈልቀው፣ በአንድ በኩል ለረዢም ጉዞ ታቅቀው በየእለቱ ጊዜያዊ ተግባርን እየተየሱ ከሕዝቡ ጋር ለመራመድ በሚታገሉ

የረጥ ሪቮሉሽናዊያንና በሌላ በኩል ደግሞ አድኃሚውንና ትዕግስት የሚጠይቁትን፣ አለሁ አለሁ የማያበዛውን የመቀስቀስና የማደራጀት ተግባር በየምክንያቱ ችላ አያሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፈንታ እኛው ሪቮሉሽኑን እናደርገዋለን ብለው ውር ውር በሚሉ ንዑስ ከበርቴ ደንፊዎች መሀከል ነው::

ይህ ሪቮሉሽኑን በቋራጭ የሚፈልገ አቋም መጀመሪያ በኢዙና መጽሔቶች የታየበት በስቸኳይ የጦር ትግል እንጀምር በሚል መልኩ እንደሆነ ዛሬ ሁሉም የሚያውቀው ነው::በዚህ መልክ የኢዙና መጽሔቶች በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ተስፋ ቆርጠው በስቸኳይ የጦር ትግል እንድንጀምር ሲወተውቱ ማህበራችን አጥብቆ ተቃወመ::በሁኑ ጊዜ ዋና ተግባራችን ሰፊ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አጊቴሽንና ፕሮፓጋንዳ እያደረገ የሕዝቡን የፖለቲካ ህሊና ከፍ ማድረግና ማደራጀት ነው በሚል እምነት ይህን ተግባር እንድንይዝ አስገነዘበ::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተማሪው ንቅናቄ ተግባርና ሚና የተከተሉት ልዩነቶች ከዚህ መሠረታዊ ልዩነት የፈለቁ መሆናቸው ገልጽ ነው::ችኩሉ ወገን የተማሪውን ንቅናቄ በስቸኳይ ለሚጀመረው 'ሕዝባዊ ጦር' መመልመያ ሊያደርገውና ሊያጠበው ሞከረ::በሌላ በኩል ደግሞ ለረዥም ጊዜ ትግል የታጠቀው ወገን እርገጥ የተማሪው ንቅናቄ ለመጭው ትግል 'ካድሬዎች' ማበርከት ታሪክ የጣለበት አደራ መሆኑን በይስቶውም፣ ሰፊውን ተማሪ በዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች እየንቀሳቀሱ ሥርዐቱን ዛሬ ወጥሮ መያዙም ዛሬ አስፈላጊ መሆኑንና እንዲያውም በወጉ ለነገው ትግል ካድሬዎች ማፍራት የሚቻለው ይህ ሰፊ ትግል የተማሪውን የፖለቲካ ህሊና ሲያዳብረው ነው ብሎ ተከራከረ::የነዚህ የተለያዩ መስመሮች ነጸብራቅ በሌሎች ልዩ ልዩ ተግባሮቻችን ላይ እንደታዩት ሁሉ ቅልጭ ባለ መልካቸው በመጽሔቶቻችንም ይዘት ይታዩ ጀመር::

ጥቂቶችን በቲዎሪ ለማነጽና ለጠና ትግል ለመመልመል ቅድሚያ የሚሰጠው አቋም አልፎ አልፎ የሚያወጣቸው መጽሔቶችን ለተራቀቀ የቲዎሪ ጥናቶችና በተራማጆች መሃከል ላሉት ልዩነቶች መከራከሪያ ከፈታቸው እንጂ በነሱ አማካይነት ሰፊውን ሕዝብ መቀስቀሱንና ማደራጀቱን ከመጤፍም አልቆጠረውም:: እንዲያውም 'ትግላችን' ለዚህ ተመድቦ ጥቃቅን የሕዝብ ትግል ሁሉ እያስተጋባ ትምህርት የሚሰጥ አጊቴሽን ማድረግ በሞከር 'የመንደር ወሬ አበዛ' በማለት በቃል የሚጠና 'ሃንድ ቡክ ኦን ሪቮሉሽን ኤንድ ኦርጋናይዜሽን' እያወጣ ለተማሪው ያድል ጀመረ::ይህ ሁሉ ቢሆን እነዚህ መሰረታዊ ልዩነቶች ከመጀመሪያው ገልጥልጥ ብለው ለአብዛኛው ተማሪ ባለመታየታቸው በጥቂቶች መሃከል የሚደረጉ 'ንትርክ' መስሉ የፖለቲካ ይዘቱ ተድበስብሶ ቆይቶ ነበር::ይህም ብዙዎችን ተስፋ እያስቆረጣቸው ከትግሉ ገለል ስላደረጋቸው ንቅናቄያችን ወደመድከም ደርሶ ነበር::በተለይ የማህበራችንን ሪቮሉሽናዊ አቋም በስመ ሪቮሉሽን እየተቃወመ ሲያወናብድ የነበረው ወገን በየጊዜው አቋሙን እየለዋወጠና እየወላወለ ፈጽሞ አልጠበጥ በማለቱ፣ ብዙውን ጊዜ ደግሞ በጽሑፍ ያሰፈራቸውን አቋሞች እንኳ እየካደ ግራና ቀኝ ሲወረጭ ንቅናቄያችንን ማወናበድ ችሎ ነበር::ቢሆንም ማህበራችን የዚህን ወላዋይ አቋም ፋርጀንነት ከመጠቆምና አደገኛነቱን ከማስገንዘብ የተቆጠበበት ጊዜ የለም::

በ1973 ዓ:ም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄ በተሻለ ለማቀነባበር ማህበራችን በበርሊን የተደረገውን ጉባዔ ባዘጋጀ ጊዜ ይህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ወላዋይ ከንፍ በርገጠኛ መልኩ መጋለጥ ጀመረ::በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በመጠ



ቀም ከሰፊው ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር ምንም ዓይነት ሊጣጣም የማይችል ፀረ-ዲሞክራቲክና እንደአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ማዕከላዊነት ያለው ሕገማህበር አጽድቆ 'ዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን' የሚል መሠረተ::በዚህም ድርጊቱ በተጨባጭ ሁኔታ ፀረ-ዲሞክራቲክ መልኩን በሰፊው ተማሪ ፊት ማጋለጥ ጀመረ::እንዲያውም ራሱ አጽድቆ ከሥራ ላይ ማዋል የጀመረውን ሕገ ማህበር ፀረ-ዲሞክራቲክ ይዘት ሰፊው ተማሪ ቢነቃበት እንደገና ይበስ ብሶ ፀረ-ዲሞክራቲክ በሆነ ፈላጭ ቆራጭ ዘይቤ ምንም ጉባዔ ሳይጠራ የህገማህበሩን አንቀጾች በመሪዎቹ መልካም ፈቃድ መሰረዝ፣ መደለዝ፣ መለዋወጥና ማሻሻል ሁሉ ተደረገ::ይህም ፀረ-ዲሞክራቲክ የሆነውን ሕገ ማህበር ፀረ-ዲሞክራቲክ በሆነ ዘዴ ለማሻሻል መሞከሩ ፌዴሬሽኑ የባሰ ተጋለጠት እንጂ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን አልጨመረለትም::ስለዚህም በ13ኛው ጉባዔያችን ማህበራችን ፌዴሬሽኑን እንደማይቀበለው አስታወቀ::

ከዚህ በኋላ ፌዴሬሽኑ የራሱ የሆነ 'ቡለቲን' ስላወጣ እጅግ ወላዋይና ተለዋዋጭ የሆነ የፖለቲካ መስመሩን በሰፊው ተማሪ ፊት እየዘረጋ በየዕለቱ ይበልጥ እየተጋለጠ ሄደ በተለይ ከየካቲቱ እንቅስቃሴ ጀምሮ ፌዴሬሽኑ አከታትሎ በሚያወጣቸው ቡለቲኖች አቋሙ እያከታተለ ቢለዋወጥም፣ አንድ ጊዜም ቢሆን የጊዜውን ዋና ተግባር አጥብቆ ባለማመልከቱ የሚከተለው ፖለቲካ በንዑስ ከበርቴ ችኩልነት ብቻ የሚገፋፋ ለረዥሙ የነጻነት ትግል አዋኪ አቋም መሆኑ በይፋ እየታወቀ ሄደ::

ይህ ፌዴሬሽኑና ኢዙና የሚከተሉት በንዑስ ከበርቴ ወላዋይነትና ችኩልነት የተበከለ አቋም የጊዜዉን አቋም በመብት በንቅናቄያችን ውስጥ ውዝንብር የሚነዛ መሆኑ በያዝነው ወር በተደረገው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 14ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በሚገባ ተጋልጦአል::የተነሱት ልዩነቶች የተሰበጣጠሩ ቢሆኑም በተለይ የየካቲቱን ሕዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በሚመለከተው በኩል የማህበራችንን መስመር የሚመለከቱ ሁለት ቲሲሶች በጉባዔው ላይ ቀርበው በትግሉ አመራር፣ በሕዝባዊ መንግስት ጉዳይ፣ በድርጅት ጥያቄና በሪፎርም ወይም ጥገና የተለያዩ መስመሮች ቀርበው ነበር::

የእነዚህ ጓዶች መሰረታዊ ስህተትና የወላዋይ አቋማቸው ምንጭ የሆነው ይኸው ስለየካቲት ትግል አመራርና የመደቦች አሰላለፍ ያላቸው 'የመጽሐፍ ገልበጣ' ችሎታ ነው::መጪው የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን በሃገሪቱ የሚገኙ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በሙሉ በሠራተኛው ፓርቲ በሚመራ ሕዝባዊ ግንባር ሥር ተደራጅተው የሚታገሉለት አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ነው::ትግሉ ከግቡ እንዲደርስ አመራሩን የሠራተኛው ፓርቲ እንዲይዘው ያስፈልጋል::ይህ ተራማጆች ሁሉ የምንቀበለው ትክክለኛ አቋም ነው::እንግዲህ ሁኔታውን በግልጽ ለማወቅና ጊዜያዊ ተግባርን በተጨባጭ ሁኔታ ለመቀየስ ዛሬ በዚሁ ሪቮሉሽናዊ ጎዳና ላይ የት እንዳለን አጣርተን ማወቅ ይገባናል::ጓዶች ግን የት እንዳለን አልገባቸውም::ዛሬ እነዚህ ጓዶች ይህ የየካቲት እንቅስቃሴ የተመራው በሠራተኛው መደብ እንጂ በንዑስ ከበርቴው አይደለም ይላሉ::ይህንን በሬ ወለደ እውነት ብለን ብንቀበል ኖሮ መጭው መንግሥት በሰራተኛው የሚመራ በመሆኑ ያሳንዓች ማወሳወል የማንቀበልበት ምክንያት አልነበረም::ነገ ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ ልብ ብሎ የሚመለከት ሁሉ እንደሚረዳው የየካቲቱ እንቅስቃሴ የተመራው በንዑስ ከበርቴው በተለይም አንድ ክፍሉ በሆነው በወታደሩ እንጂ በሠራተኛው መደብ አይደለም:: በውነቱ ይህንን መሠረታዊ

እውነት የፌዴሬሽኑ ደጋፊዎች እኛን ብለው ባይከቱትና ከስህተታቸው ምንጭ አንዱ መሆኑን በናዎን ኖሮ እዚህ ዝርዝር ውስጥ ባልገባንም ነበር፡፡ግን ሃሳባችንን መግለጥ አለብን፡፡

በቲዮሪ መልኩ ስናየው በአዲሱ ዲሞክራቲክ ረቮሉሽን ጎዳና ላይ ቆናውን የረቮሉሽኑን ፀይል—ገበሬውን—ለመምራት የሚሻኙት ሁለት ኃይሎች ንዑስ ከበርቴውና ሠራተኛው መሆናቸውን ማንም የሚያውቀው ነው፡፡ዛሬ የንዑስ ከበርቴ መደብ ከሠራተኛው ቀድሞ ገበሬውን ለማሰለፍ 'መሬት ላራሹ'ብሎ ቢነሳ፣ለጠቅላላው ሕብረተሰብ 'የንግግር የጽሑፍ ነጻነት'ብሎ ፊውዳሊዝምን ለመደምሰስ ግንባር ቀደም ሆኖ ቢታይ የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፡፡በአዲሱ ዲሞክራቲክ ረቮሉሽን ሠራተኛው መደብ ከግቡ ያደርሰዋል ተብሎ እንጂ ይህ ረቮሉሽን በሚቀጥለው በሙሉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እሱ ይመራዋል ማለት አይደለም፡፡እንደዚሁም ደግሞ ንዑስ ከበርቴው ፀረ— ኢምፔሪያሊስት ፀረ— ፊውዳሊስት ትግሉን ከግቡ ሊያደርሰው አይችልም ተብሎ እንጂ ለተወሰነ ጊዜ ግንባር ቀደም አይሆንም ማለት አይደለም፡፡ይህንን እውነት አለመገንዘብ ትልቅ የቲዮሪ ስህተት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ስለረቮሉሽኖች ታሪክ ሰምተን የማናውቅ ያስመስልብናል፡፡

ዛሬ በገራችን ባይናችን የምናየው ይህንኑ ነው፡፡እስከዛሬ ትግሉ በግንባር ቀደምነት የተመራው በወታደሩ ክፍል፣በምሁራኑ፣በተማሪዎችና በስተማሪዎች ነው፡፡እነዚህ ክፍሎች ጠቅላላውን የሕዝቡን ጥያቄዎች በአጠቃላይ ከማቅረባቸውም በላይ በተለይ ወታደሩ የመንግስት ሥልጣን ውድድር ውስጥ በቀጥታ ገብቶ ሲታገል እናየዋለን፡፡ይህንን እውነት መሸፈን፣ አልፎ ተርፎ እንደፌዴሬሽኑ ጓዶች ትግሉን የሚመራው ሠራተኛው ነው እያሉ በሬ ወለደ ብሎ ማውራት <u>ሠራተኛው ለአመራሩ እንዳይታገል ማዘናጋት ማለት ነው፡</u>፡በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ጎዳና ላይ የሠራተኛውን አመራር የሚጻረረው ዋናው ኃይል ንዑስ ከበርቴው ሆኖ ሳለ፣ ይህንን አመራር ሠራተኛው ከንዑስ ከበርቴው መንጠቅ እንዳለበት ሲታወቅ፣ ለዚህም የፖለቲካ ንቃቱን ከፍ አድርጎ ፓርቲውን ማደራጀት ዋና ተግባሩ መሆኑ ሲታወስ፣ይህንን አመራር ንዑስ ከበርቴው እንደያዘው አፍረጥርጦ አለመናገር የሠራተኛውን ሕዝብና የረዥሙን የነጻነት ትግል ትጥቅ ማስፈታት ነው እንላለን፡፡ምንም እንኳ ይህ አደገኛ ፖለቲካ የሠራተኛውን ወገን መርጠናል በሚሉ ሰዎች ቢሰነዘርም፣ ዘር ዘር የኢትዮጵያ ሕዝብ እድል በንዑስ ከበርቴው እንደተያዘ እንዲቀር የሚያግዝ በመሆኑ የተኛ አድርባይ አቋም ነው እንላለን፡፡በዚህም በውሮፓ የምንገኝ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለዘላቂውና ለረዥሙ ትግል ቆርጠን ተነስተናልና፣ ይህ ማደናገሪያ እውነቱን ከኢትዮጵያ ሠራተኛ እንዳይሸፍን ለኢትዮጵያ ሠራተኛ 'የዛሬውን ትግል አንተ አልመራኸውም፡፡የመራው ንዑስ ከበርቴው ነው፡፡ ይህ የንዑስ ከበርቴ መደብ በረዥሙ ፀረ—ፊውዳልና ፀረ— ኢምፔሪያሊስት ትግል ላይ ወላዋይነት ያጠቃዋል፣ዘር ዘር ለመክዳት ስለማይመለስ የኢትዮጵያ ተስፋ ባንተ በሠራተኛው መደብ አመራር ላይ የተጣለ ጉዳይ ነውና አመራሩን ለመያዝ ተደራጅ፣-በርታ፣ ታገል' እንላለን፡፡

እንደዚህም ስለሆነ ዛሬ ሰው ሁሉ ሕዝባዊ መንግሥት እያለ መሪ ቃሉን ከያለበት ይወረውራልና፣ ትግሉ በሠራተኛው ስላልተመራ የዚህን መሪ ቃል ምንነት ባናስረዳው ዝም ብለን ሕዝባዊ መንግሥት ምረጥ አንለውም፡፡ከፌዴሬሽኑ ጓዶች ያለን አንዱ ሌላው ልዩነት



ይህን የጊዜያዊ መንግስትና ሕዝባዊ መንግስት የሚመለከት ነው፡፡በዚህም በኩል በምንም ዓይነት የማይናወጽ ረቮሉሽናዊ አቋም አለን፡፡ዛሬ አድሃሪውም፣አድርባዩም፣ሪፎርሚስቱም ተራማጁም ተደምሮ 'ሕዝባዊ መንግሥት'እያለ የሚጮህበት ወቅት ነው፡፡በዚህን ጊዜ እኛ ተራማጆች ለዚህ መሪ ቃል የሚሰጠውን ትርጉም ቁልጭ አርገን ማሳየት አለብን፡፡በኛ እምነት ፊውዳሊዝም ባይደመሰስ፣ኢምፔሪያሊዝም ከገራችን ገጽ ጓዙን ጠቅልሎ ባይወጣ፣ እንደዚህም እንዲሆን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተቀናበረ የፖለቲካ ቅስቀሳ ታንጾ፣ በጠነከረ አንድነት ተደራጅቶ በረዥም ጊዜ አብዮታዊ ትግል ሳይፈታን፣ በኢትዮጵያ ምድር የሚደመጠው ማንኛውም ዓይነት መንግስት፣ ሞግዚት ይባል ጊዜያዊ፣ ለአራት ወር ይሁን ለአራት አመት፣ ሕዝባዊ ይባል የተወሰነ የዘውድ አገዛዝ የሰፈውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግ ጥቅም ሊያረጋግጥ አይችልም፡፡

እንደዚህም ስለሆነዛሬ ከያለበት የሚሰነዘሩት 'ሕዝባዊ መንግስት' 'ጊዜያዊ መንግስት'፣ 'ሞግዚት መንግስት' የሚሉት መሪ ቃሎች በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ከእውነተኛው ሕዝባዊ መንግስት ምን ያህል የተለዩ መሆናቸውን ማሳየትና ወደነጻነታችን የምናደርገውን ረዥም ጉዞ እንዳያደናቅፉብን ነቅተን መጠበቅ ታሪክ የጫለብን ሃላፊነት ነው፡፡

ይህንን ሃላፊነታችንን መቀበል ባይበከልን ቀርቶ፣የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩሪ ትግል በእንደዚህ ዓይነት መሪ ቃሎች ተደናግሮ ትጥቁን ቢፈታ፣የነዚህን መሪ ቃሎች ምንነት ባናስረዳው ቀርተን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የትግሉን አመራር በያዘው በንዑስ ከበርቴው ሪፎርሚስቶች ቢደለል፣ ወደእውነተኛ ነጻነት የሚወስደውን የተደራጀ የትግል ጎዳና እንዲይዝ ባናገዘው ቀርተን ሕዝባችን የተበታተነ ትግሉን ቢቀጥል፣በዚህም የተነሳ በዘመናት ጭቆና ገንፍሉ በበዙ ሰማዕታት ሰታይ እዚህ የደረሰው ትግል መሰብሰብ አቅቶት በተደራጁ ፀረ—ሕዝብ ኃይሎች ቢገታ፣ ይህ አድርባይነታችን በታሪክ ወንበር ፊት የሚያስጠይቀን ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደነጻነቱ ወደሕዝባዊ መንግስቱ ለሚያደርገው ጉዞ አንዱና ዋናው መተማመኛ የራሱ የፖለቲካ ንቃት የራሱ ድርጅት የራሱ ትግል ብቻ ነው፡፡ወደነጻነቱ ለመጓዝ ቆራጥና መራራ ትግል እንጂ ምንም ዓይነት ሞግዚት አይፈልገም፡፡ስለዚህም ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቼውም የበለጠ ትግል በሚያካሄድበት ወቅት በዚህ የዱል ጎዳና ወደፊት እንዲገፋ 'ንቃ'፣'ተደራጅ'፣ እንለዋለን እንጂ 'ሕዝባዊ መንግስት ምረጥ'ብለን ይህን እንደጊዜያዊ ተግባር አናቀርብለትም፡፡ይህ ለረቮሉሽኑ አቋራጭ በመፈለግ ሕዝቡን ትጥቅ ማስፈታት ነው እንላለን፡፡በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ የዚህን መሪ ቃል ምንነት ካስረዳን ዘንዳ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ከሃገራችን ገጽ ለማጥፋት ለረዥም ጊዜ ትግል ታጥቀን የተነሳን ተራማጆች ወደ ነጻነት የሚያመራንን ጥርጊያ ጎዳና መተለም ይኖርብናል፡፡ይህንንም ለማድረግ አሁን አገራችን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ተግባራችንን መቀየስ አለብን፡፡ሃላፊነታችንን ከወቀን፣ለዚህ ታሪካዊ ሃላፊነት በቂ ሆነን ለመገኘት የጊዜውን ዋና አጣዳፊ ተግባር ከሌሎች ተግባሮች ሁነ ከያለበት ከሚሰነዘሩ አጫፋሪ መሪ ቃሎች ነጥለን አጉልቶ ማሳየት ለሁሉም ደግሞ በያወላውሉ መታገል ያስፈልጋል፡፡

ጓዶች፡— በእኛ እምነት ዛሬ የጊዜው ዋና ተግባር ድርጅቶችን የማደደም ነው፡፡

ከፍ ብለን እንዳልነው ከሁን ወዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከፍ ብሎ አዳዲስ ዱሎችን ሊቀዳጅ
የሚችለው የሕዝቡ ትግል ተደራጅቶና መልክ ሲይዝ ብቻ መሆኑን ተገንዝበናል::

በዚህ ጊዜያዊ ተግባር ላይ ምንም ዐይነት ማወላወል ፣ ምንም ዓይነት ቸል
ተኛነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ማሳገጥ ነው ስለምንል አቋማችን ቀጥተኛ ነው:: ስለዚህም ዛ
ሬ በዚህ ጉዳይ በቸኰልነትና በወላዋይነት የተነሳበት ወገን ለድርጅቶችና ለፓርቲያች መቋቋም፣
በተለይ የኢትዮጵያ ተስፋ የሆነውን የወዛደሩን ፓርቲ፣ በጠቅላላ ለድርጅቶች መታገል ጊዜው ያ
ለፈበት ፈሊጥ ነው እያለ ቆየት ይልና ደግሞ 'ሕዝባዊ ምርጫ' የሚለውን ሕዝቡን ትጥቅ የሚያስ
ፈታ አቋም ለንታገል ቆርጠናል:: ስለ'ምርጫ' ከተነሳ፣ ሕዝቡ ባይነቃና ባይደራጅ ማንን ሊመርጥ
እንደሚችል፣የጭቁን መደቦችና የህብረሰብ ክፍሎች ተጠሪያችስ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ?መልስ ሊገ
ኙለት ይችል እንደሆን በቅድሚያ ማሰብ በተገባ ነበር::አንደኛ— እስከዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ
'እንደራሴያችን' ለመምረጥ ከላይ ከተወረወረለት 'መብት' ይበልጥ ምን ያህል ዲሞክራቲክ እንደሚ
ሆን የኛ ጌዶች ሊገልፁልን በተገባ ነበር::ሁለተኛ— በዚህ ምርጫ ገና በቅጡ ያልተነካው የፊ
ውዳሊስቶችና የኢምፔሪያሊስቶች ቢሮክራሲ ለአድሃሪያች ሳያዳላ ምርጫውን በትክክል ያካሄዳል ብ
ለው ሊያጽናኑን ይገባቸው ነበር::ሦስተኛ— በዚህ መልክ ዛሬ ሕዝቡ የትግል ትጥቁን ፈትቶ የ
መረጠውን 'ሕዝባዊ መንግስት' ሊቆጣጠሩት የሚችሉ የነቁ ሕዝባዊ ድርጅቶች ባይኖሩ በበጎ ፈቃዱ
ብቻ የሕዝቡን ፍላጎት ያሟላል:የሚለውን ፀረ—ባይንስ የሆነ ትንተና ሊያሳምነን ይገባ ነበር::አለበለዚያ ገን፣
ሕዝቡ ተደራጅቶ ሳይታገል፣ ተደራጅቶ ሳይመርጥ፣ ተደራጅቶ የማይቆጣጠረውን መንግስት በምንም
ዓይነት 'ሕዝባዊ መንግስት' ብለን አንቀበለውም::ይህም የጌዶች አቋም በአቀራረቡ፣በለው ቀደ
ም ተከተል ሪፎርምን እንጂ ረቮሉሽንን ስለማያበስር ለዚህ ከሕዝባዊ ድርጅትና ትግል ተለይቶ ለ
ሚወለደው 'ሕዝባዊ መንግስት' ለሪፎርም ካለን አቋም የተለየ አቋም አንወስድበትም::

ዛሬ ዋና ቁምነገሩን የሕዝቡን መደራጀት በወጉ ባይጠይቅና ለሱም ቆርጦ
ሳይታገል 'የሕዝባዊ ጦር ዘመን ጠባ፣በረትህን እውጣ' ብሎ ተራማጅ መስሎ የሕዝቡን ትግል ለማ
ወናበድ የሚሞከረውን የፌዴሬሽኑን አቋም አድካሚውን የመቀስቀስና የማደራጀት ተግባር ችላ ብሎ
አቋራጭ የሚፈልግ በመሆኑ እንቋቋመዋለን::በቸኰልነቱ እናጋልጠዋለን::ዛሬ 'የሕዝብ ጦር ዘመን
ነው' ከተባለ በማንኛውም አገር ታሪክ እንደታየው የሕዝባዊ ጦር ዘመን እንዲጠባ አስቀድሞ የረ
ዥም ጊዜ የፓለቲካ ቅስቀሳ፣የሠራተኛ ፓርቲ፣ በዚህም ፓርቲ የሚመራ ሕዝባዊ ገንባር አስፈላጊ
መሆኑን ስለምንረዳ፣ ዛሬ ይህ ዘመን በኢትዮጵያ ጠባ ከተባለን አስፈላጊ የሆኑት ቅስቀሳዎች
መቼ እንደተደረጉ፣ድርጅቶች የት እንዳሉና ምንስ ያህል አጥጋቢ ውጤት እንደሰጡ ሊያስረዱን በ
ተገባ ነበር:: አለበለዚያ ይህን የጊዜውን የቅስቀሳና የማደራጀት ትግል ትዕግስት አጥቶ ጦር
ለመንከስ የሚከጅለውን ወገን አደገኛ አዝማሚያ በመሰረቱ የሚያመለክተው የጥቂት ገንባር ተደም
ነን በዮች ውር ውር እንጂ የአንዱን ሕዝብ የነቃ ትግል አይደለምና ያለአንዳች ማወላወል እን
ቃወመዋለን::በኢትዮጵያ ወጣቶች ፊት እናጋልጠዋለን::

ዛሬ ዋና ጉዳይ የምንለውን የሕዝቡን መደራጀት ጉዳይ ለማደናገር አንዴ
ለሠራተኛ ፓርቲ ብቻ እንታገል፣ አንዴ ደግሞ የድርጅት ዘመን ጊዜው አልፍአል፣ አንዴ ሕዝቡ
ያለድርጅት ነቅቷል፣ በዚያው አሩ መልስ ደግሞ የጦር ትግል መጀመሪያ ጊዜ ነው ብሎ እንደገና



ተቀልብሶ 'ምርጫ መደረግ አለበት' እያለ እንዳለቀ ባሙና እየተመላለሰ አቋሙን አሳሰወበጥ ያለ
ውን ይህ በንቅናቄያችን ውስጥ የሚነዛው ቅጥ ያጣ ውዥንብር በምን ፈሊጥ ለተበደለው ለኢትዮጵ
ያ ሕዝብ ትግል እንደሚረዳ ሊያስረዳን ይገባዋል::አለበለዚያ አድሃሪው መንግስት በእመጽ እን
ዷ ሊቋቋመው ያልቻለውን፣ በብዙ ሰማዕታት ደም ተጽፎ እዚህ የደረሰውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩ
ሪ ትግል በማደናገር ብቻ ለማዳከም መሞከር ስለሆነ ይህንን የትንሽ ከበርቴ ወላዋይነት አጥብ
ቀን እንቃወማለን::

በዝጠማሪ በፌዴሬሽኑና በማህበራችን መሃከል የታየው ልዩነትየመደራጀቱን
ጉዳይ በሚመለከተው በኩል የተማሪው ንቅናቄ ቅስቀሳ ማድረግ ያለበት የሠራተኛ ፓርቲ ብቻ እን
ዲቋቋም ነው የሚለውን አቋም ተቃውመን በሃገሪቱ የሚገኙ ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃ
ይሎች በሙሉ እንዲደራጁ መቀስቀስና ማገዝ አለብን የሚል አቋም መውሰዳችን ነው::በፌዴሬሽኑ
በኩል የቀረበው ይህ የተሳሳተ አቋም ምንም እንኳ ለሠራተኛው መደብ ተቆርቋሪ መስሎ ቢቀርብም
በረዥሙ ትግላችን የሠራተኛው መደብ አጋዥ የሆኑት ሃይሎች ተጠናክረው ትግሉን እንዳያገዙና
በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ፊት የሠራተኛውን መደብ ነጥሎ የሚያስመታ አደገኛ አዝማሚያ
በመሆኑ ማህበራችን ይህን አስተሳሰብ አጥብቆ ይቃወማል::ወደረቮሉሽኑ ለመድረስ ሊዘለው የማይ
ፈልገው ተግባር ስለሌለ፣ የድርጅቶች ዘመን አልፍአል ብሎ ከተነሳ ዘንዱ ፌዴሬሽኑ እንደገና
በቸኰልነቱ ተገፋፍቶ በሕዝብ ትግል የተገኙትን ዱሎች ችላ ቢላቸውና በእነሱ እየተጠቀመ ትግሉ
ን የማራመዱ ጉዳይ አርገፍ አርጎ ቢተወው ፈጽሞ አይደንቀንም::ማህበራችን ከጊዜያዊ ተግባሮች
አንደአንዱ የወሰደው በተገኙት ሪፎርሞች በመጠቀም፣ እነዚህም ሪፎርሞች ተመልሰው በገዢው መደብ
እንዳይነጠቁ ድርጅቶች አስፈላጊ መሆናቸውንና በእነርሱም አማካይነት ትግሉ ወደፊት እንደሚገፋ
ማሳየትን ነው::በኢዙናና በፌዴሬሽን በኩል በዚህ በሪፎርም ጉዳይ በመጽሔቶቻቸው እንዳየነው
እነዚህን በትግል እንጂ በገዢ መደቦች መልካም ፈቃድ ያልተገኘውን ሪፎርም በመናቅና በዚህ
ሪፎርም በመጠቀም ተጠቅሞ አብዮታዊ ትግሉን ማራመድ ይቻላል የምንለውን 'ሪፎርሚስቶች'ናችሁ
በማለት ቢወነጅሉን ቆይተዋል::ይህ ገን በሪፎርሞች መጠቀም እንዳለብን፣ ተመልሰው እንዳይነጠቁ
የድርጅቶች ዋስትና እንደሚያስፈልገና ለዚህም መታገል እንዳለብን፣ ዘር ዘር ደግሞ የሪፎርሞች
ምንነት በማሳየት ዘላቂ ዱል የሚገኘው በረቮሉሽን ብቻ መሆኑን ማስገንዘብና ወደሱም ማምራት
እንዳለብን ፈጽሞ አያስተነም::

በዚህ አጋጣሚ በተለይ ለመጥቀስ የምንፈልገው በአህጉራችን በአፍሪቃ ያሉ
ትን የነጻ አውጪ ታጋዮችን ነው::ለብዙ ዓመታት ሲታገሉ የቆዩት የጊኒ ቢሳዎ የአንጎላና የሞ
ዛንቢክ ሕዝቦች ነጻነታቸውን የሚቀዳጁበት ወቅት በሰምንታትና በወራት የሚቆጠር ሆኖ ይገኛል::
በተለይ የአንጎላና የሞዛንቡክ ነጻ መውጣት የዚምባብዌን የናምቢያየአዛኒያን ሕዝቦች ትግል እ
ንደሚያፋፍም አይጠረጠርም::

የኤርትራ ነጻ አውጪ ገንባሮች በተለይ ከየካቲቱ አንቀስቃሴ ወዲህ አድሃሪ
ውን የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ አካባቢ ትግል መኖሩን እንዲያምን ከማስገደዱም በላይ ከገንባ
ሩ ጋር ውይይት ለማድረግ ጥሪ እንዲያቀርብ አስገድዶታል:: በኛ አስተያየት የኤርትራው ጥያቄ
ዘላቂነታ ያለው መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው የኤርትራ ሕዝብ የራሱን ዕድል ለመወሰን ያለው መብት

ሲታወቅና በድርጊትም ሲከበር ብቻ ነው፡፡ በታጋዮች መካከል ስላለው ችግር አቋማችን አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ደጋግሞ ጥሪ በማድረግ ብቻ ይወስናል፡፡ በኛ አስተያየት ኢኤልኤፍም ሆነ ፒኤልኤፍ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት እስከሆኑና ሁለቱን ጦሮ ሠራዊቶች እስከተቀጉ ድረስ በውስጥ ጉዳያቸው በመግባት አንዱን ከአንደኛው የምንመርጥበትና ይበልጥ ተራማጅ ነው የምንልበት ምክንያት የለም፡፡

የኢትዮጵያን ነጻ አውጪ ግንባር በሚመለከተውም በኩል፣ ማህበራችን በ1972 አንቀኔ ጉባዔ ድጋፍ መስጠቱ ይታወሳል፡፡ በዚያን ጊዜ ለግንባሩ የተሰጠው ድጋፍ በሌላ ጠቅላላ ጉባዔያችን እስከልተሸረ ድረስ የማህበራችን አቋም ሆኖ ይቆያል፡፡ በዚያን ጊዜ ለግንባሩ የተሰጠው ድጋፍ በፕሪንሲፕል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይኸውም ማህበራችን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነ ዲሞክራቲክ ግንባር በመሆኑ በአገራችን ወደፊት ለሚፈጠሩት እንዲሁ ያሉ ተደራጅተው ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመወጋት እስከተነሱ ድረስ [illegible]፣ የሚሰጠውን ድጋፍ ከመስጠት መቆጠብ የለበትም፡፡ የፌዴሬሽኑ ጽ. ቤት በአሉባልታ ላይ ተመስርቶ የግንባሩን ስም ለማጥፋትና ግንባሩን በተራማጆች ፊት ለማጋለጥ የሚያደርጉትን ዐረ አብዮት ድርጊት በጥብቅ እንቃወማለን፡፡

ጓዶች፡- ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው አንዳንድ ልዩነቶች በተለይ በውጪ አገር የሚገኘውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከፋፍለውት ድርጅታዊ አንድነቱን አሳልተው ይገኛሉ፡፡ በኛ እምነት የፓለቲካ ልዩነቶች መኖር ድርጅታዊ አንድነታችንን ሊያሳሳው አይገባም፡፡ ስለዚህ በልዩነቶቻችን ላይ በቁም ነገር እየተወያየን ድርጅታዊ አንድነታችንን እናጠንክር ዘንድ እነሆ ዛሬ በዚህ ጉባዔያችሁ ላይ ተገኝተን ለመወያየት ቀርበናል፡፡ የድርጅታዊ አንድነታችንን ለማጠንከር ከፈለግን ዛሬ በዚህ ጉዳይ የት እንዳለን መወያየት ተገቢ ይመስለናል፡፡

ዛሬ የት ነው ያለነው? ዛሬ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ መከፋፈልና መስነጣጠቅ ተስፋፍቶ የሚታይበት ወቅት ነው፡፡ በሰሜን አሜሪካ በ1971 በኢዙና ጉባዔ ማጆሪቲውን ረግጦ የወጣው ቡድን ከስህተቱ ተምሮና ገለሂስ አድርጎ በሰፊው ዲሞክራቲክ ንቅናቄ ውስጥ ተመልሶ ድርጅታዊ አንድነት እንዲመሰርት የተደረገውና የሚደረገው ጥረት እንዲቀጥል ያስፈልጋል፡፡ በቅርብ ምስራቅና በአፍሪካ፣ በካይሮ በአልጄሪያና በሱዳን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች 'በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር' አቋቁመዋል፡፡ በዚሁ ቀበሌ ደግሞ በዚሁ ስም በሱዳን፣ በሊባኖስና በኢራቅ -እንዲሁም በሊቢያ ተበበሬነት- ሌላ 'በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር' አቋቁመዋል፡፡ በምድረ ሱዳን በአንድ ስም የሚጠሩ ሁለት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ይገኛሉ፡፡

በአህጉር ማህበራት ግንኙነት ደረጃ ከ1971 በፊት በአውሮፓና በአሜሪካው ማህበራት መሃከል የነበረው የጠበቀ ግንኙነት እጅግ ከመላላቱ የተነሳ ዛሬ አለ ለማለት እንኳ አያስደፍርም፡፡ በሃገር ቤቱና በውጭ አገር ባለው ንቅናቄ መሃከልም ቀድሞ የነበረው የተቀናበረ ግንኙነት ባለፉት ዓመታት በሃገር ቤት ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ፋሽስታዊ ገፍና ፋሺስቱ መንግስት የሃገር ቤቱን ንቅናቄ ከውጭ አገሩ ንቅናቄ ለመነጠል በመታው ቢራ እጅግ ሳልቶ ነበር፡፡



በዚሁ ፋሺስታዊ ገፍ የተነሳ ብሔራዊው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከውጭ ተራማጅ ድርጅቶች ጋር በተለይ ከነ'አይ ዩ ኤስ' የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ በንቃት ደረጃው በዓለም ከፍተኛ ደረጃ ሲኖረው የሚገባው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በአውሮፓና በአሜሪካ በምንገኝ ማህበራት እንጂ በቀጥታ ግንኙነት በመመስረት ተገቢ ቦታውን ሳይዝ ቀርቷል፡፡

ይህን ሁሉ ተመልክቶ በ1972 ዓ.ም በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቅናቄያችን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በተሻለ የሚቀነባበርበትን ዘዴ ለመወያየት ጉባዔ እንዲጠራ ሃሳቡን ካፈለቀ በኋላ ሃሳቡም ተቀባይነት አግኝቶ ጉባዔ ቢጠራም በዚህ ጉባዔ ላይ የተቋቋመው ፌዴሬሽን በያለበት አባሳት ተወያይተው ባላፀደቁት ጥቂት ሰዎች ፀዶቁ፣ እነኚሁ ጥቂት ሰዎች እርስበርስ ተሿሹመው እንደልብ አያሸሸሉ ከሥራ ላይ በቀሉት ሕገ ማህበር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ አንድነትን ከማምጣቱ ይልቅ በንቅናቄያችን ውስጥ የነዘው ውዥንብርና መከፋፈል ያመዝናል ብንል ስህተት አይመስለንም፡፡ በዚሁ ይበልጥ ደግሞ መላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትን ለማቀፍ ታስቦ የተቋቋመው ፌዴሬሽን በልዩ ልዩ ምክንያቶች በአሁኑ ወቅት አብዛኞችን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አግልሎ እንደሚገኝ ገልጽ ነው፡፡ ዛሬ ያለአንዳች ማወላወል የፌዴሬሽኑ አባል ሊባል የሚችለው ኢዙና በመሆኑ፣ የፌዴሬሽኑና የኢዙና መሥመሮች ፈጽሞ አንድ በመሆናቸው ይህ ፌዴሬሽን የኢዙና ሌላ መጠሪያ ስም ነው ቢባል ስህተት አይመስለንም፡፡

ፌዴሬሽኑ 'አባሎቼ ናቸው' እያለ ከሚጠቅሳቸው ማህበራት ውስጥ የኛ ማህበር የፌዴሬሽኑ ሕገ ማህበር ፀረ-ዲሞክራቲክ ይዘት ከተቃወመ ወዲህ አባላት ሁሉ ዓመት ሙሉ ተወያይተው ያፀደቁትን ሕገ ማህበር ይዞ አባል ለመሆን ሊወያይ ይኸው ገና ዛሬ ጉባዔያችሁ ላይ መገኘቱ ነው፡፡ የአገር ቤቱ ንቅናቄ የፌዴሬሽኑም ሆነ የአለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ደንቡን መርምሮና ተወያይቶ አባልነቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ጠቅላላ ጉባዔ ለማጥራት ከፋሺስታዊው አገዛዝ ጋር የሚያደርጉት ትግል ፋታ ነሷቸው ስለነበር እስከዛሬ አባልነታቸውን ሊያፀድቁ አልቻሉም፡፡

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተደራጁት የቢቶች ፀጥናት ከበቦች በመሪዎች ፈላጭ ቆራጭ ውሳኔ ብቻ የፌዴሬሽኑ አባል ናችሁ ሲባሉ ቢቆዩም 'አባልነታችንን ተወያይቶ ሊወስን የሚችለው ሕጋዊ አካል ጠቅላላ ጉባዔያችን ብቻ ነው' በማለት በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ እስከዚያ ድረስ ገን የፌዴሬሽኑ አባል አለመሆናቸውን በይፋ ገልፀዋል፡፡

ፌዴሬሽኑ ቢቋቋም ሱዳንን አወከሳለሁ ብሎ በጉባዔው የተገኘው ጓዱ በከርቶም ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ወኪል ብቻ መሆኑንና በሱዳን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የፌዴሬሽኑ አባል ነው በማለት ከጠቅላላው ጉባዔ በፊት የተወሰደውን ችኩልና ፀረ-ዲሞክራቲክ አቋም በመቃወም ከሱዳን አንዳንድ ጓዶች ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል፡፡ በዚህም ጉዳይ በተነሳው ውዝግብ ዛሬ በሱዳን ሁለት ማህበራት አሉ፡፡

በአልጄሪያ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በቀበሌው ከተቋቋሙት ሁለት 'በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር' አንዱ ውስጥ ገብቶ የፌዴሬሽኑ አባል ለመሆን ጥያቄውን አቅርቧል፡፡ እውስጥ ሆኖ እንዲገባ ማመልከቻ አቀረበ ከልተባለ

የአልፕሪያ ማህበር ከሌሎች ጋር ተጠቃሎ ለመግባት ከፌዴሬሽኑ ወጥቷል ለማለት ይቻላል::

እንግዲህ በአንዳንድበጥቃቄያ በተወሰኑ ድርጊቶች ልዑካኖቻችንን አብሳል ተን መወያየት ገና በለመቻላችን፣ የአብዛኛውን ተማሪ ፍላጎት ለማክበር ምንም ዓይነት ዲሞክራቲክ ዘንበሏ በለመኖሩ የልዑካኖች ማጥ ውስጥ ገብተን፣ ንቅናቄያችን ቀድሞ የነበረውን ትብብር ያንዱነት መንፈስ አጥቶ ይገኛል::ይህን እውነት በይሉኝታ ተፈራርቶ መሸሸጉ ለአዱገታችን በሰ ማይበጀን ዱከሞችን አፍረጥርጠን ለማስየት መርጠናል::

ጥያቄው እንግዲህ ምን እናድርግ የሚለው ነው:: በለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንዱነት በዚህ ጉባዔያችሁ በምንወያይበት ጊዜ በኛ በኩል ውይይቶች የሚመሩት በነዚህ በሚቀጥሉት ሶስት ዓላማዎች ተመርኩዘው ነው::

1ኛ:እስካሁን ፌዴሬሽኑ አብዛኛቹን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ከከልሉ ውጭ ያደረገበት ምክንያት ፀረ—ዲሞክራቲክ አንቀጾችና የጠበቀ ማዕከላዊነት ሥራን የሚይዙ፣ለልዑካኖቻችን በታ የማይሰጡ፣ ተበሳልተው ከመፈታቻቸው ይልቅ ሲያፍኗቸው የሚሠከሩ በመሆናቸው ነው::ስለ ዚህ ዲሞክራሲ መከበርም የአያንዳንዱ አባል ማህበር አቶኖሚ በይበልጥ መጠበቅ ይኖርበታል:: ለዚህም በማሰብ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ያለባቸውን ሃላፊነት ጠንቅቀው በመገንዘብ የማህበራችን አባላት ከዓመት በላይ ተወያይተው የነደፉትንና ከያለበት በመጡ ወኪሎች ጉባዔ ያረቀቁትን ሕገ ማህበር ይዘን ቀርበናል::

2ኛ:የፌዴሬሽኑ ድክም ከፀረ—ዲሞክራቲክ ይዘቱ ሌላ አብዛኛውን የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄዎች በየምክንያቱ ለመሰብሰብ በለመቻሉ ነው::በኛ ግምት ስም ለማሟላት ብቻ ማህበራት በያለበት እየተሰነጠጠቁ ፌዴሬሽኑ ውስጥ በአባልነት መመዝገባቸው ብቻ ለንቅናቄያችን ምንም ዋጋ አይኖረውም::አሁንም በያለበት በአንዱ ስም ሁለት ማህበራት ሲቋቋሙ አብዛኛውን የሚያወክለውን ብቻ በማወቅ ሌሎቹ በትግሉ እንዲደበለቁ አምቢ ባሉ ደግሞ በጥብቅ በማውገዝ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የሚነዙትን ጠንቅ መዋጋት ያስፈልጋል::ለዚህም መፍትሄ እንዲሆን በጊዜው ተጠበጭ ሃሳቦችን እናቀርባለን::

3ኛ:ንቅናቄያችንን ከሚያደክሙት ምክንያቶች አንዱ በአገር ቤትና በውጭ አገር ያሉት ማህበራት በሚገባ ተቀነባብረው ሥራ ተከፋፍለውና ተደጋግፈው ወደፊት መራመድ አለመቻላቸው ነው:: ይህም የተጣራ አመራር በመጉደሉ ነው ብለን እናምናለን::በውጭ አገር ያሉት ንቅናቄዎች በከበቢያቸው ባለው ሁኔታ ፖሊሲያቸውን እየቀየሩ፣ፕሮግራማቸውን እያወጡ ትግላቸውን ማካሄድ ይችላሉ:: ነገር ግን በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ መስመር ለመቀየስ፣በአጠቃላይም ቢሆን የሥራ ትልም ለማውጣት፣የጊዜውን ተግባሮች ቀደም ተከተል ለመወሰን ቢሆን ኒውዮርክ ወይም ፓሪስ፣ በርሊን ወይም ቤይሩት ሆኖ አጠቃላይ አመራር ለመስጠት አዳጋች መሆኑ ግልጽ ነው::ስለዚህ ንቅናቄያችን ከሃገሪቱ የትግል ደረጃ ጋር አብሮ እንዲራመድ በየጊዜው ዋናዎቹ ታጋዮችና ግንባር ቀደሞች በአገር ቤት ያሉት ጓዶች ስለሆኑ እነሱ ሁኔታውን በቅርብ እያመዛዘኑ አመራሩን የማቀናበሩን ተግባር ማካሄድ አለባቸው::



በጥሩ በማንኛውም አገር እንደሚደረገው በውጭ አገር የሚገኘው ንቅናቄ ለዋናው የትግል ሜዳላይ ለሚገኘው ለአገር ቤቱ ንቅናቄ ተቀጣይና አጋዥ እንጂ፤ከውጪ ሆኖ ንቅናቄውን መምራት ይቅርና በቅሙም ማቀናበር ስለማይችል፣ በኛ ግምት ለጥንካሬያችን ዋስትና የሚሆነው በውጭ ያለው ንቅናቄ ለትግሉ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ አመራሩ አገር ቤት በለው ንቅናቄ መሆን አለበት::ሁላችንም እንደምናውቀው ፊሽስታዊው አገዛዝ ንቅናቄያችንን ለማዳከም ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ የኢትዮጵያ ወጣቶች በዓለም ተራማጅ ተማሪዎች ንቅናቄ ሸንጉቶች ተገቢ በታቸውን እንዳይዙ ግንኙነታቸው እንዳይዳብር አፍኖ መያዝ ነበር:: በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እንዳይቀነበበር፣ በውጭ የሚገኘው ንቅናቄ ከሃገር ቤቱ እንዲነጠልና እንዳይተጋገዙ መሞከሩን እናውቃለን::አሁን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በበገኙቀቻው ድል በመጠቀም በሃገር ቤቱ ንቅናቄ ላይ የሚደረገውን አጥር መበባበርና በመሃከላችን የጠበቀ ግንኙነት መመሥረት፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በዓለም ተራማጅ ወጣቶች ንቅናቄ ተገቢ በታውን ማስያዝ የሚቻልና ቅድሚያም የምንሰጠው ዓላማችን ነው::

እንደኛ-- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው ሲታገሉ አጠቃላይ አመራሩ በትግሉ ሜዳ በሚገኙት ጓዶች መሆን ይገባቃል::የአገር ቤቱ ንቅናቄ በአለም አቀፍ ተራማጅ ወጣቶች ሸንጉቶች ሁሉ እየተገኘ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምጽ እንዲያሰማ በጠቃላይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ስም በሚደረገው ግንኙነት በሃገር ቤቱ ጓዶች በቀጥታ እንዲካሄዱ ግቦራችን ይታገላል::

እንግዲህ ማህበራችን በዚህ ጉባዔ የሚጠይቃቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች በላይ የጠቀስናቸው ሶስቱ ሲሆኑ ለማጠቃለል ያህል:—

1ኛ:—በያለበት የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበሮችን ለማጠቃለል እንዲቻል የፌዴሬሽኑ ሕገ ማህበር በዲሞክራሲ ላይ የተመሰረተና የአያንዳንዱን አባል ማህበር አውቶኖሚ እንዲያከብር

2ኛ:—ይህንን ጠቅላላ ጉባዔ በሚመለከተው በኩል በ1—6—74 አስረከበው ሥራ አመራር ኮሚቴ 'አሁን ተደራጅተውና በውጭ የሚገኙ የኢት.ተ.ማህበራት በሙሉ ተጋብዘው የሚሳተፉበት' ጉባዔ እንዲሆን በውርግ ማህበር ስም በጻፈላችሁ መሠረት ዛሬ በዚህ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍ የመጡት ማህበራት በሙሉ በጉባዔው ሥራ ማለትም በአጀንዳዎች በሙሉ እንዲካፈሉ እንዲደረግ:: ይህም ማለት የቤቶች የጥናት ክበብ፣የሁለተኛ የመካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አፍሪካ የአከባቢ ማህበሮች፣የሱዳን ሁለቱ ወገኖች ሲሆኑ፣እነኝህን ማህበራት የሚመለከቱት ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ::ይህ ግን በሥራ ላይ ሳይውል ቢቀር የተደራጁ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትን በሙሉ በማቀፍ ትግሉን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያቀናብር የሚፈለገው ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን ሙሉ ተጠያቂና ሃላፊ መሆኑን በጥብቅ እናስጠነቅቃለን::

3ኛ:—ትግሉ ከዘጠበጡ የሀገሪቱ ሁኔታ ጋርና ከትግሉ ጊዜያዊ ዓላማዎች ጋር አብሮ እንዲራመድ አጠቃላይ አመራሩ አገር ቤት በሚገኙት ጓዶች እንዲሆንና የኢትዮጵያን ተማሪዎች በዓለም ተራማጆች ለመነጠል የሚደረገው አድሃሪ ጥረት ተሰብሮ በውጭ ግንኙነት በኩል የሃገር ቤቱ

ንቅናቄ በሙሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ስም በቀጥታ ከሌሎች ንቅናቄዎች ጋር ለመገናኘት እንዲሠራ እንታገላለን

እነዚህን ዓላማዎች ሙሉ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና በተለይም ለአንድነት ሲታገል የቆየውን በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበርን ጥረት የሚያንፀባርቁ ስለሆኑ፤በዚህም ጠቅላላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ያገዛሉ ብለን ስለምናምን፤ በሙሉ ነገር እንድንወያይበችውና ይህ ጉባዔያችሁ እውነተኛ አንድነታችንን የምንመሠርትበት የሁላችንም ጉባዔ እንዲሆን በአባሎቻችን ስም ጥሪያችንን እናቀርባለን:::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ለዘላለም ይኑር

ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ

ሕዝባዊ መንግስት ይኑር

በውርፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ



## በ2ኛው ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ስብሰባ ላይ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የመጽሔት ቦርድ የተሰጠ የአቋም ግለጫ

ውድ ጓዶች:

ዲሞክራሲን መሠረት ባያደርግ ከቆመ ድርጅት ዲሞክራሲያዊ የአሰራር ዘዴ አይጠበቅበትም:: የዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን ሲመሠረትም ሆነ አሁን፤ብዙ የተማሪ ማህበራትን ውጭ ያስቀረ በመሆኑ በዓለም ዓቀፍ ተማሪዎች ማህበራት ስም የጥቂት ማህበራትን — ምናልባትም የጥቂት ግለሰቦችን — አቋም ያስረጭበት የነበረው 'ቡለቲን' ለዚሁ ማረጋገጫ ነው::

የዚህ መግለጫ ዓላማ፤ወደፊት ሁሉን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የሚያቅፍ ዓለም ዓቀፍ እንዲሆን በፈለግን፤በዚሁ ድርጅት ስም የሚወጣ መጽሔት ያብዛኛውን ማህበራት አቋም የሚያንፀባርቅ እንጂ የተወሰኑ ሰዎች መጠቀሚያ እንዳይሆን ከፈለግን፤እስካሁን የነበረውን የፌዴሬሽኑን የተሳሳተ የአሰራር ዘዴ አጋልጠን ከዚሁ ትምህርት ለመውሰድ ነው:: ይህንንም የምናደርገው የተሳሳቱት ራሳቸውን ለማረም ዝግጁ ከሆኑ ከስህተቱ የሚገኘው ትምህርት ወደፊት አብሮ ለመስራት ለምናደርገው ጥረት መንገድ ይከፍታል በማለት ነው::

በመጀመሪያ በፌዴሬሽኑ ቡለቲን ላይ ያሉትን ቅሬታዎች በሶስት ከፍለን ለነሱ ማረጋገጫ እየጠቀስን አጭር አስተያየቶች ከሰጠን በኋላ በተማሪ መሃበራት መሃከል በተነሱትና ወደፊትም ሊነሱ በሚችሉት ልዩነቶች ላይ የማህበራት ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበትና የዓለም ዓቀፍ ድርጅትም በዚሁ ላይ ሊወስደው የሚገባውን አቋም ለማስየት እንሞክራለን::

የፌዴሬሽኑ ቡለቲን:— 1ኛ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ይቅርና የፌዴሬሽኑ አባላት ናቸው የሚባሉትን እንኳ ያልወከሉትን አቋምና ግምት የጠቅላላው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አቋምና ግምት አስመስሎ ያቀርባል::

2ኛ የተቃረኑ ሃሳቦችን፤ የተሳሳቱ ትንተናዎችን፤ግራ የሚያጋቡ ሃረጎችን-በየጊዜው የሚቀያየሩ ቢቀያየሩ ደግሞ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ መልዕክቶችን እያሠረጠ ለተማሪውና ለሰፊው ሕዝብ ትልቅ የፖለቲካ ትምህርት ለመስጠት አመቺ በሆነበት ጊዜ አከል የፈጠረ ነው::

3ኛ ለተማሪው ንቅናቄ አንድነት ከበረከተው ይልቅ፤አዘጋጆቹና በሱ አከባቢ ያሉ ሰዎች የሚቃወሟቸውን ግለሰቦችና ማህበራት ስም ለማጥፋት የሃሜት የጥርጣሬና ያልተረጋገጡ ወሬዎች ማሰራጫ በመሆን ያገለገለ መጽሔት ነው:

1ኛ:— የፌዴሬሽኑ ቡለቲን አዘጋጆና በሱ አከባቢ ያሉ ሰዎች አቋም እንደተማሪ ማህበራት አቋም ስለመወሰዱ

በኛ ግምት ያንዱ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት አቋም፤ይህ ድርጅት የሚሰጣቸው መሪ ቃሎች ቢያንስ በርሱ ሥር የተደራጁ ማህበራት አቋሞች፤አብዛኞች የሚስማሙበት መሪ ቃል መሆን አለበት::በተለይ ባገራችን ታይቶ የማይታወቅ የሕዝብ ትግል ባለበት ባሁኑ ጊዜ በተማሪ ማህበራት ስም የሚሰጡ መሪ ቃላት በልዩ ጥንቃቄ በዲሞክራሲያዊ መንገድ መወሰን አለባቸው::

አንዱ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል:—

"To this end patriotic democracy must come out with concrete and correct slogan. As such to demand the dawnfall of Endalkachew's regime and be replaced(sic!) by a care taker gove~nment that works out towards the convening of a popular government elected by the people is a timely and correct slogan." Bulletin No.6p.2

"There are many demands we must agitate around at present.In the immediate we must call for the downfall of Endalkachew's government and its replacement with a popularly elected care taker government that will prepare a free and democratic election" Bulletin No.8 page 3

ይህንን መፈ ቃል እነሷን አብዛኛች የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የፌዴሬሽኑ አባላት የሚባሉት እነሷ በየካቲት አቀርበውት አሳየንም::የዚህን ስሎጋን ጊዜያዊነት በመደገፍ በውጭ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው በአፕሪሉ የአውሮፓ ማህበራት መሪዎች ስብሰባ ጊዜ አንዱ ገለሰብ ነበር:: በዚያን ጊዜም እንኳንም ስምምነት ስላልተደረሰበት እንደማህበር አቋም ሳይወሰድ ቀርቷል::ስለ'ኬር ቴከር'መንግስት በሰፊው ለማተት እዚህ ቦታው አይደለም::ወደፊት በሌላ ቦታ በሰፊው እንመለስበታለን::በዚህ ጽሑፍ የምንሞክረው የዚህን ስሎጋን ፀረ—ዲሞክራሲያዊ አመራረጥና ፀረ-ሬቮሉሽናዊ ይዘት በጭሩ ለማሳየት ነው::

የፌዴሬሽኑ ቡለቲን አዘጋጅ ይህን በግለሰብ የቀረበ ስሎጋን የፌዴሬሽኑ አባል ማህበራት እንደተስማሙበት አድርጎ በፌዴሬሽኑ ስም ያቀርብና የተቃወሙትን ወይም በዚህ ላይ ውሳኔ ያልወሰዱትን ማህበራት እንዲህ ይላቸዋል::

" To oppose this slogan(i.e.care taker government)would mean nothing more but, 1-to depart from the revolutionary line of the student movement,2-to support the fascist ex-police chief Yilma Shibeshi, who has the comrades at home shot(sic!) and beaten for raising the slogan " peoples government", 3- and to be absolutly confident of Endalkachew's regime(!)and the conistitutional conference formed by the autocrat"Bull.No.6 p.2.Words in brakets added.

እንነዚህ አባል ማህበራት ባይነጋገሩበት ባይስማሙበት አዘጋጁ የራሱን አቋም እንደተማሪ ማህበራት አቋም መውሰዱ የዚህን ስሎጋን ፀረ—ዲሞክራቲክ አወሳሰን በግልጽ ያሳያል:: ይዘቱንም ስናየው፣'ከተማሪው አብዮታዊ መስመር የተገነጠለው'የፌዴሬሽኑ ቡለቲን እንጂ ይህን መፈ ቃል የተቃወሙት ወይንም በውሳኔው ላይ ያልተካፈሉት ማህበራት አይደሉም::

ሕዝቡ እየታገለ ልደረጅ እያለ በሚጠይቀበት ጊዜ ወደምርጫ ተመለስ ማለት ትጥቅ አስፈቺ መልዕክት ነው::ይህ መፈ ቃል.በተለይ የወዝአደሩ ድርጅት ባይኖር የሠፊውን ወዝአደርና ገበሬ ጥቅም ጠባቂ፣ ለሕዝብ የሚሰራ መንግስት ሊገኝ የሚችል የሚያስመስልአጉል ተስፋ ሰጪና አሳሳች መፈ ቃል ነው::



በፌዴሬሽኑ ቡለቲን መሠረት ይህ ጊዜያዊ መንግስት ሕዝባዊ መንግስት ለማስመረጥ ይመረጣል::በ14ኛው ጉባዔያችን በሬው የአውሮፓ ማህበር አባላት ያፀደቁልን አቋም እንደሚያሳየው፣'ሕዝባዊ መንግስት የሚያስመርጥ ጊዜያዊ መንግስት ይመረጥ'የሚለውን የፌዴሬሽኑን መፈ ቃል 'በኢትዮጵያ ሕዝባዊ መንግስት የሚመጣው በንዱ ምንነቱ በልታወቀ ጊዜያዊ የሞግዚት መንግስት አማካይነት ሳይሆን፣ሕዝቡ ተደራጅቶ በሚያካሄደው የረጅም ጊዜ ሕዝባዊ ጦርነት የሚገኝ ነው::ይህንንም ሕዝባዊ መንግስት ለማቋቋም ሕዝቡ ሞግዚት አያስፈልገውም'በማለት ስንታገል ቆይተናል፤:ያብዛኛች የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ማህበራት እንዲሁም የተራማጆች ሁሉ አቋም እንደዚሁ እንደሆነ እምነታችን ነው::

2ኛ ተለዋዋጭና የሚቃረኑ ሃሳቦች የተዘቡ ትንተናዎች በተማሪ ማህበራት ስም ስለመቀረባቸው

በዓለም ዓቀፍ የተማሪ ማህበራት ስም የሚወጣ መጽሔት በደፈናው ታሪካዊ ገዴታ አለብን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ በትግል ላይ እያለ ከፍተኛ የፖለቲካ ትምህርት ለመስጠት አመቺ በሆነበት ጊዜ ይህንኑ ገዴታችንን በስራ ላይ ለማዋልና የተማሪ ንቅናቄ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ያለውን ዝና በመገንዘብ ጠቃሚ ትምህርቶችን የያዘ በጥንቃቄ የሚጻፍ መሆን አለበት::የፌዴሬሽኑ ቡለቲን እንኳን ይህን ሊያደርግ፣ የተጠሩ አስተሳሰቦችን ለማስረጨት ለፈለጉ እንቅፋት ሆኖባቸው ነበር::

በቡለቲን ቁጥር ፭ ላይ፣ ዝቅ ብለው የወታደር አመፅ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የሚጻረር ነው:የአሜሪካ እጅ ያለበት ነው የሚሉት ወታደር ለደሞዝ ጭማሪ ሲነሳ ልክ ኢምፔሪያሊዝምን ሊደመስስ የተነሳና ይህንንም ሊያደርግ የሚችል አስመስለው "Alas, where is the unholly alliance of the Negus, the bishops, the U.S.imperialists..." ይላሉ:: የኢትዮጵያ ወዝ አደር ጦር ባለማንሳቱ በወታደር ስደፍ እየተመታ እንዲሰራ እየተደረገ፣ገበሬው በሚገባ ባለመታጠቁ በስንት መቶ እየተገደለ" The masses have taken up arms on all corners." ይሉናል::የወዝአደሩ መደብ ድርጅት ገና ሳይፈጠር፣ ይህም ድርጅት የገበሬውንና የወዝ አደሩን አንድነት መሥርቶ በሱ መሪነት ያንዱነት ግንባር ሳይፈጥር : "The situation(i.e.in Ethiopia) is very excellent to launch a protracted peoples war." ይላሉ::

ቡለቲን ቁጥር 6 ላይ እንዳልካቸው ሥልጣን ላይ እያለ በሕዝቡ ትግል ሰበብ አንዳንድ ሪፍርሞች ሊደረጉ ይችላሉ ስላልን 'ሞናርኪስቶች' 'ሪፍርሚስቶች ባለን ቆይቶ ቁጥር7 ላይ ደግሞ እራሱ የተደረጉ ሪፍርሞችን በማጋነን፣ ተንጠልጥለው ለሚገኙ ሪፍርሞች አርግጠኛ በመሆን እንዲህ ብሎ ጻፈ::

" The demands off the people were positively met;the constitution would be ammended in a such a way that the premier would be responsible to the parliament rather than the emperor;freedom of the press, speech,assembly, organizations and strikes will be promulgated." Bull. 7 p.2

ጥር 6 ላይ 'የጊዜው ተቀዳሚ ተግባር የፖለቲካ ፓርቲያችን ማቋቋም ነው' የሚለውን የማህበራችንን መሪ ቃል 'የፊሪ ሰሎጋን ነው ፣ የቀኝ ኦፖርቹኒስት መሪ ቃል ነው የድርጅት አስፈላጊነት ዘመን አልፍአል፣የሚቀጥለው የፖለቲካ ሥልጣን ለመንጠቅ የሚደረገው ትግል ነው' የሚል አነበብን::ጥር ሰባት ደግሞ " Thus the immediate tasks of the Ethiopian proletariat are to create revolutionary study groups..." የሚል መልዕክት ይዞ ቀረበ::በነዚህ ሰዎች ትንተና፣ትናንት ከሉ ድርጅት ለስልጣን ቀጥያ ለመታገል ደርስሃል የተባለው የኢትዮጵያ ወዝአደርዘሬ ደግሞእንኳን ለሥልጣን ለመታገል ለድርጅት መፍጠር ሀ ሁ የሆነውን የጥናት ክበብ እንዲፈጥር ያስገነዝቡታል::በነገራችን ላይ ጊዶች የጥናት ክበብ አቋ ቶም የሚሉት የወዝአደሩን አራቡን ነው::ቡለቲን ጥር 6 የየካቲቱ አንቀስቃሴ የአብዮት ቁዚ ማ ነው ሲበል ነበር::ቡለቲን ጥር ሰባት ላይ ደግሞ ያውም በሠራተኛው መደብ የተመራ አብዮ ት ሆኖ ቀጥ አለ::("the vanguard and leader of the February revolution that proved to be the most persistent and democratic class,the Ethiopian proletariat.")

በየጊዜው ለሚቀያየሩት ትንተናዎች ከላይ የጠቀስናቸው ምሳሌዎች ይበቃሉ:: በነዚህ ላይ ደግሞ ሳይንሳዊ ያልሆኑ አገላለጾች ለምሳሌ : "patriotic democracy","...any peoples upheaval aimed at social change is termed as a revolution..." ስጨማመሩበት በተማሪ መጽሔቶች ሲማሩ የሚችሉትን ሁሉ ከማወናበድ ሌላ ምንም እንደማይጠቅሙ ግልጽ ነው::ቡለቲኑ ትምህርት እንዲሰጥ በጥንቃቄ እንደማይዘጋጅ ከሚያሳዩት ሁለት ምሳሌዎች ጠቅሰን ወደሚቀጥለው እናልፋለን::የቡለቲን ጥር ሰባት ርዕሲ አንቀጽ አብዛኛው ፓራግራፍ ከሌሊን የተወሰደ ሲሆን 'is'በ 'was'፣ 'Russian'በ'Ethiopia'በመተካት እንደራሱ ትንተና አርጎ ያቀርበል::የኢትዮጵያን ልዩ ሁኔታ ለማሳየትና ለማስተማር የሚፈልገ ጸሀፊ ከነዚህ ዓይነቶ ሥራ ውስጥ አይገባም::ሌላኛው ደግሞ በጥር ስምንት ርዕሰ አንቀጽ ላይ የአንዳልካቸው መንግስት ይውደቅ ብለን አንጠይቃለን የሚል ስሎጋን አለበት::በዚሁ ጥር በዜናዎች ዓምዱ ላይ የአንዳልካቸው ካቢኔ ወርዶ የሚከኪል አምሩ ካቢኔ መተካቱን ራቡ ያወራል::ዜናውንና ርዕሰ አንቀጹን የያዘው ቡለቲን የታተመው በአንዱ ቦታና ጊዜ ሆኖ ስለ የአንዳልካቸውን መውረዱ አያወቀ'የአንዳልካቸው መንግስት ይውደቅ'የሚል ስሎጋን ማውጣቱ ምን ያህል በችልተኛነት እንደ ሚሰራ በገልጽ ያሳያል::

<u>ስለወዝአደሩ ሚና:—</u>

በቡለቲኑ መሠረት የወዝአደሩ መደብ የየካቲትአንቀስቃሴ ቀስቷሽና መሪ ከመሆኑም በላይ ከሁሉ መደቦች ይበልጥ ዲሞክራቲክ መሆኑን ለሰፊው ሕዝብ አረጋግጧል::("...the vanguard and leader of the February revolution,that proved to be the most persistent class, the Ethiopian proletariat.") Bull. No.7 p.3 እስከዚህ ተን ዶረስ ባሁኑ ነቀናቱ የወዝአደሩ መደብ መርቷል የሚል የፖለቲካ ግምት የሰጠ የተማሪ ማህበር



አሳየንም::በዶጋሚ ፀፌዴሬሽኑ ቡለቲን አዘጋጅና በሱ አከባቢ ያሉ ሰዎች አስተሰባብ እንደ ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት የፓለቲካ ግምት መቀረቡ ነው::ይህንኑ የአብዛኛው ማህበራት አቋም ለማስመሰል የተማሪ ማህበራት ውሳኔያች ይጠቀሳሉ::ያሜሪካውም ሆነ ያውሮፓ ማህበር የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት መሪ የወዝ አደሩ መደብ መሆን አለበት የሚል ውሳኔ አሳለፉ እንጂ የወዝ አደሩ መደብ በተከፈለበት ነቀናቴ ሁሉ መሪ ይሆናል እንበል ብለው አልተማማሉም:: እንዲህ ብለው የተነሳተ ውሳኔ ያሳለፉ አንዳንዱ ማህበራት ቢኖሩ[ምሮ:ኺን] የኢትዮጵያ ወዝ አደር ለመሪነቱ ማረጋገጫ የተማሪ ማህበራት ውሳኔ እንደማይረዳው በመገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ካለበት ደረጃ ተነስቶ የወዝአደሩን በየካቲት አንቀስቃሴ የነበረውን ሚና ሳይንሳዊ በሆነ መንገዶ መተንተን አስፈላጊ ነው::ባሁኑ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንቀስቃሴ የነውስ ከበርቴው ተራማጅ ክፍል በሚገባ ከመሳተፉም በላይ ሰፊውን ሕዝብ የሚጠቀልሉ ዲሞክራቲክ ጥያቄ ያችን አቀርቦአል::በሰፊው ሕዝብ ዘንዶም እንደለውጥ አምጪ የመታየትን ክብር አግኝቷል:: በጠቀሳሳው ፀረ—ፊሳዊ ፋሬዊ አገዛዝ ትግል የዚሁ የነውስ ከበርቴው ክፍል በወዝ አደሩ መደብ አስተሰባብ ላይ አያደገ የሚሄዶ ተጽእኖ አለው::ይህ ሁሉ የሚያሳየው የወዝአደሩ መደብ እንኳን ሌሎች ጭቁን መደቦች ሊመራ አራሱ በነውስ ከበርቴው እንደተመራ ነው::<u>እንዲያውም የወዝ አደር ወገንነትን የመረጡ ተራማጆች ዋናና ተቀዳሚ ተግባር ወዝ አደሩን ከዚሁ ነውስ ቨበርቴ አመራር ስር ማውጣት ነው::ቡለቲኑ በዚህ</u> ጥያቄ ላይ ያለውን ግምት("...vanguard and leader of the February revolution,...that proved to be the most persistent and democratic class,the Ethiopian proletariat.) በጥብቅ የምንቃወመው ከላይ የጠቀስነውን ሠራተኛውን ከነውስ ከበርቴው አመራር ሥር ለማውጣት የሚደ ረገውን ትግል የሚከዶ በመሆኑ ነው::ሁለተኛ የወዝአደሩ እስከመጨረሻው ዶረስ ዘላቂ ዲሞክራ ትነቱን በዚህ ትግል አረጋግጧል የሚለውንም በጥብቅ እንቃወማለን:: ምክንያቱም፣እውነተኛው በሰፊው ሕዝብ ዘንዶ ይቀርና በወዝአደሩ ዘንዶ እንኳ እንደ ዲሞክራት የታየው የነውስ ከበ ርቴው ተራማጅ ክፍል ሆኖ ስለ፣<u>የወዝአደሩ ዲሞክራትነት በዚህ</u> የሚወሰን በማስመሰል ይህ መ <u>መደብ እንደዘላቂ ለውጥ አምጪ በሰፊው ሕዝብ ዘንዶ ተቀባይነት ለማግኘት ገና ማድረግ ያለ በትን ትግል እንደተደረገ አድርጎ በማቀረብ የተራማጆችን ዓይን ከአንገብጋቢ ጥያቄያች የሚ ጋርዶ በመሆኑ ነው</u>::ስለዚህ ጥያቄ በሌላ ቦታ እንመለስበታለን::በጭሩ ግን ይህ የቡለቲኑ የፖለቲካ ግምት ምንም እንኳ የወዝ አደሩን ወገንነት መርጪለሁ ብሎ ደጋግሞ ቢጽፍም፣ ከላይ የጠቀስናቸውን ሁለት ዐብይና ተቀዳሚ ስራዎች እንደተፈጸሙ አድርጎ በማቀረብ እውነተኛውን የመደብ ትግል ሁኔታ ከተራማጆች ዓይን የሚከልል አደገኛ ግምት መሆኑን ጠቅሰን እናልፋለን::

<u>ሳንጋዶ ፓርቲ ወይስ ሳብዙ ፖርቲዎች ቅስቀሳ እናድርግ?</u>

ቡለቲን ጥር ስዶስት የተማሪ ውሳኔያችን በመቀየስ [redacted] የወዝ አደሩ ፓርቲ ብቻ እንዲፈጠር ቅስቀሳ እናደርጋለን ይላል፡፡ የሰሜን አሜሪካውም ማ ህበር ሆነ ያውሮፓው ማህበር ሳዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት የወዝ አደሩ መደብ ፓርቲ መፈጠር አስፈላጊነትና ይህም ፓርቲ የመሪነት ሚና እንደሚወስዶና መውሰዶም እንዳለበት ወስኑ እንጂ፡

ሌሎች ፀረ—ፊውዳሊስት ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች እንዲደረቹ ቅስቀሳ እንዳያደርጉና እንዳያገዙ አልተሰማም::በዚህ ጥያቄ ላይም የፌዴሬሽኑን ዓይነት አቋም የወሰደ ሌላ የተማሪ ማህበር እስከሁን አላየንም:: እንደገና የቡለቲኑ አዘጋጆና በሱ አከባቢ ያሉ ሰዎች አቋም እንደጠቀሳላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አቋም መቀረቡ ነው::እንደልማዳቸውም ይህን የነሱን አቋም ያልተቀበሉ ማህበራትን፣በጥያቄው ላይ በቲ ውይይት እንኳ ባይደረገ ቀኝ ኦፖርቹኒስት 'ፊሊስቲን' እያሉ ይሰደበሉ::በውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 14ኛ ጉባዔ የወዝአደሩ ድርጅትና ሌሎችም የፀረ—ኢምፔሪያሊስት ፀረ— ፊውዳሊስት ሃይሎች ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ቅስቀሳ እናደርጋለን ብሉ ወስኗል:: ስለዚህ አቋም ትክክለኛነት በስሬው ወደፊት እንመለስበታለን:: በጭሩ ገን የተማሪ ማህበራት ሰፊውን ፀረ— ፊውዳሊስት ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች የሚያጠቃልልመሪ ቃል ማውጣት አለባቸው::በዚሁ መሠረት የፓለቲካ ፓርቲዎች እንዲቋቋሙ ቅስቀሳ ማድረግ ሕዝቡ ለዲሞክራቲክ መብቱ እንዲታገል የሚያበረታታ አብዮታዊ መሪ ቃል ነው:: የተማሪ ንቅናቄ ለወዝአደሩ ፓርቲ ብቻ ቅስቀሳ ስላደረገ የወዝአደሩ ፓርቲ አይፈጠርም:: እንዲህ ዓይነት ገምት ያለው ካለ ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠረረት የማያውቅ ሰው መሆን አለበት:: የወዝአደሩ ፓርቲ 'ተደራጁ' ከሚለው ቅስቀሳ ጋር አጣምረው በገቢር ሲያደራጁት የሚችሉ ንቁ አብዮታዊያን ሲኖሩ ነው::እነዚህ የሙያ አብዮታውያን እንኳ ቢሆኑ በማደራጀቱ ተገባር ለወዝአደሩ ቅድሚያ ይሰጣሉ እንጂ 'ተደራጁ' የሚለውን ቅስቀሳ ገን በሰፊው ሕዝብ መሃል ማካሄድ አለባቸው::የሌሎች ፀረ—ፊውዳል ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች መደራጀት የወዝአደሩን መደብ በምንም መንገድ አይጉዳውም:: በሌላ አንጻር ደግሞ ያንድነት ገንባር ይፈጠር እያልን እዚህ የአንድነት ገንባር ውስጥ የሚገቡ ሃይሎች ይደራጁ የሚለው መሪ ቃል እንዴት አድሃሪ እንደሚባል የሚያውቀው የቡለቲኑ አዘጋጅ ብቻ ነው::

ሌሎችም እንዲሁ የተሳሳቱ ትንተናዎችን ከቡለቲኑ እየጠቀሱ ማሰየት ይቻላል:: እዚህ ላይ የሞከርነው በነዚህ ሁለት ነጥቦች ምሳሌነት ፌዴሬሽኑ የተማሪ ማህበራት ያልተሰማሙበትንና ያልተወያዩበትን እንደነሱ አቋም አድርጉ የተሳሳተ የፓለቲካ ገምት ያስረጭ እንደነበረ ለማሰየት ነው::

በውሸት ክስ ስም ማጥፋት፣ ጥርጣሬና ሀሜት ስለማስረጠቱ፣

ቡለቲን ቀጥርሀስት ላይ በሱዳን የአድሃሪዎች ድርጅት መፈጠሩንና ይህም ድርጅት በውጭ አገር ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚገልጽ ዜና ተሰረጠ::ያውሮፓ ማህበርና በሱዳን ከሚገኙ ሁለት ማህበራት አንደኛው ስለዚህ ዜና ማረጋገጫ ወይም ቢያንስ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀውፌዴሬሽኑ ራሱ ብቻ ሊያውቀው በሚችለው ምክንያት ይህን ሳያደርግ ቀርቷል::ይህንን ዜና የማረጋገጥና የማብራራት ሃላፊነት አሁንም የፌዴሬሽኑ ነው::

ቡለቲን ቁጥር አምስት ላይ ያውሮፓ ማህበር ሥራ አመኪያጅ ኮሚቴየከይሮን ማህበር እንዲሁም የሱዳንን ማህበር ለመከፋፈል ከጀርመን መልዕክተኛ መላኩን የሚከስ አበሳትም 'በመሪዎቻቸው' ላይ እንዲነሱ የሚጠራ ልዩ መግለጫ ወጣ::የአውሮፓ ማህበር የላከው ማንም



ሰው እንደሌለና የሃሰት ክስ መሆኑን ገልጾ፣ተላከ የተባለው ማን እንደሆነ እንዲያስታውቁ ደጋግሞ ጠየቀ:: እስከ 14ኛው ጉባዔያችን ድረስ ስማቸውን እንገልጻለን የሚል ማስፈራሪያ ብቻ ነበር::በ14ኛው ጉባዔ ላይ የፌዴሬሽኑ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ በአበሳት ተወጥሮ ስለተያዘ ከአምስት ዓመት በፊት ከአውሮፓ የወጣ በአሁሮፓው አመራር ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውንና እንዲሁም የአንድ ጀርመን አገር ኖሮ የማያውቅ ከ13ኛው ጉባዔ በፊት፣ማለት ሰው ላከ የተባው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ገና ሳይመረጥ ወደአገር የተመለሰ ስም ጠቀሰ:: እንግዲህ ያ ሁሉ የክስ ጋጋታ የፌዴሬሽኑን ያሰረር ዘዴና የተሳሰተ የፖለቲካ መስመር የሚቃወሙ ማህበራትንና ገለሰቦችን የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ጠላቶች አድርጉ ለማቅረብ ፌዴሬሽኑን እስከሁን የመረ ትጋደች ያደረጉት ጥረት መሆኑን በመገንዘብ የ14ኛው ጠቅላላ ጉባዔያችን እንዳወገዘው ሁሉ አብዛኞች የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትም ይህንኑ ፀረ—አብዮታዊ የትግል ዘዴ በጥብቅ እንደሚኮንኑ እምነታችን ነው::

ቡለቲን ቁጥር ስምንት ላይ የፈረንሳይ ማህበርን ስም ለማጥፋት የሃሰት ወሬ ተሰረጠ:: አዲሱን ዲሞክራቲክ አብዮት የማይቀበሉ፣ በሕገ ማህበራቸውም 'በኢትዮጵያ አብዮት የሚካሄደው በገበሬው መሪነት በወዝአደሩ ተከታይነት' ነው' የሚሉ ኢትዮጵያውያን በገሩናብል ተደራጅተው ይገኛሉ::እነዚህ ሰዎች የፈረንሳይ ቀርንጫፍ ማህበር አባል ሆነው አያውቁም:: የፈረንሳይ ቀ.ማህበርም እነዚህን ሰዎች ማህበሩ ውስጥ ለማስገባት ያደረገው ጥረት በዓላማና በአቋም ልዩነቶች ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል::የፌዴሬሽኑ ቡለቲን አዘጋጅ ገሩናብል ደርሶ ሲመለስ በጻፈውና በኋላም በቁጥር 8 ላይ የነሱ መሆኑን የሚያጠራጥር ደብዳቤ ላይ፣የነዚህ ሰዎች ማህበር በፈረንሳይ ቀርንጫፍ ማህበር ፀረ—ዲሞክራቲክ አሰራር ምክንያት አብሮ ለመስራት ያለመቻሉንና በዚህም ምክንያት መውጣታቸውን የሚገልፁ ጽሑፎች ወጡ:: የፈረንሳይ ማህበር የፌዴሬሽኑን ፀረ—ዲሞክራቲክ ያሰረር ዘዴ የሚቃወም በመሆኑ ብቻ ፌዴሬሽኑ የዚህን ማህበር ስም ለማጥፋት በንዱ ቀርንጫፍ ማህበር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሃሰት ወሬዎችን በማሠረጠቱ በጥብቅ እንቃወማለን::

በዚሁ ቁጥር ላይ በአውሮፓ ማህበር ውስጥ በልዩ ልዩ አገር በተማሪው ንቅናቄ በሚገባ በመሳተፍ ላይ የሚገኙ ገለሰቦችን ስም እየጠቀሰ በትውልዳቸው በመመርኮዝ ፀረ—አብዮት ናቸው ብለው የሚከሱ ደብዳቤዎች ተሰረጡ:: የነዚህ ጽሑፎች በደብዳቤ መልክ መውጣት አዘጋጅን ከሃላፊነት አያድነውም:: በፖለቲካ ልዩነት ላይ መከራከር ሲያቅታቸው ኪኮፋፍኑንለሚዎከሩ አድሃሪዎች የዓላም ዓቀፍ መጽሔት የሃሜት ማሰረጫ በመሆኑ ለንቅናቄያችን ታላቅ ሃፍረት ነው::

የሰሜን አሜሪካው ማህበርና የፖለቲካ ልዩነቶቻችን

ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ የሰሜን አሜሪካው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሔቶች ያውሮፓው ማህበር በየመጽሔቶችና በየመግለጫዎች የሚወስዳቸውን አቋሞች ወደጉን እየተው፣ ከይዘት ውጭ ዓረፍተ ነገሮችን እየጠቀሱ፣ያልተባለውን ተብሏል እያሉ በማህበራችን ላይ የፖለቲካ ሳይሆን የሃሜት ዘመቻ ሲያደርጉ ቆይተዋል::ለምሳሌ ያውሮፓ ማህበር ለተማሪው የገል ጥቅም መታገል የመጀመሪያው ተገባራችን ነው ይላል:: የተማሪን ማህበር የዓንስና

የመዝናኛ ከበብ ሲያደርጋቸው ይፈልጋል የሚለውን ክስ እንውሰዱ፡፡የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር
የተወሰደው ያውሮፓው ማህበር ፕሬዚዳንት ለአሜሪካው ማህበር 21ኛ ጉባዔ ከላከው ደብዳቤ
ላይ ነው፡፡ ይህን ደብዳቤ ያነበበ፣ከዚህ ዓረፍተ ነገር በፊት ያሉትን በተለይ ልክ ከዚህ
ዓረፍተ ነገር ቀጥለው የሚገኙትን መስመሮች የተመለከተ ፣ ያሜሪካውን ማህበር የመጽሔት አዘ
ጋጆች ቀንነት እንደሌላቸው ያውሮፓ ማህበር ከዚህ ዓይነቱ ክስ ነጻ እንደሆነ በግልጽ ይገነ
ዘባል፡፡ያውሮፓን ማህበር ስራዎች፣የሚወጡትን መጽሔቶችንና መግለጫዎች ሁሉ የተከታተለ የዚ
ህን ክስ መሠረተ ቢስነት ያረጋግጣል፡፡

የኢዜና መጽሔት አዘጋጆች አንደኛው ክስ ያውሮፖ ማህበር የድርጅትን አስፈላ
ጊነትና አስቸኳይነት አይገነዘብም የሚል ነው፡፡ የፌዴሬሽኑ ቡለቲን ጥር ስድስት ደግሞ
የአውሮፖ ማህበር ያቀረበውን 'የጊዜው ተቀዳሚ ተግባር መደራጀት ነው' የሚለውን መሪ ቃል
እንደ ፊሪ የቀኝ ኦፖርቹኒስት ስሎጋን ይከንነዋል፡፡የነዚህ ሁለት ያውሮፖን ማህበር ለማስጠት
የሚይተቹ መጽሔቶች በዚህ ክስ ላይ መለያየት በድጋሚ የከባቸውን መሠረተ ቢስነት ያረጋግጣል፡፡

በ14ኛዉ ጉባዔያችን ላይ ተገኝቶ የነበረው የኢዜና መጽሔት አዘጋጅ አብዛኞ
ቹ የጉባዔ ተሳታፊዎች ያሳሰሩትን ውሳኔ በመኮነን 'የኢዜና አቋም የአውሮፓ ማይኖሪቲ አቋም
ነው፡፡እስካሁን የነበረው ቅራኔ በሰሜን አሜሪካው ማህበሩና በአውሮፓው ማህበር መሪዎች መሃል
ነበር፣ ከነገዲህ ገን ቅራኔው በሁለቱ ማህበረት መሃል ይሆናል፡፡ አብዛኞቹ የወሰዱት አቋም
የፀረ— ኢምፔሪያሊስት ፀረ—ፊውዳሊስት አቋማችንን ይቀለብሰል፡፡' የሚል መግለጫ በኢዜና ስም
ሰጠ፡፡የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ሁኔታ የሚያጠናና የኢዜናን የፓለቲካ መስመር የሚተልመው 22ኛው
ጉባዔ ገና ሳይደረግ፣ በሃገሪቱ ሁኔታ ላይ ጠሚወሰደው አቋም ገና ሳይወሰድ ጊዳ የግል አቋ
ሙን እንደማህበር አቋም በማህበር አቋም ማቅረቡን በጥብቅ እንኮንናለን፡፡

እስካሁን የሁለቱን ማህበሮቻችን ግንኙነት ካሳሉት ምክንያቶች አንዱ፣በኝዱ
በኩል ያውሮፓ ማህበር የሚያወጣቸውን መጽሔቶችና መግለጫዎች የአሜሪካው ማህበር አባሎች እን
ዳይደርሳቸው እየተደረገ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግለሰቦች ዓረፍተነገሮችን ከይዘት ጭጭ እየጠቀሱ
ያልተባለውን እለ እያሉየሚጽፏቸው የአውሮፓን ማህበር የሚከሱ ጽሑፎች እየተሰራጩ ነው፡፡ለወ
ደፊቱ የግል አቋም እንደማህበር አቋም እንደማይወሰዱና የኢዜናው መጽሔት አዘጋጅ በሁለቱ
እህትማማች ማህበሮቻችን መካከል ይፈጠራል ያለው ቅራኔ የርሱ ምኞት ሆኖ እንደሚቀር እምነታ
ችን ነው፡፡ በሁለቱ ማህበሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻልም የማያቋርጥ ጥረታችን ነው፡፡

## የፖለቲካ ልዩነቶችና የተማሪ አንድነት

በፖለቲካ ልዩነቶች ምክንያት የድርጅታዊ አንድነትን ማናጋት የምንቃወመውን
ያህል በአንድነት ስም የፖለቲካ ልዩነቶች እንዳይሸፈኑ እንታገላለን፡፡ድርጅታዊ አንድነት
ከጠበቀ በፖለቲካ መሥመር መለያየት የሚያሰዝንና የሚያስፈራ አይደለም፡፡የፖለቲካ ትግል ሲደ
ረግ ቀጥ ያጣ መልክ ከወሰደ ድርጅታዊ አንድነትን ስለሚያናጋ በጥንቃቄ፣ ትምህርት ሰጪ በሆነ
መንገድ መካሄድ አለበት፡፡ በድጋሚ ለማገባት፣ ሰው ባላለውና፡ ባልወሰደው አቋም ላይ ተነስቶ
አንዱን ማህበር መክሰስ የፓለቲካ ትግል ሳይሆን የማታለልና የስም ማጥፋት ዘመቻ ሆኖ ይቀራል
በዚህ አንጻር የአንዱ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት በማህበረት መካከል የተለያዩ



አቋሞች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ግምቶች ሲኖሩ ያንዱን ማህበር ይዞ የሌላውን ማውገዝ ሳይሆን
ውይይቱ ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ያንዱን ሃሳብ የያዙ ጽሑፎች፣ በሌላው ማህበር
አባላት ዘንድ የማሰራጨት ሃላፊነት በመውሰድ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አብዛኛው የሚደ
ገፋትን እንደ ተማሪ ማህበረት አቋም ማስተጋባት አለበት፡፡

ያውሮፓ ማህበር የመጽሔት ቦርድ በተማሪ ንቅናቄያችን ውስጥ ሁለት የቆለያ
ዩ የፓለቲካ መስመሮች መኖራቸውን በመገንዘብ፣ በነዚህም መሃከል የሚደረገውም ትግል ለሰ
ፊውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበረት አባሎች የፖለቲካ ዕውቀት እንደሚያሰፋ በማመን፣የተ
ለየ አቋም ካላቸው ማህበረት ጋር ውይይት በመክፈት የነሱን አቋም ሳይጠመዝዝ ለአውሮፓ
ማህበር አባላት ለማሰራጨት ዝግጁ ነው፡፡

በዓለም ዓቀፍ ስለመደራጀት ያለው አለመግባባት በዚህ ጉባዔ አማካይነት ተወ
ገዶ ሁሉን ማህበረት የሚያጠቃልለው የዓለም፡አቀፍ መጽሔት እስካሁን እንደነበረው ያባል ማህበረትን ግንኙ
ነትና ዝምድና የሚያሻክር ሳይሆን ግንኙነትን የሚያጠብቅ፣ የሚሰጣቸው የፖለቲካ ግምቶች
በአባል ማህበረት የተደገፉ መሆን አለበት፡፡ በመጽሔት ማሠራጨቱ ጉዳይና በሌሎችም ተግባ
ሮች የአውሮፖ ማህበር ከዚህ ዲሞክራቲክ የአሰራር ዘዴ ሳኖረው ከሚገባው የዓለም ዓቀፍ
ጋር በሙሉ ትብብር እንደሚሰራ ያረጋግጣል፡፡በመጨረሻም ይህ ጉባዔ ፌዴሬሽኑን ሁሉን የሚያ
ቅፍ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት እንዲያደርገው ያለንን መልካም ምኞት እንገልጻለን፡፡

ከየትኛውም አቅጣጫ ንቅናቄያችንን ለመከፋፈል የሚሞክሩ ሃይሎች ይውደሙ!
የኢትዮጵያ ተማሪዎች አብዮታዊ አንድነት ይጠንክር!
ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!

በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የመጽሔት ቦርድ

ይህ ጽሑፍ ባውሮፓ ማህበር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተዘጋጀ የአንድ ጊዜ ጽሑፍ ነው:: የፌዴሬሽኑ መሪዎች የጉባዔውን ቃለ ጉባዔ ስለከለከሉን የተመሰረተውም እኛ ለራሳችን ከወሰድነው ቃለጉባዔ ላይ ነው

## እኛ እንዳየነው — ስለፌዴሬሽኑ ጉባኤ አንዳንድ አስተያየት

የአለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ናቸው ተብለው ሶስት ጓዶች ከሰልሳ በላይ በሆኑ ተመልካቾች ተከበው ከመሃል ጉብ ብለዋል:: የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ጓዲት አበበች ስለጉባዔው አካሄድ የፕሬዚደንሽል ካውንስሉ ውሳኔዎች ናቸው ብላ አንዳንድ ማብራሪያዎች ሰጠች:: ከነዚህም ውሳኔዎች አንዱ ጓድ ተሰፋዬ ታደሰ በጉባዔው ላይ በተመልካችነት እንዳይገኝ የሚል ነበር:: የአውሮፓ ማህበር ዴሌጌሽን ይህ አሰራር ልክ አይደለም ለማለት ሞከረ:: ነገር ግን 'ጉባዔው አልተጀመረም፤ የመናገር መብት የላችሁም' ተባለ:: ጓድ ተሰፋዬ 'ይመዝገብልኝ' ብሎ ወጣ::

ይህ 'ጉባዔ' በተቀመጠባቸው ሰባት ቀናት ውስጥ ብዙ ነገሮች 'የፕሬዝደንሽል ካውንስሉ' ውሳኔዎች ናቸው እየተባሉ ከክርክር አምልጠዋል:: 'ካውንስሉ' ተደጋግሞ ይጠቀሳል::ጠቅላላ 'ጉባዔው' አንድ ጥያቄ አብራርቶ መመለስ ሲያቅተው 'የካውንስሉ' ውሳኔ ነው ብሎ ይመሽግና ቁጭ ይላል:: እንግዲህ ነገሩን የማያውቅ ሰው ይህ ፈላጭ ቆራጭ ካውንስል ምንድን ነው? አባሎችስ እነማን ናቸው ብሎ መጠየቁ አይቀርም::ከፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ሌላ የዚህ ካውንስል አባላት የአሜሪካው ማህበር ፕሬዚደንት ጓድ በቀለ፤ የሱዳኑ ፍስሃና የአልጄሪያው ጓድ ገዛኸኝ ናቸው:: ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው እነዚህ ሶስቱ ናቸው::

ታዲያ ጠቅላላ ጉባዔውስ የሚለው ጥያቄ ይቀጥላል::ጠቅላላ ጉባዔውም እነዚሁ ሶስት ጓዶች ናቸው::እርግጥ እንደማህበሩ ሕግ ከሆነ ጠቅላላ ጉባዔ ሲባል የነዚህ ማህበራት የመጽሔት ቦርድ አባሎች አሉበት::ግን የመጽሔት ቦርድ አባሎች ድምጽ የመስጠት መብት የላቸውም:: ስለዚህ ከኛ 'ከተራ' ተመልካቾች የሚለዩበት ፈሊጥ የለም::ለዚያውም እንኳን የመጽሔት ቦርድ ኖሮት ይዞ ሊመጣ ይቀርና ከኢራቅ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የመጣው ጓድ ሰደ'በአልጄሪያ ያሉት ሁለት ጓዶች ብቻ ናቸው:: ማስረጃ ሳቅርብ እያለ ይወጡታል::ሱዳንም የመጽሔት ቦርድ ከለው ይዞ መጥቶ አላየንም:: ይህ ቀርቶ እንኳ'ብዙሃኑን የሚያቅፈውን የሱዳን ማህበር አወከላለሁ'የሚለው ጓድ ኃይሉ ገርባ 'በሱዳን ስም በዚህ ጉባዔ ላይ የሚሳተፈው መምህር ፍስሀ የሚወክለው 7 ሰው ብቻ ነው'እ ባለጉባዔዎቹ እንዳይናገር ቢከለክሉትም ለመቃወም ይሞክራል::ይህንን ዝቅ ብለን እንመለስበታለን:: እዚህ ግን 'ይሁን'ብለን በአልጄሪያ ማህበር አለ፤ መምህር ፍስሀም ብዙሀንን ይወክላል ብንል እንኳን ካውንስሉና ጠቅላላ ጉባዔው የሚለዩበት ነገር የለም::

ታዲያ ምንድነው የዚህ ካውንስል ትርጉም? ግልጽ ነው::'ሰው ፊት'ሊወሰዱ ለማይችሉ 'ሰው ፊት'አጥጋቢ መከራከሪያ ሊገኝላቸው ለማይችሉ ፀረ—ዲሞክራቲክ ውሳኔዎችና ድርጊቶች መሸፈኛ ጓዳ ነው::ቀላል ምሳሌ:: ከሱዳን ብዙሃኑን አወከላለሁ ማስረጃ ሳቅርብ ያለው ጓድ ኃይሉ በጠቅላላው ጉባዔ ላይ በሱዳን ስም አትናገርም ተባለ:: ለምን ሲባል 'ካውንስሉ'ነገሩን አጥንቶ ብዙሃኑን የሚወክለው ጓድ ፍስሀ መሆኑን ተረድቶታል ተባለ::የኢራቅም ጓድ ሰደ በቅርብ ምስራቅና



በሰሜን አፍሪካ መህበር ስም አትናገርም ተባለ::ለምን ቢባል 'ካውንስሉ'እንዳመሉ ነገሩን አጥንቶ በአካባቢው ብዙሃኑን የሚወክለው ጓድ እያሱና ጓድ ፍስሀ ከካይሮ ጋር ሆነው ያቋቋሙት ማህበር ነው ተባለ::

ነገሩ እንግዲህ የሚያዝ የሚለቀቅ የሚጠፋው እዚህ ፈላጭ ቆራጭ 'ካውንስል'ውስጥ 'ማጆሪቲ'ሆነው የሚፈልጡትና የሚቆርጡት እነዚሁ የአልጄሪያና የሱዳን ወኪሎች ሆነው ሲገኙ ነው በተለይ በቅርብ ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አባልነት ጉዳይ ሲነሳ ትርኢት ታየ::ፌዴሬሽኑ ውስጥ ሆነው አስተናጋጆችና ተቀባዮች፤ ከፌዴሬሽኑም ውጭ ሆነው 'አስገቡን'ብለው ማመልከቻ አቀራቢዎች እነዚሁ አልጄሪያና ሱዳን ሆኑ:: እርግጥ ከውጭ ሆነው 'አንገባ'ብለው 'በማጆሪቲ'ቢወስኑ የካይሮ ማህበር አብሮአቸው አለ::በወዲህ በኩል ከፌዴሬሽኑ ውስጥ ሆነው ደግሞ 'አዲስ'አመልካቾችን እንቀበል ሲሉ ደግሞ ቢወዱ ተስማምቶ በይወዱ 'ማይኖሪቲ'ሆኖ ተቀባይ ኢዙና አለ:: ሁለቱም ጋ 'ማጆሪቲ'አልጄሪያና 'ሱዳን'ናቸው::

እንግዲህ ይህ በአንድ አገሩ የቆመ የፌዴሬሽኑ ሕገማህበር ዲሞክራሲ ትራጀዲና ኮመዲ የተደበላለቀበት ነው::ምክንያቱም 'አሉ፤የሉም' እስከመናገራቸው ሰው የሚወረረዱባቸው ስድስት መቶ አባላት ካሉት ከኢዙና ጋር እኩል አንድ ድምጽ ይሰጣቸውና እነሱ 'ማጆሪቲ'ኢዙና'ማይኖሪቲ' ሆነው ውሳኔ ማሳለፍ ይችላሉ::

ለማንኛውም ፕሬዚዳንቷ አጭር የመክፈቻ ንግግር አደረገችና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የተላኩ የድጋፍ መልዕክቶች ተነበቡ::በማህበራችንም ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የቀረበ ረዘም ያለ ያቋም መግለጫ መልዕክት በጓድ አማረ ተገባሩ ተነበበ:: በአውሮፓ ማህበር የመጽሔት ቦርድ ስም ያቋም መግለጫ መልዕክት ሳቅርብ ብሎ ጓድ ደረጀ ዓለማየሁ ጠየቀ::የጓድ አማረን መልዕክትና አፍረጥርጦ ያቀረባቸውን የማህበራችንን ችግሮች ጉባዔው አቀህዶ አልጠረሰቸውም ነበር::ስለዚህ የጓድ አማረ ሰያንስ ጓድ ደረጀ አይጠምርበትም ብሎ ተከለከለ:: ግን ጉድ የለም:: ይህ በሽሽት የሚመሰቀበት ጉዳይ አይደለም:: እኛ እንደሆንን ለበሬው ተማሪ ድምጻችንን ከማሰማት የሚያግደን ነገር የለም::የጓድ አማረን ንግግር 'በሁለተኛው የዓለም ዐቀፍ ፌዴሬሽን ጉባዔ ላይ የተነበበ' መልዕክት ብለን አናትመዋለን:: የጓድ ደረጀን ደግሞ 'እንዳይነበብ የተከለከለው መልዕክት'ብለን አናወጣዋለን:: እንዲያውም ይህ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ሥራ በጉባዔው ላይ ለተፈጸሙት መዐት ፀረ— ዲሞክራቲክ የሽሽት ድርጊቶች አንደአንድ ቋሚ መረጃ ሆኖ ይቀርባል::

መልዕክቶቹ እንዳለቁ ሊቀመንበር ይመረጥ ተባለ::የአውሮፓ ማህበር ዴሌጌሽን 'አባላት እነማን ናቸው?'የሚል ጥያቄ አቀረበ:: ጓዲት አበበች 'የፌዴሬሽን አባላት ኢዙና፤ሱዳንና አልጄሪያ ናቸው'ብላ ደመደመች::ዓመቱን በሙሉ 'አውሮፓ የፌዴሬሽኑ አባል ነው'ይባል የነበረው ድርቅና ቀርቷል::በየመግለጫው 'ብኄራዊው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የፌዴሬሽኑ አባል ነው' የሚለው በረ ወለደ አነጋገር ተትቷል::ከአገር ቤት የመጡት ጓዶች በአባልነት ባ ይሆን በተመልካችነት ተገኝተዋልና:: በአቋም መግለጫ መልዕክታችን ላይ 'ዛሬ የዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን የሚባለው የኢዙና ሌላ መጠሪያ ስም ነው' ያልነው ሌላም ብዙ ማረጋገጫ አላስፈለገው:: በገዛ ፕሬዚዳንቷ አቀራረብ ፌዴሬሽኑ የተራቆተባቸው ተመልካቾች 'ምነው ጠምሪበት

እንዲሰማለት የሚያጣው አነጋገር አመጡ፡፡ የቤቶች ወኪል ነኝ ብላ በጉባዔው አካባቢ ወደተቀመጠቹው ወደጓዲት አበባ እያመለከተ ተይ እንዴ ይሏት ጀመር፡፡ ጓዲት አበበችም ትክክል መናገሯ ገባትና ደንገጧእንደገና ነገሯን ማስተካከል ጀመረች፡፡ እያን አባላት አራት ናቸው፡፡ ቤቶችም አሉበት፡፡ ግን ድምጽ የላቸውም፡፡

በኛ ዲሌጌሽን በኩል ጥያቄውና ውካታው ይጐርፍ ጀመር፡፡ ድምጽ የሌለው አባል ምን ማለት ነው? ሕገ ማህበሩ የት ላይ ነው እንዲህ ዓይነት አባልነት የሚፈቅደው? በአውሮፓ የቤቶች የጥናት ክበብ የፌዴሬሽኑ አባል አይደለንም ብሎ ያበሳሰፈው ውሳኔ የት ደረሰ? የሚሉ ጥያቄዎች፣ ሥነሥርዐት ተቃውሞ የሚለው ጩኸት በዛ፡፡ የአውሮፓ የቤቶች የጥናት ክበብ ወኪሎች መገለጫ እንስጥ ይላሉ፡፡ እነጓድ ኃይሉ መምህር ፍስሀ ቡዳንን አይወክልም፣ መገለጫ እንስጥ ይላሉ፡፡ ጓድ ባደ አልጄሪያ ማህበር የሰም ማስረጃ ሳቀርብ እያለ ይወተውታል፡፡ በውካታውም መሃል ጓዲት አበበች ቃላት ያለቀበት ትመስላለች፡፡ አይሆንም አልቀበልም ብቻ ነው የምትለው፡፡ በኋላ ግን እንደምንም ብላ እነዚህ ጓዶች ከፊሉን በግለሰብ ደረጃ ሲናገሩ ይችላሉ፡፡ አለበለዚያ ግን ከውንስሉ ከጉባዔው እንዲወጡ ወስኗል፡፡ ብላ አስታወቀች፡፡ ጓድ አማረና የመጽሔት ቦርዱ ጓድ ተስፋዬ 'ስነስርዐት' 'ጥያቄ' እያሉ ይጮሃሉ፡፡ ጓዲት አበበች አሁንም መልሷ 'አልቀበልም' የሚለውን ፈሊጧን ስትጀምር ሰው ሁሉ 'ይመዝገብልን' ይል ጀመር፡፡ እኛም የቻልነውን መዘገብን፡፡

ከዚያም 'አሁን ወደምርጫ እንሂድ' ተባለ፡፡ ምርጫው ተደረገና ሶስት ሁነኛ ጓዶች ተመረጡ፡፡ በሙሉ ድምጽና በጭብጨባ ጓድ አብቶል ሊቀመንበር ጓድ ዘነበና ጓድ ሠረቀ ጸሃፊዎች ናችሁ ተባሉ፡፡ የጠዋቱ ስብሰባ በዚህ ላይ አከተመ፡፡

ፌዴሬሽኑ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ማህበራችን የፖለቲካ መስመሩን ከማጋለጥ የቦዘነበት ጊዜ የለም፡፡ አብዛኛውን ተማሪ የማይወክል ፀረ—ዴሞክራቲክ ድርጅት መሆኑን አውቆ ቢታገለው እስከዚህ ጉባዔ ድረስ መጥቷል፡፡ የፌዴሬሽኑንም ባለሥልጣኖች 'የአንደልቡ' አሰራርም ስለምናውቀ ይህ ጉባዔ ከተጀመረ እንስቶ እስከተፈጸመ በየነው ፀረ—ዴሞክራቲክ ድርጊት አንዱም አልተደነቀንም፡፡ ታዲያ ይህን ሁሉ በቅድሚያ ካወቅን እዚህ ጉባዔ ላይ ስንገኝ ምን ዓይነት አላማ ይዘን ነው? ለዚህስ ዓላማችን እንዴት ታገልን?

ከመጀመሪያውኑ በዚህ ጉባዔ ላይ በቁም ነገርና የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄ በሚመለከቱ ችግሮች ላይ መወያየታችን የሚያጠራጥር ነበር፡፡ በአጀንዳው ላይ ድምጽ መስጠት 'አይፈቀድልንም' የሚል ፍራቻ ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ ሃሳባችንን አብረርተን እንዳንገልጽ 'የሚያቋርጠን' ይበዛል የሚል ስጋት ነበረን፡፡ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ዛሬ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ላይ ስለሚወዱት አደጊዎች እንዳይወያዩ ሳብልጭልጭ ውሳኔዎች ያላቸው ዝንባሌ ያሸንፋቸዋል ብለን ፈርተን ነበር፡፡ ስለትብብራችንና ስለአንድነታችን እንዳንነጋገር ጉባዔያቸው ይሸሻል ብለን ገምተን ነበር፡፡ በኋላ ይህ ሁሉ ልክ ሆኖ አገኘነው፡፡ ግን በቅድሚያ አስፈላጊውን አርምጃ ወስደን ነበር፡፡ በበኩላችን የምናቀርበውን፣ ስለሶስት የፖለቲካ ልዩነቶች፣ ስለሶስት የድርጅት ችግሮች፣



እኛ ስለምናቀርባቸው መፍትሔዎች አጠቃለን በመጀመሪያ ው አጋጣሚ አፍረጥርጠን እንናገር ብለን ነበር፡፡ ስለዚህም በጉባዔው መክፈቻ ላይ ልዩ ልዩ ድርጅቶች የድጋፍ መልዕክት ሲያሰሙ ተራ ጠብቀን ገባንና ተናገርን፡፡

የፖለቲካ ልዩነቶቻችንን በሚመለከተው በኩል በኛና በኢሠዩና መሃል ባሉት ልዩነቶች አንስተን ከነታሪካዊ አመጣጣቸው ተነተንን፡፡ በተለይ በ14ኛው ጉባዔያችን ላይ በተወሰኑት ሬቮሉሽናዊ አቋሞች ላይ እየተመረኮዝን የተጣራ አስተሳሰባችንን አቀረብን፡፡ አምናም 'አሁኑኑ ሕዝባዊ ጦርነት' ሲሉ ዘንድሮም 'አሁኑኑ ሕዝባዊ ምርጫ' ሲሉ ከነሱ ጋር የሚያጋጠን ይኸው ለነጻነቱ ትግል የሌለ አቋራጭ አፈልጋለሁ እያለ በተበደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያላግጠው ወላዋይ አቋማቸው መሆኑን ነገርናቸው፡፡ ግን እንደዚህ አቋራጭ የሚያስፈልጋቸው፣ ሃይ ሃይ የሚወዳላቸው፣ 'ረዥም ጉዞ' ቢባል ትሬዔ የሚያስመዘዛቸው ያው የነውስ ከበርቴ ቀንጥንጥነት ነው ብለን በመደብ ላይ የተመረኮዘ ሳይንሳዊ ትንተና ብናቀርብ የሰደብናቸው መሰላቸው፡፡

የድርጅት ችግሮችን በሚመለከተው በኩል ደግሞ በዚሁ ያቋም መግለጫችን 'በሽታውን የሸሸገ መድሃኒት አይገኝለትም' ከሚለው እውነት ተነሳን፡፡ ስለዚህም ለውይይታችን መንደርደሪያ እንዲሆን በማሰብ የፌዴሬሽኑን ጠቅላላ ክስረት ማሳየት አስፈላጊ ሆኖ አገኘነው፡፡ ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ከነሱው ጋር በቅን መንፈስበመወያየት መፍትሔ መፈለግ ሬቮሉሽናዊ ግዴታችን መሰለ ስለዚህ ነገሩን ሁሉ ፍርጥርጥ አድርገን 'ፌዴሬሽን ማለት የኢሠዩና ሌላ መጠሪያ ስም ነው፡፡ ሌላ ትርጉም የለውም' አልናቸው፡፡ ይህም እንዴት እንደሆነ አንድ በአንድ አስረዳናቸው፡፡ ግን ይህ መከራችን የተጨበጡ እውነት ነፀብራቅ ሳይሆን ከኛ በኩል ፌዴሬሽኑን ለማራቆት ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ 'የፊውዳል ሴራ' መሰላቸው፡፡ ፌዴሬሽኑ አሁን ባለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊወክል አይችልም አልን፡፡ ይህን ደግሞ 'በመላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ስም' 'ከመቶ አርብ፡ድርጅቶች' ጋር እናደርጋለን የሚሉትን ግንኙነት ልናስናክልባቸው የወሰድነው የማጋለጥ ተግባር አደረጉት፡፡ በቅርብ ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ ማህበራት መካከል ስላለው ችግር ተወያይተን ሁሉም የፌዴሬሽኑ አባል መሆን ይቻሉ አልን፡፡ ይህ ደግሞ በፌዴሬሽኑ ውስጥ 'የአውሮፓን ማህበር ደጋፊዎች ለማብዛት የሚሞከር— ጓድ ንጉሤ እንዳለው — የቡጦር ፓወር ፖለቲካ መሰሰብንና ቀጥ አለ፡፡

ስላሉት ችግሮች መፍትሔ በሚመለከተው በኩል በዚሁ ባቋም መግለጫችን ላይ በአጠቃላይ አቀረብን፡፡ ነገር ግን እኛ ብቻችንን መፍትሔ ለማግኘት አንችልምና በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት እንዲደረግ ያለንን ፍላጎት ገለጽን፡፡ ይህንንም ውይይት ያስችላል ብለን ይዘን የሄድነውን አጀንዳ አቀረብን፡፡ ዝቅ ብለን እንደምናስበው በዚህ በኛ አጀንዳ ቢሄድ በብዙዎቹ ችግሮቻችን ላይ መወያየት ይቻል ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎችም አንድነት ከዚህ ውይይት ተጠናክሮ እንደሚወጣ እነሱም አላጡትም፡፡ ግን ደግሞ ይህ ከሆነ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች በብዙ ፀረ—ዴሞክራቲክ ድርጊቶቻችን እንጋለጣለን የሚል ተገቢ ፍርሃት አደረባቸው፡፡ ነገር ግን ከዚህ አጀንዳ ሸሽተው ሊያመልጡ አልቻሉም፡፡ የቅማል ስደት ከራስ ወዳንገት ይባላል፡፡ የኛን አጀንዳ

ተከትለው ከሄዱና በቂም ነገር ላይ ከተከራከሩ እንጋለጣለን ብለው የሰጉት ሰዎች ከቁም ነገር ሲሸሹ የሸሰውን ይጋለጡ ጀመር:: አሁን ወደአጀንዳቸውና ወደአጀንዳችን እንገባ::

1:— <u>የሸሸት አጀንዳ ወይስ የውይይት አጀንዳ?</u>

የፌደሬሽኑ ጊዶች ከተጠበቁ ሁኔታ ተነስተው ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች መወያየት እንደ ማይፈልጉ ካቀረቡት አጀንዳ ግልጽ ሆነ::እኛ ያቀረብነውን አጀንዳ እንኳን ሊቀበሉት ይቅርና 'እንቀበለው አንቀበለው'ብለው መከራከር አራቡ ብዙ 'አስፋሪ' ጥያቄዎች ውስጥ ጉትቶ እንደሚያ ስገባቸው ታያቸው::ስለዚህ በዚህ በኛ አጀንዳ ላይ ክርክር ለመክፈት እንኳ አልፈለጉም::'እና ንተ ያቀረባችሁት አጀንዳ በዚህ በዚህ ምክንያት አይስማማንም:: እኛ ያቀረብነው አጀንዳ በዚህ በዚህ ምክንያት ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነትና እድገት ለመወያየት ያስችለናል::' ብሎ መከ ራከር ያባት ነው::ዝም ብለው 'አንቀበልም' አሉን::

ለምንድን ነው የማትቀበሉት? ብለን ጠየቅን::እዚህ ላይ ያልፄሪያው ጊዱ ገዛሽኝ በጥ ልቀቱ ታዛቢን ሁሉ የማረከውን የማያሳውስ ምክንያት ሰጠ:: 'አንቀበለውም፣ ምክንያቱም ይህ የናንተ አጀንዳ ሌሳ አጀንዳ ነው::'

እንዴ ሌሳ በመሆኑማ ነው ሌላ አጀንዳ አለን ብለን ያቀረብነው:: ይህንን ማን አጣው? እኛም ለሥራችን የተሻለ ለችግራችን መፍትሄ መፈለጊያ የሚሆነን አጀንዳ ስለሚመስለን ነው እስቲ እንወያይበት ብለን ይዘን የመጣነው::'በሜል መንፈስ የአውሮፓው ወገን ለመከራከር ሞከረ:: ገን አሁንም ያው ጊዱ ገዛሽኝ ረሳጭ ቆራጭ ውሳኔ ውስጥ ገብቶ መሸገ::'ይህ የፌዴሬሽን ጉባዔ ነው:: እናንተ ተመልካች ናችሁ' አለን:: የኢዙናው ጊዱ በቀለ ነገሬን ይበልጥ አፍረጥርጦ 'ማህበርተኖች አይደላችሁም:: ተመልካቾች ናችሁ፣ አሁን በእኩልነት ደረጃ አስብ አለን ተቀበ ሉን ልትሉ አትችሉም'ብሉ አስረዳን::

ይህንንስ ቢሆን መቼ አጣነው? እናንተስ እስክትነግሩን መች ጠበቅን? ገና አቷም መገ ለጫ መልዕክታችንን ስንጀምር 'ውዱ ጊዶች ዛሬ ይህ <u>ጉባዔያችሁ</u> ...' ብለን አይደል እንዴ የጀ መር ነው? ገን ይህንኑ መገለጫችንን ከመዝጋታችን በፊት ምናልባት ለኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል አንድነት ትንሽ ስሜት ቢኖራችሁ ብለን 'ይህ <u>ጉባዔያችሁ</u> እውነተኛ አንድነታችን የሚመሰረትበት <u>የሁላችንም</u> ጉባዔ እንዲሆን' በአባሎቻችን ስም ጥሪ አቀረብንላችሁ::አመጣጣችንማ በተመልካች ነት ጀምረን ወደሙሉ ተሳታፊነት ለመዘወርና የኢትዮጵያ ተማሪዎችን አንድነት ባዲስ መንፈስ ወደፊት ለማራመድ ነበር:: ስላዓመቱ ክብብራችን፣ ስለወደፊቱ አጣዳፊ ተግባሮቻችን ተጠባጭ ውሳ ኔዎችን ይዘን ለመሄድ ነበር::ይህ ሁሉ ባቀረብነው አጀንዳ ላይ ይታያል:: እናንተ ገን አሁ ንም የነውስ ከበርቴ ዶንፉታችሁ አሸነፋችሁ:: ገና ውይይት ከመጀመሩ ከተመልካችነት ወደተወገ ዥነት ልታወርዱን ትጥሩ ጀመር::

የሆነ ሆኖ ሊቀመንበሩ በኢንፎርሜሽን መልክ እንድናስመዘግበው 'ስለፈቀደልን' አስመ ዝገበናልና አንባቢ ያነጻጽረው ዘንድ የፌዴሬሽኑን አጀንዳና 'ሌላውን አጀንዳ' እናስፍርለት::

የፌዴሬሽኑ አጀንዳ ስምንት ነጥቦችን የያዘ ነበር:: እነሱም: 1— የጸ. ቤት ሪፖርር 2— የየከቲት አንቀስቃሴ 3— የተማሪ ሚና 4— የአለም ዐቀፍ ሕገማህበር: ማሸሸያና አባሳት: 5— ረሃቡና ተግባራችን 6— በኢትዮጵያ ስላሉት ዱርጅቶች የሚኖረን አቋም 7— አዲሱ



ጽህፈት ቤትና የመጽሔት ቦርዱ ምርጫ 8— የፕረዚዳንሸል ካውንስል ስብሰባ

'ሌላኛው'አጀንዳ ደግሞ ስድስት ነጥቦችን የያዘ ነበር:: 1— ስለጉባዔው አካሄዱ በመጀመሪያ መጣራት ያለባቸው ነገሮች —ሀ— የዱምጽ አሰጣጥ ጉዳይ —ለ— በአሁኑ ወቅት በኢት ዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ያሉት ቅራኔዎች:— መካከለኛው ምስራቅና አፍሪካ፣ ሱዳንና የሴቶች የጥናት ክበብ ጉዳይ —ሐ— የችግሮቹ መፍትሄ 2— የጽህፈት ቤቱ ሪፖርር 3— የኢትዮጵያ ተማ ሪዎች ዱርጅታዊ አንድነት የሚጠነከርበት ዘዴ 4— ሁሉን የሚያቅፍ ሕግ ማህበር ስለማቅረብና ስለማጽደቅ 5— ሕገ ማህበሩ በጠቅላላ ጉባዔያችን እስኪፀዱቅ ዱረስ የአመራር ጥያቄና የሥራ ክብብር 6— የየካቲቱ እንቅስቃሴና ቀተማሪ ሚና እንዲሁም 7— ስለረሀቡና ተገባራችን

በገልጽ እንደሚታየው የፌዴሬሽኑ አጀንዳ ብዙ ነገር ሲያስቾውስ በንቀናቴያችን ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች፣ ዱርጅታዊ አንድነታችን የሚጠነከርበትን ዘዴ፣ በመጭው ዓመት ስለሚኖረን የሥራ ክብብር፣ ባጭሩ የትግል አንድነታችንን የሚመለከቱትን ነጥቦች 'ረስሁቀቸው'ብሉ አልፏ ቸዋል:: አውቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማምና አውቆ የረሳቸውን ነጥቦች ብንጠቁም ሊያስታውሳቸው አልፈለገም:: ይህንን ፀረ—ዴሞክራቲክና ፀረ—አንድነት ሕገ ማህበር የማሸሸሉንም ጉዳይ 'አለ መርሳታቸው' ተመስገን ነው::

ለማንኛውም በዚህ አጀንዳቸው ላይ እንደሚታየው የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች 'አለም ዐቀፍ ፌዴሬሽን'የምትለዋን <u>ስም ከያዙና</u> አመራሯን ካፏ ተነጠቁ — አገር ቤት ይገባ ሲባል አምቢ ብለዋል— የቀረው ተማሪ ቢደባለቅ ባይደባለቅ ፣ በተማሪዎች መሃል ያለው ቅራኔ ቢፈታ ባይፈታ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዱርጅታዊ አንድነት ቢገኝ ባይገኝ፣ ከማህበራችን ጋር ቢተባበሩ ባይተባበሩ ፈጽሞ ዴንታ እንደሌላቸው አሳዩን::

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ እዚህ ጉባዔ ላይ ምንም ዓይነት ቁም ነገር እንደማይሰራ ግልጽ ሆነ:: የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖቹ ብቻቸውን የጀመሩት ጉባዔያቸው እስከመጠረሻው የአንድ ነታችን መመስረቻ የሁሉችንም ጉባዔ እንደማይሆን ተረዳነው:: እንደአያያዛቸው ከሆነ ጉባዔው ውስጥ ከሚደረጉት ውይይቶች ይልቅ ከጉባዔው ውጪ እየተብለጠለጩ ለሚያቦሩትና 'በማጆሪቲ' አያሳፉ 'ለታሪክና'ለፕሮፓጋንዳ የሚወረወሩት 'ውሳኔዎች'ቀዳሚያ ይሰጣቸዋል ብለን ገመትን::' እነዚህም 'ታሪካዊ ውሳኔዎች' ብልጭልጭና 'ቦምባስቲክ'እንደሚሆኑ ለመገመት ጠንቋይ መቀለብ አላስፈለገንም:: ለምን?

ቀላል ነው::ብዙ የሚጋለጥ ጉዱ ያለበት ሰው እንዳይጋለጥ ከፈለገ ብዙ ሽፋን ያስፈልገዋል:: ለፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች የፖለቲካ ከስረታቸውን 14ኛው የማህበራችን ጉባዔ አሳይቶባቸዋል:: የዱርጅት መረቆታቸውም ዐመት ሙሉ ሲከፉ ቆይተው እዚሁ ጉባዔያቸው ላይ የአውሮፓና የአገሬ ቤቱ ማህበር ወኪሎች በአባልነት ሳይሆን በተመልካችነት ደረጃ ቁጭ ብለ ውባቸዋል:: ለዚያውም ደግሞ 'ጉባዔ'ብለው ከተቀመጡት ስስት ሰዎች <u>ሁለቱ</u>'አትወክሉም'ሲባሉ '<u>ማስረጃ አይቀርብብንም</u>'ብለው ነው መሽገው ቁጭ ያሉት:: እንግዲህ ይህን ጥልቀት ያለው ኪሳራ ለመሸፈን ከተነሱ ብዙ 'ሃይ ሃይ' ብዙ 'ጉሳ ጉሳ'የሚሉ ውሳኔዎች እንደሚያስፈልጋቸው

ለማንም ገልጾ ነበር:: ስለዚህ ቁም ነገር የያዘ ውይይት አይኖርም በማለት በተመልካችነት መደሳደል የጀመረው ማህበራችን ወደ ተወጋዥነት ሲንሸራተት ይታየን ጀመር::

በውነቱ በዚህ ጉባዔ ላይ በማህበራችን ላይ የወረዱት 'ፋሺስቶች' 'የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች' የሚሉት ስድቦችና ማህበራችንን በማውገዝ የተላለፉት መዐት የፕሮፓጋንዳ ውሳኔዎች በኛ በኩል ከመጤፍም አልተቆጠሩም:: በተቻለ ፍጥነት ቶሎ ቶሎ አውግዘውን ቢያንስ ቢያንስ ወደ ሕገማህበሩ ውይይት እንዲገቡ ደጋግመን እናስገነዝብ ነበር:: መወገዛችን ስሜት እንዳልሰጠን አይቶ ያሜሪካው ጓዱ ያፌት 'መወገዝ እንደኪኒን ይስማማቸዋል' አለ:: ነቀታችንን አይቶ ያሜሪካው ጓዱ በቀለ 'ምን ሆናችሁ? መወገዝ እኮ ታሪካዊ ትርጉም ያለው ነገር ነው' እያለ 'ደንግጡ እንጂ ሊለን ትንሽ ቀረው:: ግን ጓዱ በቀለ የገዛ ውሳኔዎችን 'ታሪካዊ' እያለ ቢመጻደቅ ቆዳ ማቀደዱ ነው እንጂ ከኛ በኩል በዚህ ማስፈራሪያ የተፈታ የለም :: የቦስቶ ስዎች 'ጉባዔ' የሚያሰልፉበን የማውገዝ ውሳኔ ቢኖኃጋ ልር 'እየሰደደ የሚሄደውን የማህበራችን ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር ከተማሪ ንቅናቄ ሊነቀል እንደማይችል፣ የነሱንም የከሰረ መስመር ሊያድን እንደማይችል አልተሳተንም::

የሆነ ሆኖ ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነትና በጠቀሳሳው ስለነጻነት ትግሳችን ለነገሩ መወያየት ስንጀምር መለያየታችን ታየንና አዘንን:: ግን ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንደዚህ የሚያሳገሙት ነውስ ከበርቴዎች አሁን ቢደነፉም ዘር ዘር መጋለጣቸው አይቀርም፣ ትግሉንም ሊያደናቅፉት አይችሉም የሚለው ዕምነት ሳንዲት ስኩንዱ እንኳ አልተለየንም ነበር:: ስለዚህም በአዱሃሪ ፓርሳሜንቶች መሬረብ ላይ ተረማጆች ሃሳባቸውን እንደሚያስፋፉት እኛም <u>በዚህ በፀረ— አንድነት ጉባዔያቸው ላይ ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት አስከመጨረሻው ለመታገል ወሰንን</u>::

እንግዲህ በዚህ ፀረ—ዲሞክራቲክና ፀረ— አንድነት አካባቢ የኛም 'ሌላኛው' አጀንዳ እንዳልነበረ ተረስቶ ቀረ:: ለፍርማሊቲ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ የነሱ አጀንዳ ይጽደቅ ተባለ:: ጓዱ ገዛኸኝ 'ይጽደቅ ብለናል' አለ:: በዚህም ትላንት ካውንስል ሆነው ያጸደቁትን አጀንዳ ሶስቱ ጓዶች ዛሬ ደግሞ ጠቅላላ ጉባዔ ናቸው ተብለው በድጋሚ አጸደቁትና በአጀንዳቸው መሰረት የአመቱ የስራ ሪፖርት በፕሬዚዳንቷ በጓዲት አበበች ቀረበ::

## 2— <u>የጽህፈት ቤቱ ሪፖርት</u>

የዓመቱ የሥራ ሪፖርት ረዢም ነው:: ብዙ ቁም ነገሮችንም አዝሏል:: ብዙ የተፈጸሙ ዱርጊቶችንም ይዘረዝራል:: ብዙም የሚያከራክሩ ነጥቦች አሉበት:: ግን ለምን እንደቀረበ አልገባንም:: በዚህ በኩል ደግሞ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ያላቸውን ፍልስፍና ገና ስላሳብራሩልን ትንሽ ገር አለን:: ለወትሮው የሥራ ሪፖርት ሲባል ለምንድን ነው የሚቀርበው?

ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ባለፈው ጠቅላላ ጉባዔ ስለተሰጡት አደራዎች፣ ከነሱም የተፈጸሙትንና ያልተፈጸሙትን፣ አዳዲስ የተወጠኑ ወይም የተሰሩ ሥራዎችን ፣ በዓመቱ ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች ወዘተ... እየተጠቀሱ በሪፖርቱ ይዘረዘራሉ:: አደራ የተጣለበት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ዓመቱ ውስጥ በሰራው ተመስገኖ በጉደለው ሂስ ተደርጉበት በኋላም ባጠቃላይ ሚዛኑ ታይቶ



ዱምጽ የሚሰጥበት ዲሞክራቲክ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ነው:: ይህንን እዚያው በርሊን ከ15 ቀናት በፊት በአውሮፓ መህበር ጠቅላላ ጉባዔ ላይ አይተናል:: ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴያችን በዓመቱ ውስጥ የነበረውን ፕላን፣ የተከተለውን ፖሊሲ፣ የፈጸማቸውን ድርጊቶች፣ ያጋጠሙትን ችግሮችና እንቅፋቶች በዝርዝር አቀረበ:: የአመቱ ሥራዎች ባጠቃላይ ሲመዘኑ በተለይ በረሀቡ ጉዳይ ላይ ጉድለት ስለታየበት ተወቀሰ:: ተቀበለው:: በዓመቱ ውስጥ የሥራ እንቅፋቶች ናቸው ብሎ ካቀረበው ውስጥ የዚሁፌዴ ሬሽን ባለሥልጣኖች የሚጠቀሙበት የትግል ዘዴ ስለነበር ጉባዔው ሥራቸው እውነትም የአንድነት ጠር መሆኑን ተረድቶ አወገዛቸው:: የከሰረ ዘይቤያቸውንም እንዲለውጡ በኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል አንድነት ስም ጥሪ አደረገላቸው:: በመጽሔት ቦርዳችንም በኩል በቀረበው ሪፖርት ላይ በአጠቃላይ ሥራው አጥጋቢ ሆኖ ሳለ ከህገወጡ 'ኢታና' ጋር የሕጋዊውን ኢታና ስም በመጠቀም ስላደረገው የደብዳቤ ግንኙነት ገለሂሱን አቀረበ ጉባዔያችንም የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት በዚህ አለመገባባት ተፈጥሮ እንዳይሸከር በማሰብ ለኢታና ጓዶች የይቅርታ ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ወሰነ:: ይህ ነው ዲሞክራሲ ማለት:: በአፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር::

የፌዴሬሽኑ ጽ.ቤት ሪፖርት ግን ለየት ያለ ነበር:: ሪፖርቱን አንብባ ከመጨረሷ ጓዲት አበበች 'ካውንስሉ እንዲያፀድቅልን እንጠይቃለን' አለችና በቤቱ ውስጥ ጠቅላላ ውዥንብር ተነሳ:: ከአውሮፓ ወገን አንዱ ጓዱ 'ለምን ካውንስል ትያለሽ? ይህኮ ጠቅላላ ጉባዔ ነው' ብሎ ለማስተካከል ሞከረ:: ጓዲት አበበችም ትንሽ አመነታችና 'አዎ ትላንት ለካውንስሉ ቀርቦ ታርሟል:: ይህ ፋይናል ነው ካውንስሉ አጽድቆታል:: አሁን የቀረበው ለጉባዔው ነው' ብላ ተመልሳ ሳች:: ያው ጓዱ ይመልስና 'ትላንት ካውንስሉ ውስጥ አልቼሪያን፣ 'ሱዳንን'ና ኢታናን በመወከል እነዚሁ ሶስት ጓዶች ነበር የተሰተፉት :: ታዲያ በትላንትና በዛሬ መካከል ምን ...' ብሎ ሲጀምር ጓዱ አማረ ከጓዲቷ ነገር የታዘበው ጉዱ አሳስችልህ ብሎት ቀጠል አደረገና 'የጽ.ቤቱን ሪፖርት ካውንስሉ እንዴት አዱርጉ ሊያርም ይችላል?' የሚል ጥያቄ ዓብ አደረገ:: ቤቱ ውስጥ ሳቅ ውካታና ውዥንብር ብቻ ሆነ:: 'ካውንስሉ — ጠቅላላ ጉባዔው' — እንዳመጣባቸው የዚህን የፌዴሬሽኑን ከምስጢረ ሥላሴ የረቀቀ ዲሞክራቲክ 'ሚካኒክ' ለማብራራት መውደቅ መነሳት ጀመሩ::

በቀለ ከኢታና 'የቀረበው ለማስማት ነው:: ጸዱቋል ለማለት ይቻላል:: ይጽደቅልን የሚለው ጸዱቋል በሚለው ይለወጥ' ብሎ ስለዓመታዊ የሥራ ሪፖርት አዲሱን ፍልስፍና ለቤቱ ሲያበስር በአውሮፓም በፌዴሬሽኑም በኩል ሰው ተደናገጠ:: ማንም የሳቀ የለም:: በመሃሉ ጓዱ ገዛኸኝ 'ነገሩን እንነጋገርበታለን:: ነገር ግን ሪፖርቱ ጸዱቋል:: ጥያቄ ለማቅረብ ይቻላል' ሲል ፈቀደ::

የነገሩ አዝማሚያ ደስ ያላሰው ተመልካች ጓዱ ንጉሤ ነገሩን መልሶ ወደዲሞክራሲ ሊቀላብሰላቸው በመሞከር 'አጽድቀነዋል ብለዋል:: ግን እንኳ ከስ አለ ከተባለ ለውይይት መቀረብ አለበት:: ከስ ቀርቧል እንጂ ፈርደናል ማለት አይደለም::' ሲል የዚህን ጓዱ አነጋገር ሎጂክ ለመረዳት ከምንሞክረው መሃል ጓዱ ተዱሳ 'ክሥ ቀርቦ ውሳኔ ሰጪዎች ካጸደቁት በኋላ እንዴት ፍርዱ አልተሰጠም ይባላል?' ብሎ ጠየቀ:: ማንም ደፍሮ አብራራለሁ የሚል ጠፋ::

'ውይይቱ' በሌላ አቅጣጫ ቀጠለ::

ጓዱ አማረ:— ካውንስሉ ስሙን ቀይሮ ጉባዔ ሆኖ ቁጭ ብሏል:: የመጣል የማሰለፍ መብት ያለው እሱው ነው::

ጓዱ አያሌ:— ካውንስሉ አጽድቆታል:: እንዲታወቅ እዚህ ቀርቧል:: ጥያቄ ያለው ያቅርብ:: አውርጃ ከሌለው ይተወው::

ጓዱ ደረጀ:— እንዲያውነው የምንከራከረው:: ጓዲት አበበች 'ካውንስሉ እንዲያጸድቅልን እንጠይቃለን' አለች:: እንዱ ተነስቶ 'ተበስተሸል ጸዱቋል በይ' አሳት እንዲህ አይነት'ስህተት'ለታሪክ ነው :: ለማንኛውም ሪፖርቱ በንዲህ አይነት 'ጸደቀ':: ቀደም ብሎ ስለአጀንዳ በነበረው ሁይይት ላይም እንዲሁ ነበር:: ግና ውይይቱ አንዱ መልክ ሳይይዝ፣አጀንዳችን ምን ይደርስ ይሆን ብለን ስንጠብቅ ጓዱ ገዛኸኝ እንደዳበባ'ካውንስሉ ያቀረበውን አጀንዳ ተቀብለናል' ሲል ውሳኔ መተላለፉ ነው ተባልን:: ይህንን ሁሉ ስናይ በዚህ ጉባዔ በዚህ የአሰራር ዘዴ የሚኖረን መብት ቀረታችንን ማስመዝገብ ብቻ ነው::

ጓዱ አንዳርጋቸው :— ሪፖርቱን በስቱና አንዱ ተጠማሪ ዱምጽ የሌለው አባል አጽድቆታል ነው የተባለው?

ጓዲት አበበ:— ሪፖርቱን የሚያጸድቀውና የሚጥለው ካውንስሉ ነው:: የቀረበው ጠቅላላ ጉባዔው እንዲሰማው ነው:: ቀጥሎ ካለ ቢቀርብ ማስረጃ ይቀርባል:: ካውንስሉ ያቀረበው ሪፖርት አይደለም,,::

ጓዲቷ በዚህ ነገሯ ነገሩን የባሰ አምታታችው:: የፌዴሬሽኑን ሕገማህበር ይዘት ለፌዴሬሽኑ አባላት እየጠቀሱ ማስረዳት መቻል በኛ በኩል ተቀዳሚ ተግባራችን አለመሆኑን እናውቃለን:: ቢሆንም ይች ጓዱ የፌዴሬሽኑን ሕገማህበር አንቀጽ 14 እንደምንም ብላ ብትመለከተው ነገሩን እንዲህ አድርጋ 'ባላበራረችልንም' ነበር:: ስለዚህ ጓዲት አበባም ሆንሽ እነጓዱ በቀለ ሕገማህበራችሁን እንደምንም አንብቡት::

ከርከሩ በዚህ መልክ ቀጠለ:: በዚህ ሁኔታ ሪፖርቱ ምን ሊሆን በማን ለማን እንደቀረበ እንኳን ለኢዜና ጓዶች የፌዴሬሽኑን ሕገማህበር ጠንቀቀን ለምናውቀውም ዘረበን:: ውዥንብር በውዥንብር ላይ እየተጠመረ ነገሩ ጠርቦ ከቁጥጥር ሥር መውጣት ጀመረ:: ለጉባዔው መልክ ለመስጠት አሰብን:: ሌላ ሌላ ማብራሪያዎችን ጠይቆ ውይይት መክፈት ይሻላል አልን:: ጥያቄዎቻችንን ለማስመዝገብ አስፈቀዱንና ብዙ ጥያቄዎች አቀረብን:: በነሱ ላይ ውይይት ተጀመረ::

ገን ባቀረብናቸው ጥያቄዎች ላይ መልክ የያዘ ውይይትና ስለፌዴሬሽኑ የአሰራር ዘዴ የተብራራ ስዕል ለማግኘት አልተቻለም::ትንሽ እንደሄዱን የተስፋዬ ታደሰ ጉዳይ ተነሳ:: እኛም የሱ ጉዳይ ከተነሳ አይቀር እዚህ እንዲገባ ተፈቅዶለት በሚከሰስባቸው ነገሮች የሚጋለጥ ከሆነ እንዲጋለጥ፣ መልስ የሚሰጥ ከቻለ መልስ እንዲሰጥ፣ ማስረጃዎች ከሁሉም በኩል እየቀረቡ እንወያይ የሚል ሀሳብ አቀረብን:: 'መረጃዎች እየቀረቡ እንነጋገር'ያልነው አማርኛ ያልጣመው



ጓዱ በቀለ:'አሁንስ ነገሩ ያስቆ ጀመር:: ይህ ፊውዳል ፍርድ ቤት አይደለም::በኘርግረሲቭ ስታንዱ ነው የምንሄደው::' የሚል አነጋገር አመጣ::እኛም ይህንን እውነት እንደምናምንና ይህ 25ው የዓለም ዐቀፍ ፌዴሬሽን ጉባዔ እንደ የፊውዳል ፍርድ ቤት አለመሆኑን እንደምናቅ ገለጽን:: እንዲያውም መረጃ ማለታችን አንዱ ሰው ቢከሰስ ያለአንዳች መረጃ ስንኰንነው የምንለው ይህ ጉባዔ የፊውዳል ፍርድ ቤት ስለሊመስለን ነው አልናችው::

በቤቱ ውስጥ ሆነ ተብከው ወደ 'ሂስቴሪያ' የሚወከረው አየር ተፈጠረ:: ሌላው የኢዜና ጓዱ ያሬት ለምናልባቱ ድንፋታው የሚያስደነግጠው የሚቸል ሰው ይገኝ እንደሆነ በማለት 'ስላዩን ተስፋዬ ታደሰን ደግፈው የሚከራከሩ ሁሉ ስማቸውን እያስመዘገቡ እንዲናገሩ' ብሎ እንደ ብላክ ሜይል ቃጣው::

እዚህ ላይ የአገር ቤት ማህበር ወኪሎች እስካሁን በጉባዔው በዙ/ካዲካተፉም ተስፋዬ ታደሰን 'እንደናጋልጠው ተነግሮን መጥተናል' ብለው ሃሳባቸውን እንደሚከተለው አቀረቡ::

ጓዱ ጌታቸው በተናገረው መሰረት ተስፋዬ ታደሰ አገር ቤት በነበረበት ጊዜ 'ሪስተረር' ከሚባለው ሎዞዋን ከሚያረር ቡድን አባል ነበር::'ዣምር ማስተማር' የተባለው ፕሮግራም ውስጥ ሃላፊ ሆኖ ሲሰራ ገንዘብ አጉድሎ ለቤተሰቦች ቤት አሰርቷል:: የሰላም ጓዶች አስተማሪ ሆነ ተማሪዎችን ስጋይ እያደረገ ወሬ ያቀብል ነበር::ማራ ላርሰን የተባለቸውን የታወቀች የሲ.አይ.ኤ. ሰላይ ወሽማ ነበር::እርሷም የሲ.አይ.ኤ. ሰላይ ነው ብለን እናምናለን' የሚል ነበር::

በጓዱ እቦማ በኩል ደግሞ የቀረበው ተቀጢላ ከስ 'በሌባኖስ ሶስት ሰዎች እንደ ማህበር የለም::ኘሬዚዳንት የመምረጥ መብት የላቸውም:: እዚ ያሉት የፖለቲካ ንቃታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ጋጥ ይሰራና ተጠርተው ተስፋዬ እንተው ሁንለን ይሉታል:: ተስፋዬ ታደሰ ደመኛችን ነው:: ተስፋይ በሌባኖስ ማህበር ስም ለመጠቀም ሲል ጋራ ነገሮችን እንደሚሰራ እናውቃለን:: ተስፋዬን በአዜቶ ስም አንፋረደዋለን' የሚል ነበር::

በማስረጃዎቹም ጉዳይ በተነሳው ክርክር ጓዱ ጌታቸው ሲመልስ 'ፍርድ ቤት እንሄዳለን ብለን ማስረጃ ይዘን አልመጣንም::በተስፋዬ ታደሰ ጉዳይ ተነጋግረንበት የምናጋልጣትው ነገሮች ስላሉ እንዲናጋልጠው ተነግሮን መጥተናል:: ሪስተረር ሆነ ሊሻሻል ይችላል::ግን አልተሻሻለም::የሲኢይኤ ኤጀንት ሆኖ ይሰራል:: ከውጪም የሚመጣለን ወሬ ኢኪሽ ነው የሚል ነው:: አገር ስንመለስ ማስረጃዎች ሰብስበን እንልካለን::'አለ::

እንግዲህ በርጋታ መወያየት ቢቻል ኖሮ መዐት ጥያቄዎች ነበሩን:: የመጀመሪያው መቾስ አሁንም የመረጃ ጉዳይ ነው::እውነት ነው ፍርድ ቤት አይደለንም:: ግን ወደድንም ጠላንም በምንለውና በምንወስነው በአንዱ ሰው የፖለቲካ ህይወት ላይ እንፈርዳለን::አንዱ ሰው ሰላይ ነው ተብሎ ውሳኔ ይሰፍልኝ ማለት፣ አንዱ ሰው ሰላይ ነው ብሎ ደምጽ መስጠት

በዚህ ሰው የፖለቲካ ህይወት ላይ የሞት ፍርድ መፍረድ ማለት ነው::በኛ ግምት ይህ ትልቅ ሃላፊነት ነው::

14ኛው ጉባዔያችን ላይ በቂ ማስረጃ አልተገኘም ሲባል የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች 'ትንሽ ቆየ ጉባዔያችን ላይ መረጃዎች ይቀርባሉ' ሲሉ ነበር:: አሁን ደግሞ 'መረጃ ይዘን ስለመጣንም' ከተባለ ግድየለም እንጠብቃለን:: 'ይዘን ስለመጣንም' ሲባል 'መረጃ አለ' ማለት ነውና ተይዞ ያልተመጣው መረጃ እንዲላክልን አሁንም እንፈልጋለን:: በመረጃ እንፈርዳለን እንጂ አይናችንን ወፍ ነን አንነሳም::

ሌሎችም ወሳኝ ጥያቄዎች ነበሩን::"በዜጋ-ብ ተስፋዬ ታደሰ ጉዳይ ተነጋገሩን" ይላሉ ብዙዎ ጓዶች:: እነማን? የሉዞቁ ጠቅላላ ጉባዔ? ከነገሩሱ? ኘሬዚዳንቱና ጸሐፊው? ተስፋዬ ታደሰ ከሃገር ተሰዶ ከወጣ ከአራት ዐመታት ያለፈዋል:: ብዘው የሉዞቁ አባል ከነ መፈጠሩስ ያውቀው ይሆን? የሱስ ነገር መች በምን ሰበብ በምን መድረክ ላይ ቀርቦ ንግግር ተደረገበት?!ከውጭ የሚመጣልን ወሬ አሁንም ቪሺሻ ነው" ተባለ:: ከየት ከውጭ? ከአውሮፓ ማህበር? ከሌዞና? ከፌዴሬሽኑ?ከግለሰቦች?

ጓድ ጉታቸው እናንተ 'ከውጭ የሚመጣለን ወሬ ቪሺሻ ነው የሚል ነው'ብላችሁ ታወግዙታላችሁ::'ከውጭ'ደግሞ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ደግሞ 'የሃገር ቤት መልዕክተኞች ባሰረ ጉት መሰረተ'እያሉ ያወግዙታል:: ታዲያ ማነው ለማ ማስረጃ ያቀረበው? ስለዚህ ነው እኛም ይመጣሉ የሚባሉት መረጃዎች በዝርዝር ይሰጡንና በማህበራችን ይወገዝ እውነት ሰላይ ከሆነ የምንለው:: ይሌሎች ማህበራት አባሎች ተገንዝበውት እንደሆነ አናውቅም:: በኛ ግምት ግን ይህ እጅግ ጥብቅ ጉዳይ ነው:: ለዚህም ነው እዚህ ጽሑፋችን ላይ በሰፊው ያነሳነው::እን ጓድ ያፊት እዚህ ላይ ተስፋዬ ታደሰን ነጻ ለማውጣት የምንከራከር መስሎአቸው ይሁን አውቀው 'ስትናገሩ ተወዘገቡ'እያሉ ይደነፋሉ:: ግን ቢደነፉም ግድ የለን:: በሌዞና መሪዎች ድን ፋታ የምንሸበር ብንሆን ትግሉን ገና ድር አርገፍ አድርገን ትተነው ነበር::

እዚህም ላይ ከፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ጋር የምንጣላው ያው እና የዓመቱን ስንል እነሱ የዐለቱን ስለሚሉ ነው:: ማህበራችን ተስፋዬ ታደሰ ሰላይ አይደለም ብሉ እርሱን ነጻ ለማውጣት አልተነሳም::'ሰላይ ወሆኑ በሰርቴፊኬት ልናረጋግጥላችሁ አንችልም::'ብለዋል የፌዴሬሽኑ ጓዶች:: እውነታቸውን ነው:: ይህንን ለማድረግ አይችሉም:: ግን ደግሞ ተስፋዬ ታደሰም ሰላይ አይደለሁም ብሉ በሰርቴፊኬት ሊያረጋግጥ አይችልም:: እነዚህ ጓዶች ልብ ያላሉት የመሰለን ይህንን ነው:: እንደዚህ ዓይነቱን ክስ በዙውን ጊዜ ማረጋገጥ አይቻልም:: በዚህም ምክንያት ክሱ ወነዛተ ብቻ በአንዱ ሰው የፖለቲካ ህይወት ላይ የተፈለገውን ውጤት ሊያመጣ ይችላል:: በተራማጆች መካከልም በቀላሉ መጠራጠርንና አለመተማመንን ፈጥሮ ትግሉን ሊያዳክም ይችላል:: ለምሳሌ ያገራችን ሰላዮች 'ሳር ቀጠሉን' ሰላይ ነው የሚለውን ዘዴ



በጣም የሚጠቀሙበት ለዚህ ነው:: እኛም ለዚህ ነው እንዲህ ዓይነቱ ነገር በንቅናቄያችን ውስጥ ወደፊት ተደጋግሞ ሊመጣ ስለሚችል ካሁኑ የዐለቱን ሳይሆን የዓመቱን ጥምር የሚያተኩር ኘሪንሲፕለድ የሆነ አቋም ይኑረን የምንለው:: 14ኛው ጉባዔያችን ነገሩ ከተስፋዬ ታደሰ አልፎ የሚሄድ ኘሪንሲፕል የሚነካ መሆኑን ስላመነበት በዚሁ ጉዳይ ላይ ባሳለፈው ውሳኔ '... በማስረጃ የማይደገፉትን አሉባልታዎች ማሰራጨት አንድነትን የሚያናጋ ለትግላችን አደገኛ መሆኑን በመረዳት ለወደፊቱ ከዚህ ዓይነቱ የአሰራር ዘዴ የኢት. ተማሪዎች ማህበራት እንዲጠነቀቁ -... ከዚህም በላይ/ይህ ክስ/ ከጓድ ተስፋዬ ታደሰም አልፎ... በኢትዮጵያ ተራማጆች መሀል መተማመን እንዲጠፋና ጥርጣሬ እንዲነገስ ያደርጋል' የሚል ይገኝበታል::

ማስረጃ ይምጣ ስንል ሰርቲፊኬት አይደለም የምንጠይቀው:: 14ኛው ጉባዔያችን ላይ ጓድ እያሱ ማስረጃ ስንለው 'ምን ማስረጃ እንድሰጣችሁ ትፈልጋላችሁ'ብሎን ነበር:: ወቸስ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች አብረውት ሲሰሩ ቆይተው፣ እንዲያውም አንዳንዶቹ የሰደት ጓደኞቹ ሆነው ሳለ ዛሬ በፖለቲካ አስተሳሰብ ስለተለያዩ ብቻ እንዳልከሰሱት ተስፋ እናደርግ:: ስለዚህ 'ድርውንስ ምን ማስረጃ ይዛችሁ ነው ከስድስት ወር ወዲህ ሰላይ ነው እያላችሁ መክሰስ የጀመራችሁት'ብለን ጠየቅን:: ያገኛችሁትን ማስረጃ አሳዩን ለኛም ይበቃ ይሆናል ነው የምንለው:: ፌዴሬሽን ስብሰባ ላይ ማስረጃ ይቀርባል ሲባል ቆይቶ አሁን እዚህ ጉባዔያችሁ ላይ ይቀረብ ስላልን ከድፍረት ተቆጠረብን:: እንዲያውም በማስረጃ ፈንታ የመስካሪያችን 'አብዮታዊ ቃል' አላመናችሁም፣ የቃል ምስክርነታቸውን /ኢንቴግሪቲ/ ተጠራጠራችሁ በመባል ተወገዝን::

እናጠቃል:: ማህበራችን በተስፋዬ ታደሰ ሆነ በሌላ ጓድ ላይ ሰላይ ነው የሚል ክስ ሲቀርብ የሚከራከረው የኛው ተከሳሹን ነጻ ለማውጣት አይደለም:: በተቻለ እውነቱን ለማወቅ ነው:: ያለበቂ ማስረጃ እንዲህ ዓይነቱ መርዘኛ ክስ በቀላሉ እየተወረወረ የፖለቲካ ልዩነቶች ቁጭት መወጫ እንዳይሆንለመከላከልና በዚህ ጉዳይ ላይ ካሁኑ ኘሪንሲፕለድ አቋም መውሰድ የተራማጆች ተግባር መሆኑን ለማሳየት ነው:: በማህበራችን ውስጥ የብዙ ጓዶች ፍራቻ ዛሬም ሆነ ወደፊት ይህ ዓይነቱ ክስ በተራማጆች መሃል የተስፋፋ የትግል ዘዴ እንዳይሆን ነው:: በኢራቅ የኢት. ተማ. ማህበር ወኪል ጓድ ሳይ በዚሁ ጉዳይ ላይ የተናገረው ይህንኑ ፍራቻ ያመለክታል::ጓድ ሳይ 'ለጉባኤው/ ለፌዴሬሽኑ/ የማሳስበው በተስፋዬ አማካይነት በቀርብ ምስራቅና በአፍሪካ ያቋቋምነውን ያካባቢ ማህበር ለማጥፋት የሚጥር መሆኑን ነው' በማለት አሳስቦ ነበር::

ከዚህ በኋላ በተስፋዬ ታደሰ ጉዳይና ያወርጀ ማህበር ከርሱ ጋር 'በጥበቃ ገን ኙነት በመስራቱ'፣ 'የተራማጅ ኃይሎች የቃል ምስክር ነትና ኢንቴግሪቲ' እያለ ማስረጃ አቀ ርቡ በማለቱ ተወገዘና ደግሞ ሌላ የመወገዣ አቀጣጫ ተሰጠንና 'እየተከራከርን' ቀጠልን::

አደም ከድር መሃ የተባለ ሰው ከዚህ በፊት ስሙን ሰምተን የማናውቀው ድርጅት 'ሕብነአገን ለማሻሻል የተቋቋመ ኮሚቴ' ወኪል ነኝ ብሉ አንድ መልዕክት አነበበ:: ማህ በራችን የሚያውቀው ሕብነአገ ወኪል ጓድ አብዱል ሃፊዝ በተመለካቾነት ተገኝቶ ስለነበር 'ተቃውሞ' እያለ ሲጣራ ገራ ገባን:: በዚህ ጥያቄ ላይ እንገኘህ ብዙ ጥያቄዎች እያቀ ረብን መወያየት ፈለገን ነበር:: ግን በየት በኩል፥:

አሁንም የተፈለገው ከጉባዔው ውስጥ የሚደረገው ጠቃሚ ውይይት አልነበረም:: ከጉ ባዔው ውጭ የሚሰራጨው ፀረ_አወርጀ ማህበር ፕሮፖጋንዳ ነበር:: ስለዚህ ሌላው ቁም ነገር ሁሉ ተረስቶ እያሱ ዓለማየሁ ከነአደም ከድር መሃ ጋር አደረገሁ ስላለው የፈጠራ ኢንተር ቪውና ዓለማየሁ ገ/ጻድቅ የተባለ ጓድ 'የኢያሱ ልብወለድ' በሚል አርእስት ስለጻፈው ጽሑፍ ውይይት ተጀመረ:: የዚህን ልብወለድ ኢንተርቪው ታሪክ ለማያውቁት:_

ኢያሱ ዓለማየሁ የፌዴሬሽኑ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ አደም ከድር መሃ የተባለውን የሕብ ነአገ አባል ኢንተርቪው አደረግሁ ብሉ ገንቢሩን የሚያንቋሽሽ ራፖር ጽፍ በተነ:: ራፖሩ እንደወጣ ሕብነአገ ይህን ድርጊት አውግዞ መግለጫ አወጣ:: ከድር መሃም በበኩሉ ይህንን ኢንተርቪው ለኢያሱ አልሰጠሁም እራሱ የፈጠረው ነው በማለት በ13/5/74 መግለጫ አወጣ:: ይህ ከንገኘህ 'የኢያሱ ልብ ወለድ' በመባል የታወቀው ኢንተርቪው ስለሕብነአገ ከድርጅቱ አባሎች የተገኘ ነው ተብሉ ብዙ አደገኛ ገምቶችን ይዟል:: ከዚህም ፀረ ሕብነአገ ፕሮጀ ጋንዳ ሌላ የሌለ ኢንተርቪው ፈጥሮ ማውራት ራሱ ከተራማጆች ሀቀኛነት የራቀ ድርጊት መሆኑ ግልጽ ነው:: ስለዚህም መኩነን እንዳለበት ለማስገንዘብ ጓድ ዓለማየሁ ገ/ጻድቅ 'የኢያሱ ልብ ወለድ' በሚል አርእስት ይህን አድሃሪ ድርጊት የሚያወግዝ ጽሁፉን አቀረበ:: ታሪኩ ባጭሩ ይኸው ነው::

145ው ጠ/ ጉባዔያችን ላይ የተገኙት የገንቢሩ ዋና ጸሀፊ ሸህ ሁሴን ንግግር በደረጉ ጊዜ 'አንዳንድ ሰዎች የሚያደርጉትን ፀረ ሕብነአገ ፕሮጀጋንዳ...' መቃወማቸውን ሲገልጡ ይህ ቀጥሚ ማንን ያመለከተ እንደነበር በጉባዔው የነበረት ሁሉ አልሳቱትም:: እን ገኘህ ሸህ ሁሴንም፣ አደም ከድር መሃም፣ እያሱ ዓለማየሁም፣ ተስፋዬ ታደሰም ሌሎችም ስለ ጉዳዩ በቀርብ የሚያውቁ በተገኙበት፣ ስለዚህም ማጥበርበር በምንም ዓይነት በማይቻልበት ከ200 ሰው በላይ በተከፈለበትና ውሳኔ ሊሰጥበት በሚቻልበት ጉባኤ ላይ የፌዴሬሽኑ



ባለሥልጣናት ሌላ ሰንት 'ክርክር' ሲያነሱ <u>ይህንን ጉዳይ ለማንሳት አልደፈረም</u>:: እዚህ ግን ፌዴሬሽኑ ወሬፍ ቢያደርገው 'በሬ ወለደ' ብሉ 'በማጅሪቲ' ውሳኔ ሊያሳልፍ በሚችልበት ስስት ሰዎች ብቻ ደምጽ በሚሰጡበት ጉባዔ ላይ አነሱት:: አደም ከድር መሃ በዚህ ጉባዔ ላይ 'በሕብነአገ አሻሻይ ኮሚቴ'ስም ቀርቦ ሲናገር ስለሕብነአገ መሻሻል አምብዛም አላወራ:: በንግ ግሩ ስለሕብነአገ ሁኔታ አያወራ ትንሽ ካዘናጋ በኋላ 'አውን ለኢያሱ ዓለማየሁ ይህንን ኢንተ ርቪው ሰጥቼአለሁ' ብሉ የራሱን ፊርማ ከዳና ቁጭ አለ:: 'ሀለ የጻፍከው መግለጫ' ቢባል 'ተስፋዬ ታደሰ ነው የጻፈው' ወይንም ደግሞ 'ተስፋዬ ታደሰ አስቶኝ ነው' ብሉ በቀጡ ሳይለይ 'ይህ የተስፋዬ ታደሰ ሥራ ነው' አለንና ሌላ ቃል ሳይጨምር ቁጭ አለ:: ተስፋዬ ታደሰ ገና ድሮ 'በካውንስሉ' ውሳኔ ወጥቷልና ሌላ ነገሩን በቀርብ የሚያቅ ሰው ሳይታሰብ ብድግ አለ:: የሕብነአገ ወኪል ጓድ አብዱል ሀፊዝ ተነሳና 1ኛ/ የአወርጀ ማህበር ከሕብነአገ መጣ የሚለው መግለጫ በእርግጥ ከሕብነአገ የወጣ መሆኑን 2ኛ/ ከድር መሃ ጻፈው የተባለውን ደብዳቤ በር ገጥ የጻፈው መሆኑን ለቤቱ አስረዳ::

'የኢያሱ ልብ ወለድ' ብሉ በጻፈው በጓድ ዓለማየሁ ገ/ጻድቅ ላይ በአደሉ የከድር መሃ ልብወለድ ላይ በመመርኮዝ መረባረብ መጣ:: ከዓለማየሁ አልፍ ጠቀላላ 'የአወርጀ መሪዎች' ላይ የማውገዝ ውርጅብኝ ይጉርፍ ጀመር:: አሁንም አልፍ ተርፍ 'በማውገዝ ብቻ መታለፍ የለበ ትም፣ እነዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ናቸው...'እየተባለ ይደነፋ ጀመር:: ቤቱ እንደገና እንደ 'ሄስቴሪያ' ቀከረው::

ከድር መሃ የራሱን ፊርማ ከዳ:: ታዲያ የአወርጀ ማህበር ምን ይበል:: ከሁለት ነገሮች ሌላ ብዙም ማለት አንፈልግ:_

1ኛ: ከድር መሃ የዛሬውን አያድርገውና 'እያሱ ውሸተን ነው ኢንተርቪው ያለው ውሸተን ነው',

ይል የነበር ጊዜ የዚህን ሰዎች የመሰሉችን ቀራል 'የምትጠራጠሩ' መሆናችሁን በጽሁፍ ገልጻችሁ ነበር::እና ከዚህ 'አጠራጣሪ'ሰውየ ጋር እንደገናት እስከኢንተርቪው'ለንታደል' ይቀርና በርሊን እስከመጣ ድረስ ዓይኑንም አይተነው አናውቀም:: ስለዚህ ከናንተ ይበልጥ እና ቀውምና እናም እንደናንተው 'ቀራሉን እንጠራጠራለን::' በተለይማ እንዳህ ዓይን ባይን የገዛ ፊርማውን ሲሸፍጠን 'ምን አገኘተ ይሆን...' 'ምን አገኘተ ይሆን'እንላለን:

2ኛ ከዚህም አልፈን የዚህ ሰው'ቀራሉ አጠራጣሪ' ስለመሆኑ <u>እርግጠኞች</u> እንሆናለን:: ግን ይህ እርግጠኛነታችን በኛ ብቻ እንዲወሰን አልፈለግንም:: ቤቱም እንደኛው ነገሩ እንዲብራራለት ይፈልግ እንደሆነ ብለን <u>ከዚህ በፊት ከድር መሃ ኢንተርቪው ለለመስጠተ የጻፋቸው የማይከዳቸው</u> ደብዳቤያች ፋይላችን ውስጥ ስላሉ ከሱ ለመሆናቸው ለማረጋገጥ ጽሀፈትንና ፊርማውን ማስተያየት

የፈለገ ያስተያዩ አልን::ሊቀመንበሩ 'ጥሩ የከድር መላ ጽሁፈት ይታይ' ብሎ ሲስማማ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ዉርስ ተደናገጡ:: ቆየት ብሎ ፈርማ አይታይብንም የሚሉ ሆኑ:: ተበድያለሁ፣ ይወገዝልኝ፣ መወገዝ ብቻ አይበቃም ነገሩ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም'ሲል የቀየው እያሱ ዓለማየሁ ብድገ ብሎ በቀጥ 'እዚህ ፈርማ የሚጣራበት ምክንያት የለም' አለ ገና ቀጭ አለ:: እውነትን አፍናለሁ ብሎ ያደረገው ከንቱ ጥረት የባሰውን አጋለጠው::ፈርማ ውም <u>አይታይባቸውም ተብሎ በሊቀመንበሩ ተወሰነ</u>::

እንግዲህ ከመወገዝ 'እንደማናመልጥ' ግልጽ ነበር:: ነገር ግን በንዲህ ዓይነት የሚወርድብንን' ታሪካዊ ተርገም' ያለው ወገዛ ከመጤፍም አንቆጥረው አልን:: ይልቁንስ ተሎ ተሉ አውገዘውን ወደፊት እንድንራመድ አሳሰብናቸው::

ውሳኔው ተቀነባብሮ እስኪመጣ ብዙ ጊዜ ወሰደበት:: 'በሙሉ ድምጽ _3ለ0_ ተወገዝን:: ለነገሩ ግን ይቾን ውሳኔ ስናይ ትንሽ ተገረምን:: ቀደም ብሎ በተሰፋየ ታደሰ ጉዳይ 'ይህንን ሰው ከማውገዛችን በፊት ለሶ የምትሉትን ማስረጃ ስጡን' ስንል 'በተራማጆች መሃል ምንድነው ማስረጃ ብሎ ፈሊጥ' በሚል ማስረጃ መጠየቃችን እንደ ተጨማሪ ወንጀል ሆና ተወገዝን::ይኸኛው አሁን ተረስታል:: አሁን ደግሞ ማስረጃ አናቀርብ እያልን እንቀበልም ያሉት እነሱው ሆነው 'በቂ መረጃ ሳይዙ...'በሚል ሰበብ ተወገዝን::

ሌላ ማውገዢ እስኪመጣ ድረስ ደግሞ አንዳንድ ቀም ነገሮች ጠልቃ እያስገባን ለመወያየት ጥረት አደረግን:: ወደሌላ ጉዳይ ታለፈ::

3. <u>በስሁት ወቅት በሲት. ተማ. ማህበራት ውስጥ በሰሉት ቾግሮች</u>

እንባቤ እንደሚያስታውሰው ይህንን ጉዳይ ዓይኑን እንዳናየው ብለው አጀንዳችንን አልተቀበሉም:: በነሱ አጀንዳ ውስጥም አላስገቡትም:: ነገር ግን እንደምንም እየተፍጨረጨርን እዚህ ጉባዔ ላይ ስለተማሪ ማህበራት ቾግር አልፍ አልፍ ለመናገር ቾለናል:: በያለበት እየተቀራረጠ የተወያየንበት ቢሆንም እዚህ ጽሁፍ ላይ በዚህ ጉዳይ የተነጋገርናቸውን ሰብሰበ መልክ ማስያዝ ተገቤ መስሎናል:: የመህበራት ቾግር በርግጥ ተነሳ ማለት የሚቻለው ከሱዳን አንዱን ማህበር/ፌዴሬሽኑ የለም የሚለውን/ ወክሎ የመጣው ጓድ ኃይሉ ገርባባ ጉባዔው መዉረሻ ድረስ መቀየት አልቻለም ብሎ በ4/9/74 ማታ ቃል ይሰጠኝ በማለት ሲጠይቅ ነው:: አንድ አጭር ስቴትመንት ለስጥ ብሎ ጀመረ::

ጓድ ኃይሉ፡ በሱዳን ማህበር ስም...

ጓድ መላኩ፡ አብጿክሸን

ጓድ ኃይሉ፡ በግለሰብም ለስማ:: መግለጫየን ብቻ ተቀበሉኝ:: እዚህ ሱዳንን እወክላለሁ ብሉ የተ...

ከፌዴሬሽን በዙል፡ ኦብጀክሽን



ጓድ ኃይሉ፡ በግለሰብ ደረጃ ነው የምናገረው...

ጓድ በቀለ፡ እኔ እያልክ ተናገር:: ይኸ ጠላ ቤት አይደለም::

ሊቀመንበር፡ በሰጠሁህ ፍሬምወርክ ውስጥ ተናገር::

ጓድ ኃይሉ፡ ስንት ሚሊታንት ስደተኛ ወክየ ነው ከሱዳን ድረስ የመጣሁት:: በግለሰብም ደረጃ ቢሆን እሺ ልናገር:: እዚህ ሱዳንን እወክላለሁ ብሎ ..../ ከፌዴሬሽኑ ሰዎች በመጣ ጩኸት እንደገና ይቋረጣል/

ጓድ ጌታቸው/ከሎዛየ/ ምንም እንኳ ካውንስሉ ቢወስን ለኛ ኢንፎርሜሽን ያህል ስላለው ቾግር እንዲናገር እንዲፈቀድ እጠይቃለሁ:: እኔ እንደረዳኝ ሬዘንታቲዝም መቀበሌ አይደለም::ሱዳን ሁለት ማህበር አለ ይባላል:: አንዱ የፌዴሬሽኑ አባል ነው:: ያኛው ምን እንደሆነ ይናገር:: ካልተፈቀደለት ውጪም ሊነገረኝ ይቾላል::

ፍስሀ/የፌዴሬሽኑና 'የሱዳኑ'/ ካውንስሉ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት ነው የምንሰራው::በግለሰብ ደረጃ ውጭ ሊያናግር ይቾላል::

ሊቀመንበር፡ በግለሰብ ደረጃ ይናገር:: ነገሩ ሴንሲቭ ነው:: ግን ቢሆንም ዕድል እንድን ሰጠው አፒል አደርጋለሁ::

ከዚህ ሁኔታ በውኪታው መሃል ጓድ ኃይሉ መግለጫውን እንደምንም ማስመዝገብ ሲጀምር ሁሉም ያዳምጥ ጀመር::

'በሱዳን ከአርባ በላይ የሚሆኑ ስደተኞች ተማሪዎች አሉ:: ከነዚህ ውስጥ 31 ህጋዊ በሆነና በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተቋቋመ ማህበር አላቸው:: አሁን እዚህ ጉባኤ ላይ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚደንሻል ካውንስል አባል ነው ተብሎ በጨሳተፍ ላይ ያለው መምህር ፍስሀገ/ሚካኤል የመጣው ስድስት ሰው ወክሎ ነው:: ይህ ጉዳይ ሳይጣራ በሱዳን ተማሪዎች ስም እዚህ እንዲሳተፍ በመሆኑ ህገ ወጥና ፀረ ዲሞክራቲክ ነው:: አሁን እኔ የማሳስበው ከሃገር ቤት የመጡት ጓዶች ወደአገር ስመለሱ እንገረመንገዳቸውን በአንድ ቀን ሊያጣሩ ስለሚቾሉ ጉባዔው በዚሁ ተባብሮ የነሱም ፈቃደኛነት ተጠይቀ በሱዳን ባሉት ሚሊታንት ስደተኞች ስም ከንገዴህ ማንም እንደፈለገው እንዳይጠቀም ይደረግ ዘንድ የአገር ቤቶቹ ጓዶች እንዲያጣሩ እጠይቃለሁ::'

ይህንን ቀለጭ ያለ አቃም 'በወዲያ በኩል'ሱዳንን እወክላለሁ ብሎ ራሱ ካውንስሉ ውስጥ ሆኖ ያሳለፈውን ውሳኔ መሸጉ ከተቀመጠው ከፍስሀ ሸሸት ጋር አንባቤ ያነጻጽረው:: ጓድ ኃይሉ በራሱ፣ በማህበሩ፣ በሚወክላቸው ጓዶቹና በሚናገረው ሙሉ ርምነት እንዳለው ግልጽ ነበር:: 'ይጣራ' ሲባል ፍስሀ 'እሺ ይጣራ' አላለም:: ነገሩን'ካውንስሉ' አጥንቶ ወስኗል ነው ያለው:: የባሰ አለ:: ጓድ ኃይሉ ሁለት ደቂቃ ተናገሮ ፍስሀን የማያላውስ 'ቦምብ' ነው የጣለበት:: 'የሃገር ቤት ጓዶች እንገረመንገዳቸውን በዚያ ይለፉና ባንድ ቀን ሊያጣሩ ይቾላሉ' ነው ያለው::

የማህበራትን ችግር በማመለከተው ደግሞ በሌላው በቅርብ ምስራቅና በአፍሪካ የኢት. ተማሪዎች ማህበር ስም ጓድ ሳይደ ያቀረበውን መግለጫ ከዚህ በታች እናሰፍራለን:: ያው በጓድ ኃይሉ ጊዜ እንደታየው 'እናገራለሁ' 'የለም አትናገርም' እየተባለ ጥቂት ክርክር ተደርጉ እሱም 'በካውንስሉ' የተፈቀደለት በግለሰብ ደረጃ ብቻ ስለሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚከተለውን አስመዘገበ::

> የሊባኖስ ማህበር ሰባት ሰው ብቻ ነው ያለበት የተባለው ውሸት ነው::35 አባሎች አሉት:: ሱዳን እና የምናቀው 31 አባላት ያሉትን ጓድ ኃይሉ የሚወክለውን ነው:: እርግጥ ጓዶች ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሰባት ሆነው ያቋቋሙት ማህበር አለ::ሊባኖስ ጋር የሚተባበር የማህበር አዘጋጅ ኮሚቴ ተቋቁሟል:: በአልጄሪያ ማህበር የለም:: ሁለት ግለሰቦች አሉ:: ሁለት የፖለቲካ ጥገኞች አሉ:: ተማሪ የለም፤ ማህበርም የለም:: እና በአካባቢው አብዛኛውን የሚወክል ማህበር ያለን ነን::ፌዴሬሽኑ በመካከለኛው ምስራቅና በአፍሪካ የኢት. ተ. ማህበር ስም የተሰበሰው ማህበር በመካከለኛው ምሥራቅ አንድም አባል የለውም::አልጄሪያ ምንም ማህበር የለም:: ሱዳን ማህበር ሳይሆን እነመምህር ፍስሀ ናቸው እንደማህበር የሚያስቆጥሩት:: እና የምንለው በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ተደራጅተናል:: በዚህም እንወክላለን:: ከፌዴሬሽኑ ጋር አንድነትን ተባብር ጠይቀናል:: እነሱ ግን ጓዶቻችንን እየጠሩ መካከለኛው ምስራቅንና አፍሪካን ይወክላሉ ይላሉ:: ገዛኸኝና ፍስሀ ማህበር አይደሉም:: የተማሪ አንድነት ከተፈለገ ይህ ጉባዔ ከሊዙና ከሊዙሲ ከፌዴሬሽን የተውጣጣ ኮሚቴ አቋቁሞ ነገሩን እንዲያጠና እናሳስባለን:: ኃይሉ ለሊዙዋ ጓዶች ጥሪ አድርጉ ነበር:: እናም እንዲሁ አቅርበን መልስ አልተሰጠንም::

እያን ለዚህ ለተደረገላቸው ጥሪ የሃገር ቤቶች ጓዶች እሺም እምቢም አላሉም:: በዚህ አካባቢ እውነትን ለማረጋገጥ አንድ ቀን ይበቃል ይላሉ እነጓድ ኃይሉ:: እስከዚህ ድረስ በራሳቸው ስለሚተማመኑ:: ታዲያስ የፌዴሬሽን ጓዶች ቀንጣት በራሳቸው ቢተማመኑ:: ይህን ጥሪስ ላገር ቤት ጓዶች እነሱም ማቅረብ በተገባቸው ነበር:: እርግጥ ነው ያገር ቤት ጓዶች በዚያ ቢያልፉ እውነቱ ይወጣልና ወጥመድ ውስጥ እንገባለን የሚል ፍራቻ አለባቸው::ግን የፌዴሬሽኑ ጓዶች ነገሩን ለመገላበጥ ቢሆን ከላይ የወረደ ልዩ ስጦታ አላቸውና ጥራሹን በዚህ በተደረገው ጥሪ ምክንያት እነሱ ሳይሆኑ ካገር ቤት የመጡት ጓዶች 'ወጥመድ' ሲገቡ ታያቸው:: ተጠንቀቁ ይሏቸው ጀመር:: ጓድ ገ/እግዚአብሄር ተነስቶ:'ወጥመድ ውስጥ ሊያስገቡዋቸው ነው ያገር ቤቶችን ጓዶች የሚፈልጉት:: በዚያ በኩል ያለፉ እንደሆነ ትልቅ አጂቴሽን ሊያደርጉባቸው ነው' አለና ቤቱን አስጠነቀቀ::

የምን ወጥመድ አመጣችሁ ደግሞ:: ማነው ወጥመዱስ የሚገባው:: ካልቻሉ ለምን ብለን አጂቴት እናደርግባቸዋለን:: እውነቱ ቢጋለጥ ወጥመድ የምትገቡ እናንተ እንደሆናችሁ ስለምታውቁት ተጨባጭ እውነትን ለመሸሸ የምታመጡት የተለመደ ተልካሻ ሰበባችሁ ነው:: እና እንደሆንን ለኢት. ተማሪዎች አንድነት ከመታገል በስተቀር ለማንም ወጥመድ መዘርጋት ባሳባችን አይመጣም:: ከናንተም የምንጣላው በንቅናቄያችን ውስጥ ችግር በተነሳ ቁጥር በተጨባጩ እውነት ላይ የተመሰረተ አንድነታችንን የሚያጠነክር አቋም ይኑረን ስንላችሁ እምቢ እያላችሁ ነው::

በዚህ በኩል በጉባዔው ላይ ለንገልጽ ሞከረን ባለጉባዔዎቹ ስላላስቻሉን አቋማችንን እንናገር:: የኢት. ተማሪዎች ትግል እየዳበረ ቢሄድ የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እየጎሉና አቀድ



እየያዙ ይሄዳሉ:: ነገር ግን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመዋጋት ድርጅታዊ አንድነታችን ምን ጊዜም መናጋት የለበትም:: በፖለቲካ ልዩነቶች ምክንያት አንዳንዴ ባንዳንድ ቦታ የንቅናቄያችን ድርጅታዊ አንድነት የሚናጋበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል::እዚህም ላይ እና የዐመቱን ስንል የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች የሰኩቱን ስለሚሉ እንጋጫለን::

በአንድ አካባቢ ሁለት ማህበራት ቢቋቋሙ ዘለን አንዱን 'ልክ ነህ እናውቅሃለን' ሌላውን ደግሞ 'ዞር ነህ አናውቅህም' ለማለት አንችልም::በዚህ ጥድፊያ አያስፈልግም::ምክያቱም እናርኪ እንጂ ትግል በዚህ ዐይነት አይቻልም:: 14ኛ ጉባዔያችን ላይ በቅርብ ምስራቅና አፍሪካ ከተቋቋሙት ሁለት የአካባቢ መህበራት አንዱ ተገኝቶ ነበር:: በሱዳንም ካሉት ሁለት ማህበራት አንዱ ተገኝቶ ነበር:: ነገር ግን ማህበራችን አንደናቸውንም ለይቶ አላወቀም:: ለምን?

መጀመሪያ ነገር አንዱን የለህም ብሎ ሌላውን ከማወቅ በፊት ሁለቱም የኢት. ተማ. ማህበራት ናቸውና፤ ሁለቱም ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ናቸውና ነገሩን አጥንቶ የሚዋሃቡትንና ድርጅታዊ አንድነታቸውን የሚመሰርቱበትን ዘዴ ከነሱው ጋር ተባብሮ መፈለግ ያሻል:: ማንም ለኢት. ተማሪዎች አንድነት የሚቆረቆር ሰው በመጀመሪያ ይህንን ማድረግ አለበት::ይህ እነዚህን ማህበራት ለማዋሀድ ሚደረግ ጥረት እንዳይደናቀፍ 14ኛ ጉባዔያችን ለጊዜው ማንናቸውንም ለይቶ ከማወቅ ተቆጥቧል::

በሁለተኛ ደረጃ ግን ይህ ጥረት ካልተሳካ ተገቢውን ጥናት አድርጉ አብዛኛውን ተማሪ የሚወክለውን ወገን ለይቶ ያውቅና 'ማይኖሪቲው' የሚያደርገውን የመስነጣጠቅ ሥራ ይኮንናል::

የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ግን በአፍ ብቻ ለኢት. ተማሪዎች አንድነት ተቆርቋሪ ነን ከማለት በስተቀር እነዚህን ማህበራት ለማዋሀድ ምንም ጥረት አላደረጉም:: በተለመደው የእንደልቡ ሥራቸው ለነሱ የሚመቻቸውን ነጥለው አውቀው ሌላውን ወገን ጨርሶ የለም ይሉናል:: በዚህም ድርጊታቸው በንቅናቄያችን ውስጥ አንድነትን ሳይሆን መስነጣጠቅን እንዳገዙ ለማንም ገለጽ ነው::

ባጭሩ እና በዚህ አካባቢ አስቸኳይ ድርጅታዊ አንድነት እንዲገኝ ጥረት ይደረግ እንላለን:: ለይቶ አንዱን ለማወቅ ደግሞ እውነቱ በሚገባ ተፈልጎ ይውጣ:: ጓድ ሳይደ በአልጄሪያ ማህበር የለም ማስረጃ አለኝ ስለሚል ያምጣ:: ጓድ ኃይሉ ፍስሀ ሰባት ሰው ብቻ ነው የሚወክለው ማስረጃ አለኝ ስለሚል ያቅርብ:: ጓድ አቦማ በሊባኖስ ሰባት ማህበርተኞች ብቻ እንዳሉ ሰው ነግሮኛል ይላል:: የተሻለ ማስረጃ ያምጣ:: እውነቱ ይጣራ:: ማን ማንን እንደሚወክል ይታወቅ:: አጥበርባሪውና ከፋፋዩ ይጋለጥ:: ይህን ሁሉ በአቋም መግለጫችንና በመደምደሚያ መግለጫችን ላይ በሚገባ ተናግረነው ነበር:: ከፌዴሬሽኑ በኩል ሰሚ ጠፋ::

በሴቶች የጥናት ክበብ ጉዳይም ያለን አቋም ይኸው ነው:: አንድነት ከፈለግን ዘለን የሚያመቸንን ወገን መርጠን እናስገባ ነው የምንለው:: ዓመቱን ሙሉ ፌዴሬሽኑ ዓለም ዐቀፍ የሴቶች የጥናት ክበብ አባሌ ነው ሲል ከረመ:: በአውሮፓ የሴቶች የጥናት ክበብ ስብሰባ ጠ/ጉባዔ ማህበራችን በመጓከሙ ዛሬ በሀገራችን እህቶቻችን እንዲህ በጀግንነት ሲነሱ የሚገባንን አልፈጸምንም በማለት አስረዳ:: ከዚህም ተነስቶ በአሁኑ ጊዜ እንዴት በዚህ ትግል ለመሳተፍ እንደሚቻል ተወያይቶ የሥራ ተልዑን አወጣ:: ፌዴሬሽኑን በሚመለከተው በኩልም መሪዎቹ በገዛ ፈቃዳቸው የወሰኑት እንጂ የአባልነቱ ጉዳይ የአውሮፓውና የአሜሪካው የተማሪ ማህበራት እንዳደረጉት በጠቅላላ ውሳኔ ያልተወሰነና የፌዴሬሽን አባል እንዳልሆኑ ውሳኔ አሳለፈ:: ሌዘና ባስለመደው የጉልበተኛ ክርክር ከአሜሪካ የመጡት ሴቶች መውጣታቸሁ ፀረ-ዲሞክራቲክ ነው ሲሉ የአውሮፓው የሴቶች የጥናት ክበብ ደግሞ ድርውንም ገብታችኋል የተባለነው በመሪዎቻችን ፈላጭቆራጭነት ፀረ ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ ነው:: የፌዴሬሽን አባል ሆነንም አናውቅም:: ብለው ተከራከሩ:: ሃኖቨር ጉባዔ ላይ ማህበራችን ፌዴሬሽን ውስጥ ገባ ብሎ አልገባም ሲል በነጋዴ ሰለቀን ተሰማ 'እንገዲያውስ አትወጣም' የተባለውን ያስታውሰናል:: በአውሮፓ ያሉት እህቶቻችን ፌዴሬሽኑ ውስጥ አልገባንም ይላሉ:: አሜሪካ ያሉት ደግሞ ገብታችኋል አትወጡም ይሏቸዋል:: እነጌቶች አበበች ለዚህ ችግር ያገኙለት ማስታረቂያ ዓለም ዐቀፍ የሴቶች የጥናት ክበብ በፌዴሬሽኑ ውስጥ ድምጽ የሌለው አባል ነው የሚለው ፈሊጥ ነው::

በዚህ ጉዳይ ላይ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ዘለው ወገን ለይተው ጣልቃ ከመግባት አስቀድመው፣ በአንደኛው ጉን ተሰልፈው ነገሩን ከማባባስ ይልቅ የእህቶቻችንን ዲሞክራሲያዊ መብት በመጠበቅ ውይይቱ በሁለቱ የጥናት ክበቦች መሃል እንዲቀጥል ማገዝ ነበረባቸው:: የዓለም ዐቀፍ የሴቶች የጥናት ክበብ ጠ/ጉባዔ በነገሩ ከስምምነት ላይ እስኪደርስና ከፌዴሬሽኑም ሆነ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸውን የግንኙነት ዓይነት እስኪወስን ድረስ የሴቶችን የጥናት ክበብ ምንም ዓይነት አበል አርጉ መቁጠር ወገን ለይቶ ጣልቃ መግባት ነው:: ፀረ-ዲሞክራቲክ ነው፣ እህቶቻችን ለአንድነታቸው የሚያደርጉትን ትግል ያደናቅፋል::

4. በጭር የተቋጨው የፓለቲካ ውይይት

በ4/9/74 ቢት ምናልባት የማውገዝ ጋጋታ አይኖርበትም በሚል ዕምነት በትንቱና ደረጃ ሀሳብ ሳጣብ ለመለዋወጥ ተስፋ የጣልንበት የፖለቲካ ውይይት ተጀመረ:: በዚህ ጉዳይ የተደረገው 'ክርክር' ብቻውን አንድ መጽሀፍ ይወጣዋል:: ግን በመሰረቱ የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች በቁም ነገር ተከራክረው በ14ኛው ጉባዔያችን ላይ የወሰዱነውን ሬቮሉሽናዊ አቋም ሊሸሩ አልቻሉም:: መከራከር ትተው እና የምንለውን ማጣመም ብቻ ነበር ሥራቸው::



ዛሬ የህዝቡን ንቅናቄ በመምራት ላይ ያለው ንዑስ ከበርቴው ነው ስንል፣ ሬቮሉሽኑን ንዑስ ከበርቴው ወደፊትም መምራት አለበት አሉ ይባልልናል:: የህዝቡን ንቅናቄ ሰብስቦ የሚመራ ድርጅት የለም፣ ሀሊናዊ ሁኔታ አልተሟላም/ስብጀክቲቭ ኩንዲሽን አልተሟላም/ ስንል፣ ህዝቡ ደንቆሮ ነው ጨርሶ የፖለቲካ ሀሊና የለውም አላቸሁ እንባላለን:: የተማሪው ንቅናቄ የወዝአደሩ ፓርቲ ብቻ እንዲቋቋም ሳይሆን የተጨቆኑ ሁሉ እንዲደራጁ ማገዝ አለበት ስንል፣ እናንተ ፋሽስቶች ይደራጁ ነው የምትሉት ይባላል:: ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ቅራኔ በአንድ በኩል ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝቦች መሆኑን ባንረሳ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ካሉት ልዩ ልዩ ቅራኔዎች ዋነኛው በጭሰኛና በባለመሬት መካከል ያለው ነው:: 'መሬት ላራሹ' የጊዜው ዋና ጥያቄ የሚሆነውም ለዚህ ነው ስንል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትነትን ተዋቸሁት ተባልን::/በነገራችን ላይ መሰብሰቢያ ቤታቸው በር ላይ እነዚሁ ጓዶች በትልቁ -Feudalism no,Peoples de-[illegible]s!- ብለው የጻፉትን አይተን በዚህ ብቻ ፀረኢምፔሪያሊስትነትን ተዋቸሁት ማለቱ በሀሳባችንም አለመጣ::

እንግዲህ አንድ ቀን ሙሉ በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን በኋላ የደንቆሮ ጨዋታ እንደተያዘ ግልጽ ሆነ:: ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች እንደምናወራ ታየ:: ሁለትና ሁለት አራት ነው ስንል፣ ሁለትና ሁለት አምስት ነው ብሏችኋል ከሚል 'መንደርደሪያ' እየተነሱ ስላስቸገሩን መወያየት አልተቻለም:: የረባ ውይይት አለመቻሉን እንደተረዳን ጊዜ ሳይባክን ወደ ሀገማህበሩ ጉዳይ እንድናልፍ በማለት ውይይት አላስቸል ያለውን ድርጊታቸውን በመቃወም መግለጫችንን ሰጥተን 'በውይይቱ' መሳተፍ አቆምን:: ነገር ግን በሰፊው ተማሪ ፊት የሚያጣምሙብንን እያቃናን፣ የኛን መስመር በደንብ እያሳየን፣ የነሱን መስመር እያጋለጥን እንቀጥላለንና እስከዚህም አልተጨነቅንበትም ነበር::

ለዚያውም በሰፊው ተማሪ ፊት መከራከር ተማሪውን ይከፋፍላል፣ ብዙ አትጻፉ በሚለው በኩል አዲስ የተገለ ግንባር ከፍተዋል:: ይህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መታዘብ የጀመርነው ነው:: በአውሮፓ ማህበር አንዳንድ ጓዶች በመሃከላችን ያሉት ልዩነቶች በሰፊው ተማሪ ፊት እየተፍረጠረጡ ውይይት እንዲደረግባቸው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ጽሁፎች እያወጡ በትነዋል:: እነዚህ ጽሑፎች ስላሉት ልዩነቶችና በተለይ የፌዴሬሽኑን የከሰረ ወላዋይ መስመር እያጋለጡ በሰፊው ተማሪ ዘንድ ብዙ ተቀባይነትን አትርፈዋል:: የዚያኑ ያህል በፌዴሬሽኑ አካባቢ ሽብር የፈጠሩ ይመስላል:: 14ኛው ጉባዔ ላይ አንዳንድ ጓዶች እንደዚህ አውሮፓን ያጥለቀለቁ ጽሁፎች' እያሉ ቅሬታቸውን ቢገልጹም ፌዴሬሽኑ ጉባዔ እስኪደርሱ ድረስ ይህን ማህበራችን የከፈተውን ግልጽ የአይዲዮሎጂ የትግል ምዕራፍ ለማስኰ

ነን ስለደፈረም ነበር:: እነጋዴ በቀለ ያመጡትን ጥናት ስጡን ብለን በገጠይቅ 'ድፍረት ነው፡፡ ደሞ ወስዳችሁ ዘጠኝ ገጽ ለመዘብዘብ ነው' ብለው እምቢ የተባል ነው፤ 'የእያሱ ልበወለድ' ብለው የተሳፈው የዓለማየሁ ገ/ሕይወት ጽሁፍ ከነአሥራት ገርማ ጽሁፍ ጋር እያዙ እንዲህ የመረረ ወገዛ የደረሰበት፤ እነዚህ ሁሉ የአቋሙ ሽሽት ምልክቶች ናቸው::

የጽሁፎችን ይዘት እየተነተኑ እየጠየቁ መከራከር የተለመደ ነበር ነው:: የፌዴሬሽኑ ባለስልጣኖች ግን 'ተማሪውን ለመከፋፈል ተነስታችኋል:: የተማሪውን ገንዘብ ለምን በነዚህ ፍሬከርስኪ ጽሁፎች ታባክናላችሁ ወዘተ. እያሉ 'ዳርዳሩን' የሸሸት ክርክር ደምረዋል::በዚህ ጉዳይ ላይ ከሃገር ቤት የመጡትም ጓዶች 'እነዚህ ጽሁፎች ተማሪውን ይከፋፍሉብናልና አትላኩብን አደራ ብለውናል::ጓድ አበባ ምትኩ ከነጭራሹ ለነዚህ ጽሁፎች በሚደረገው ወጭ በኩል ዞር በመከራከር 'ጉባዔያችሁ ላይ በገንዘብ ችግር ምክንያት ከምግባችሁ ቀንሳችሁ እንደነበር አማረ ነገረኝ:: እነዚህ የመሳሰሉ ጽሁፎችን በማውጣት ታድያ ለምን ገንዘባችሁን ታባክናላችሁ' የሚል አነጋገር አምጥቶ ነበር::

ይህ መቸስ ወርስ አለመገባባት ነው::እነዚህን ጽሁፎች በማውጣትና አቀማችን እስከፈቀደ ወደአገር በማስገባት አገር ካሉት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር በቁም ነገር ስለነጻነት ትግላችን መወያየት እንድንችል ገንዘብ ወጭ አድርገናል:: ነገር ግን በዚህ የተነሳ አባሎቻችን ጦም ማደራቸውንና በማህበራቸው ችግር መካፈላቸውን እንደጉዳት ቆጥረው እስካሁን አልተጠየቅንበትም:: ጽሁፎቹ 'ይረባሉ አይረቡም' ብሎ መከራከር ያባት ነው:: በነሱ የተነሳ ተማሪ ጦሙን አደረ ብሎ መከራከር ግን በአውሮፓ የምንገኝ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን ቆራጥነት የሚንቅ አስተሳሰብ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም::

ሁለተኛው ደግሞ ጽሁፎቹ ተማሪውን ይከፋፍላሉ ይባላል:: <u>ይህንን ከሰፊው ተማሪ ሌላ በሰፊው ተማሪ በታ ሆኖ ማንም ሊፈርድ አይችልም</u>::እነዚህ ልዩነቶች ራሳቸው የመጡት የተማሪው ንቅናቄ <u>በማደጉ</u> ስለሆነ በሰፊው ተማሪ ፊት እየወጡ በግልጽ ቢተቻቸው መከፋፈልን ያመጣሉ ማለት ንቅናቄያችንን ዝቅ አድርጎ መመልከት ነው::እርግጥ ውይይቱ መስመር እየያዘ ሲሄድ፤ እንከርዳዱ ከስንዴው፤ የደገፊው ንዑስ ከበርቴ መስመር ከረጋው ረቮሉሽናዊ መስመር፤ የወላዋዩ መስመር ከቆራጡ መስመር እየተለየ ንቅናቄያችን የተጣራ ረቮሉሽናዊ መስመር እየያዘ ይሄዳል:: ይህ ታዲያ መከፋፈል አይደለም:: በረቮሉሽናዊው የትግላችን ጎዳና ላይ ወደፊት መራመድ ነው እንላለን::

ዛሬ የምንለያይባቸውን የፖለቲካ ጉዳዮች በሚገባ ብናውቃቸውና <u>ሰፊው ተማሪም</u> ቢያውቃቸው በማንለያይባቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ ድርጅታዊ አንድነታችንን ማጥበቅ እንችላለን:: ልዩነቶቻችንን በማድበስበስ የሚገነባ አንድነት ግን ዘላቂነት አይኖረውም:: ስለዘላቂው ትግላችን በኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል መደረግ ያለበት ውይይት በምንም



ዓይነት ሊታፈን አይችልም:: ለማፈን መሞከርም አይገባም:: የዚህን ዓይነት ውይይት ዋጋ ቢስና ትርፍ ጸጉር ስንጠቃ እየመሰላቸው ይህን ከሚያንቋሽሹ ሰዎች እንዲጠነቀቁ ታላቁ ሌኒን ለሩሲያ ተማሪዎች ያስተማራቸውን ጠቅሰን በዚህ ጉዳይ ላይ እንደመድማለን::

> They(the student youth,ed.) should be aware of those false friends of the youth who divert them from a through revolutionary training through recourse to empty revolutionary or idealist phrase-mongering and <u>phlistine complaints about the the harm and uselessness of sharp polemics between the revol-</u>tionary and the opposition movements, for, as a matter of fact these false friends are only spreading an unprincipled and unserious attitude towards revolutionary work. (Lenin, Collected works,Vol.VI, p.471. Emphasis ours.)

ስለዚህ የፖለቲካ ውይይት የምንናገረውን ከመጨረሳችን በፊት የምንጨምረው ነገር ቢኖር ስለሀገር ቤት ንቅናቄ የተነሳው ክርክር ነው::እዚህም ላይ በተለይ ባሁኑ ወቅት ብዙ የፖለቲካ ልዩነቶች ቢነሱ ጥሩ ነበር:: ስለወደፊቱ ግንኙነታችንና ትብብራችን ተጨባጭ እርምጃዎችን እያነሳን ብንወያይ ጥሩ ነበር::ግን 'የታህሳሱ ዕልቂት የመጣው በተማሪዎች ገራ ቀደምነት ነው ብላችኋልና የሚል ክስ ዳብ አለብንና በዚሁ ላይ ሙግት ተጀመረ:: ማህበራችን እንኳን እኛን ማውገዝ 'በሬ ወለደ'ቢባል በማጆሪቲ እያ ብሎ ሊወስን በሚችልበት በዚህ ጉባዔ የሚያስፈልገውን ውሳኔ ለመቀየር እንደማይችል ቢያውቅም ፕሪንሲፕል ላይ የተመሰረተ አቋሙን ከማብራራት አልተቆጠበም::

ከመጀመሪያ አንዱ ነገር ግልጽ መሆን አለበት::ስለሃገር ቤት የተማሪ ንቅናቄ በናና በኢዜና መሃል ውይይት በተካፈተ ቁጥር ወላዋዮች ዘለው ዋብ የሚሉበት የ'መንደርደሪያ' አቋም አላቸው:: ነገሩ ለነሱ በጣም ቀላል ነው:: የቴያትር መድረክ ላይ የወጡ ይመስላቸዋል መሰል ቶሎ ብለው ሮል/ሚና/ ያከፋፍላሉ:: እነሱ ተሽቀዳደመው የሃገር ቤትን ንቅናቄ'ስም ጠባቂ' 'ሮል'ይወስዳሉ:: ለኛ የሃገር ቤትን ንቅናቄ ተኪዓቢ ሮል ይሰጡናል:: እኛ እንደታዘብነው ግን ክፍፍሉ እንዲህ አይደለም::በአንዱ በኩል ለዘላቂው ትግል ፈጽሞ ጓንታ የሌለው፤ከጉድለቶች እየተማረ ለመራመድ የማይቀኮር፤የሃገር ቤትን ንቅናቄ <u>በመናቅና</u> '<u>አረጋዊ</u>'/ፓተርናሊስት/ አቋም በመውሰድ'ደገደጉን' ብቻ እያነሳ ጉድለቶችን በወጉ የማይጠቁም አድሃሪ አቋም አለ:: በሌላው በኩል ደግሞ በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ <u>ሁላችንም ከሚታዩብን ጉድለቶች</u> ትምህርት እየቀሰመ፤ አገር ካሉትም ጓዶች ጋር አረጋዊ ሳይሆን ጓዳዊና ረቮሉሽናዊ በሆነ መንፈስ እየተራረመ ወደፊት ለመግፋት የሚ

የሚኖር አብዮታዊ ተራማጅ ስም ያለው ስለ፡፡በዚህ በኩል የነጓዴት አበበችን ዋና የመከራከሪያ'ለምና በርሊን ጉባዔ ላይ ሰምተነው በቀቶል፡፡ 'እውጭ አገር ሆናችሁ ስለሀገር ቤት ንቅናቄ ለማውራት መብት የላችሁም' የሚል ፈሊጥ ነው፡፡እነጻውሎስ ናኛም እውጭ አገር ሆናችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ እናስባለን ብትሉ አይገባንም' ይሉናል፡፡ገን ውጭ አገር ሆነን ለመታገል የማንንም ፈቃድ አልጠየቅንም፡፡ከማንም የሚሰጥ ግምት ደግሞ ተስፋ አያስቀጠንም፡፡

እሁንም ስለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፣ ስለጉድለቶቻችንና ስለድክመቶቻችን እናፍረጥርጠን በቁም ነገር የመወያየት መብት ለማግኘት ከፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ፈቃድ የምንጠይቅበት ምክንያት የለም፡፡ ተፈራርተን ጉድለቶችን የሚጠቁም 'ጉበዝ' ጠፍቶ ንቅናቄያችን ውስጥ ውስጡን ተበርብር ቢዳከም የሚያገዘው አድሃሪያችን ብቻ ነው፡፡ስለዚህ 'አንተራረም' እያሉ የሚደነፉት ግለሰቦችም በንቅናቄያችን ውስጥ መታረም ካለባቸው አንከርዳዶች ውስጥ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ የነዚህን ግለሰቦች ስም መቀጋት እራሱ በንቅናቄያችን ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች ለማረም ከሚደረገው ሙከራ አንዱ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ለዚያውስ <u>ዛሬ</u> እናንተው በዚህ ትከሱናላችሁ እንጂ ስለአገር ቤት ንቅናቄ አንጓንዴ 'ቤታያችሁ'ራባችሁ ከምትሉት የተለየ ምንም ብለን አናቅም፡፡'በመሰደብ' በኩልም ከመጣችሁብን የናንተን 'ትንተና' ያህል ረቀ የሄደ የለም፡፡/ የፌዴሬሽኑ ገና ጉባዔ ያለጉባዔ'ቋሚ' ተበሎ በፌዴሬሽኑ ባለስልጣኖች ባሰራውት ጽሁፍ ውስጥ ስላገር ቤት ንቅናቄ ከወራነው ውጭ ለበኋላ ከርከራቸው አንጓሎች ወምረው 'ቀባብተው' ፈጥረው የጻፉትን ማህበራችን አይቀበለውም፡፡/

ጓድ አበባ በዚሁ ጉባዔ ላይ በትክክል እጸደገለጠው የአገር ቤት ንቅናቄ ራሱን የህዝቡ ትግል ፊታውራሪ አድርጎ የሚቀጥርበት ጊዜ ነበር፤ ይህ አደገኛ አዝማሚያ ዛሬ ተጠናክሎ ብሎ በትክክል አስቀምጦት ነበር፡፡ እናም ያልነው ይህንኑ ነው፡፡ገራቀደምነት ማለትም ይኸው ነው፡፡ በመላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ/ስለዚህ ባዐር ቤቱ ንቅናቄ ውስጥ/ ከታህሳሱ አልጋት በፊትና በተለይም ከዚያ በኋላ የገራቀደምትነትና የፍከዚዝም /በተለይ በሌዘና ውስጥ/ አዝማሚያ ተስፋፍቶ ነበር፡ብለናል፡፡ በአውሮፓ ማህበር ውስጥም እንዲህ ዓይነት ጉድለት ነበረብን ብለናል፡፡ ከዚህ ሌላ ያልነው የለም፡፡

ነገር ግን ከዚህ ውጭ ተንደርድራችሁ <u>በተለይም የሌዘና መሪዎች</u> ፈጥራችሁ እኛን 'ሆተማሪዎች አልጋት የመጣው በተማሪው ገራቀደምነት ነው አላችሁ' በትሉን ለናንተው አፈርን፤ በዚህ ከመጣችሁም 'እንከራከር፡፡'

የዚያን ጊዜ እናንተ ምን ትሉ ነበር፡፡ እኛስ ምን እንል ነበር፡፡ ያን ጊዜ ነውስ



ሌተራችሁ "It is precisely because of its essentially spontaneous and disorderly and infantile nature that the movement remained exposed and defenceless during the three months propaganda just before the decembre massacre." ያላችሁት እናንተው ነበራችሁ፡፡

በናንተ ግምት እንግዲህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለታህሳሱ አልጋት ያበቃቸው 'ልጅነት'ስላጠቃው፣ በስነስርዐት ስላልተደራጀና ስፖንቴንየስ መልክ ስለነበረው ነው፡፡ በናንተ ግምት ንቅናቄያችን 'ልጅነት'ባያጠቃው አልጋቱ አይደርስም ነበር፡፡ እና ደግሞ የዚያን ጊዜ ለካ የናንተን <u>ተቃራኒ</u> አቋም ይዘን እንከራከር ነበር፡፡ ይህንን ዝቀ ብለን እናያለን፡፡ በመጀመሪያ ግን የናንተን ቴዎሪ ስህተትና የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ ተመልከቶ መተንተን እንዓለ ተባካላችሁእናስባይ፡፡

ይህ የኢት. ተማ. ንቅናቄ ለአልጋት የበቃው በልጅነቱ ነው፣ በስነስርዐት ባለመደራጀቱ ነው የምትሉት ራሱ 'ቴዎሪው'ስህተት ነው፡፡ በየትም አገር፣ መቼም ጊዜ የአንድ ንቅናቄ 'ልጅነት[3]' አድሃሪያችን አሸብር አያውቅም፡፡ጠቅላላውን ገራ ቀደምነቱን፣ ቸኩልነትና ልጅነት አንድን መንግስት እስደገጠው እንደታህሳሱ ዓይነት ፋሽስታዊ ድርጊት በአደባባይ እስከመውሰድ አያደርሱትም፡፡ <u>የዚያን ጊዜ</u> ማህበራችን ባወጣው መግለጫ ያለው ይህንኑ ነበር፡፡'ታህሳስ 20ን ታሪካዊ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ፋሽስታዊው መንግስት በዜቸ ቀን ፋሺስታዊ መልኩ እንዲጋለጥ መገደዱ ነው' ካለ በኋላ ከዚያው አከታትሎ ይህንን አጋላጭ እርምጃ እንዲወስድ <u>የተገደደው</u> እናንተ እንዳላችሁት የተማሪ ንቅናቄ 'ልጅነት'ስላጠቃው ሳይሆን እንዲያውም '... የተማሪ ንቅናቄና የህዝቡ ቅጣ ተባብሮ በዝባዦችን የሚያርበተብተበት ደረጃ በመድረሱ መሆኑን ታሪክ ይመዘገበዋል' ይላል፡፡ እያን ጓዶች የናንተ 'ቴዎሪ' የሬቮሉሽንን ሳይገስ 'ሀሁ' ያልቀመረ ነው፡፡ የታህሳሱ አልጋት የመጣው ንቅናቄያችን በድርጅት፣በፖለቲካና በአይዲዮሎጂ'ከልጅነት' ወደበሰለት ደረጃ በመተሻሻፉ ነው፡፡ ይህ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ያኔም ያልነው ነው፡፡

እናንተ'ልጅነት ያጠቃው ስለነበር...'ስትሉን እና የዚያን ጊዜ ንቅናቄያችን ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱታህሳስ 20 ቀን በብዙ አመታት ጥረት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው የኢት. ተማ. ንቅናቄ ለተጨቆነው ህዝብ ያለውን የነጻነት ጉጉትና ዓላማ በብዙ ወጣቶች ንጹህ ደም በኢትዮጵያ አፈር ላይ የጻፈበት ቀን ነው' ብለናችሁ ነበር፡፡

'በስነስርዐት ስላልተደራጀ፣ ስፖንቴንየስ መልክ ስለነበረው...'ስትሉን እና ታግለው የኢት.ተማ. ንቅናቄ ድርጅታዊ ችግሮችን ህዝቡም የሚነቃበትንና የሚደራጅበትን ዘዴ አተኩሮ ማሰላሰል ጀምሮ እንደነበር ስንገልጽ በዚሁ ያን ጊዜ ባወጣነው መግለጫ '... የህዝቡ የቀየ ትግል የሚደራጅበትንና የሚፋፋምበትን ዘዴ በተግባር እያሳየን

ማበሰር ጀምረናል'ብለን ነበር:: ስርዐቱን ያስደነገጠው'ልጅነታችን' ሳይሆን ይኸው እድገታችን መሆኑን ስንገልጽ በዚሁ መግለጫችን 'ከንጉሡ የተማሪያች ንቅናቄ ሌላው በከተ ስርዐት አደገኛነቱ ታውቋል፣... የ ተማሪው እንቅስቃሴ ፈጽሞ መደምሰስ አለበት የሚለው ከንቱ ቅዠት በአብሪተኞች በዘበዦች መንፈስ ተቀርጿል' ብለን ነበር::

ከናንተ ተለካሽ 'ቴያሪ' አለፈን የዞያን ጊዜ የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ በንመለከት የምናየው ይህንኑ ነው:: በዚያን ዓመት የአገር ቤት ንቅናቄ የሥራ አቀድ ሬቮሉሽናዊ ፕሮፖጋንዳ በህዝቡ ዘንድ ለማስፋፋት ስለነበር የተቀናበረ የመቀሃድ ዘመቻ ለማድረግ ሲዘጋጅ እንደነበር እናውቃለን:: ይህም ሊሆን የቻለው በቀላሉ ሳይሆን እነ ጋዱ ጥላሁን ገዛው በደረጉት የከረረ ትግል ቸኩሎችና ገራ ቀደሞች/በንቅናቄው ውስጥ የነበሩ/ በመቀከማቸውና በታቸውን ለረጉ ሬቮሉሽናውያን ቀደም ብለው እንዲሉቀ በመገደቸው ነው::መንገስተንም ይህንን ፋሽስታዊ እርምጃ ለመውሰድ ያበቃው ይህ የተማሪው ንቅናቄ መብሰልና መሰመር መያዝ አስደንገጠት ነው እንጂ እናንተ እንዳላችሁት 'ልጅነት' አደፋፍርቶወይም ደገፉ የጥቂት ገራ ቀደሞች ውር ውር ማለት አሸብሮት አይደለም::ሊሆንም አይችልም:: በዚህ በኩል ሺህ ጊዜ እንደፈለጋችሁት አጣማችሁ አቅርቡት የኛ ትክክለኛ አቋምና ትክክለኛ ትንተና የዚያን ጊዜም ይኸ ነበር:: አሁንም ይኸው ነው::ሺህ ጊዜ ቀባብታችሁ አቅርቡት የናንተ የከሰረ ትንተና እንጂ የዚያን ጊዜ ይህ ነበር::

ሽረ ለመሆኑ በሃገር ቤት ንቅናቄ በዚህች ጉባዔያችሁ ላይ እንኳ ከእኛ መግለጫ መልዕከቱ አንስቶ እስከ መደምደሚያ መግለጫው ድረስ ሙሉ እምነት ያሳየ ማነው እኛ ነን:: ደግመን ደጋግመን የሃገር ቤት ንቅናቄ ጽኑ የሆነ ሬቮሉሽናዊ ንቅናቄ ነው ውጭ ያለው ውስጥ ባለው ንቅናቄ መመራት አለብን:: የውጭ አገሩ ንቅናቄ የሃገር ቤት ንቅናቄ ተቀጥላ ሊሆን ይገባዋል ብለን ተከራከርን:: አሁንም ንቅናቄውን 'ልጁ' አድርጋችሁ ተቀጥራላችሁና 'ልጅ እንዴት ይመራል' ብላችሁ ነው መሰለ ይህንን ሃሳባችንን ለማሰናከል ያልቆከራችሁት የለም:: ከመጀመሪያውም የአመራሩ ጉዳይ እንዳይነሳ የኛን አጀንዳ/ስለአመራር ጉዳይ የሚል ነጥብ ነበረበትና/ ጣላችሁት:: ገን ጉዳዩን ማፈን ስላልተቻለ ቀረበ::

የሚያሳፍረውና የሚያሳዝነው ይህን ሃሳብ በማደናቀፍ ብቻ አለ ተወሰናችሁም:: 'እንደልጅ' ለቃችንን ተነሳችሁ:: 'ይኸው አመራሩን አስገባንላችሁ' ብላችሁ ከአገር ቤት አንድ ኘሬዚዳንት ሾማችሁ:: ጠቅላላ አመራሩ ግን አንድ ምከተል ኘሬዚዳንት በሚባል ሰው እየተመራ ውጭ እንዲቀይ አደረጋችሁ:: በዚህ መልክ ተጋዳዮንና በስንት መስዋዕትነት እዚህ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰውን ንቅናቄ' የኮንስቲትዩሽናል ሞናርክ' ማዕረግ



በመስጠት ተሳለቃችሁበት::ሰውን ሁሉ እንደልጅ እንደሚል ቀጥራችሁ በዚህ ለታታለሉን ተነሳችሁ::ገን በዚህ ማጭበርበሪያችሁ እንዳልተወናበድንና መላው አመራር በአገር ቤት ንቅናቄ እንዲወሰድ የምናደርገውን ትግል እንደምንቀጥል እዚያው በሰጠነው መግለጫ ነገረናችኋል::

እስቲ ደግሞ ወደህገማህበሩ መሻሻል እንሂድና ከሁሉ ያከራከረንን የአመራር ጉዳይ እንመልከት::

## 5. የህገ ማህበር ማሻሻልና የአመራር ጉዳይ

በውክልናችን መሰረት በዚህ ጉባዔ ላይ የተገኘነው ዋናው ምክንያት ይዘን በመጣነው ዲሞክራቲክ ህገ ማህበር ላይ በመመስረት ለአባልነት ለመወያየት ነበር:: እንደሚታወሰው 135ኛ ጠ/ጉባዔያችን ፌዴሬሽኑ ውስጥ እንዳንገባ የወሰነው ህገማህበሩ ፀረ ዲሞክራቲክ ነው፣ድርጅታዊ ቀርጾም ዲሞክራሲን ያፋልሳል፣አንድነት ያላላል፣ሥራ ያውካል በሚል እምነት ነበር:: ነገር ገን ማህበራችን 'አልገባም'ብሎ በዚህ አላቆመም:: ለኤትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ይበጃል የምንለውን ህገማህበር ለመንደፍ በአውሮፓ የኤት. ተማ. ማህበር አባላት በያለንበት ዓመት ሙሉ በዚህ ጉዳይ በቂ ነጋር የተካሄደ ውይይት አደረገን:: ያለፈውም ዓመት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይህንን ውይይት ሲያገዝና ሲያበረታታ ቆይቶ በአፕሪል ወር የመላ የአውሮፓ ማህበር ቅ/ማህበራት ወኪሎችን ለስብሰባ ጠራ:: በዚህም ስብሰባ ላይ የየቅርንጫፍ ማህበራቱ ሀሳብ ተጨምቆና ተቀነባብሮ ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲን በተከተለ ስነሥርዐት አንድ የህገማህበር ንድፍ ላይ ስምምነት ተደረሰ::ይህንን ንድፍ ህገማህበር ነው ፌዴሬሽኑ እንዲቀበል ይዘን የመጣነው::

ውይይቱ እንደተከፈተ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በዋና ዋና አንቀጾች ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ እንደማንቀበል በቅድሚያ ስላስታወቅን የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ፀረ ዲሞክራቲክ ህገ ማህበራቸውን በምንም ተንኩል እድሜውን ማራዘም አልቻሉም:: አንዳንዶቹ አንቀጾች እንዲያውም እነሱው ራሳቸው ፀረ ዲሞክራቲክ ናቸው ብለው ስላመኑ አላከራከሩንም:: ስለዚህ ዛሬ የፌዴሬሽኑ ህገማህበር ዲሞክራቲክ ስለሆነ የማህበራችን ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በሰጠው የመደምደሚያ መግለጫ ይህን ህገ ማህበር ለ15ኛው ጉባዔያችን ሲያቀርብ የፌዴሬሽኑ አባል እንድንሆን በመደገፍ እንደሚጠይቅ አስታውቋል::

በዚሁ የመደምደሚያ መግለጫ 'የፌዴሬሽኑን ህገማህበር ከፀረ ዲሞክራቲክ አንቀጾች አንድ ባንድ እየፈለቀቀ ላላቀቀ የማህበራችን አባላት አንድ ታላቅ ድል መሆኑ ተገልጿል::ነገር ግን ይህ ለኤት. ተማ. አንድነት በሚደረገው ትግል ይህ ድል አንድ ምዕራፍ እንጂ የመጨረሻው ድል እንዳልሆነ እናውቃለን:: ህገማህበሩን ዲሞክራሲያዊ

ለማድረግ የተደረገው ትግል ተሳክቷል:: አሁን ደግሞ በዚህ ፌዴሬሽን ውስጥ መላ የኢት. ተማሪዎች ማህበራት እንዲጠቃለሉ የሚደረገው ትግል መቀጠል አለበት:: በቅርብ ምስራቅና በአፍሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎችን አብዛኛችን የሚወክለው ማህበር የፌዴሬሽኑ አባል እንዲሆን እንታገላለን:: በተጨማሪ የአመራሩ ጉዳይ ገና ብዙ የምንታገልለት ነው:: የኢትዮጵያን ተማሪዎች ከፓሪስ ወይም ከኒውዮርክ፣ከበይሩት ወይም ከአልጀርስ ሆኖ 'መምራት' የሚቻል ነገር አይደለም:: አጠቃላይ የዓለም ዐቀፍ አመራሩ አገር ቤት መግባት አለበት::

ይህንን ሃሳብ ለጉባዔው ስናቀርብ የፌዴሬሽኑ ጓዶች ያሳዩትን የንቀትና የማጥበርበር ተግባር ባጭሩ ከፍ ብለን ጠቅሰናል::እኛ ያቀረብነውን ሀሳብ ለማደናቀፍ፣ አመራሩ እንደምንም __በግለሰቦች__ እጅ ለማቀየት ማገናቸውም ይዘው ያለመጡትን'ማሻሻያ' አቀረቡልን::ፕሬዚዳንቱ አገር ቤት እንዲሆን:: ጽ/ቤቱ ግን'ለመግባት ስለማይችል' ውጭ እንዲቆይ::

ጓድ አማረ: ፕሬዚዳንቱ ከጽ/ ቤቱ መለየት የለበትም ነው የምንለው::

ጓድ በቀለ: የአገር ቤቱ ፕሬዚዳንት ግላዊ ሴክሬታሪያት ሊኖረው ይችላል:: ጽ/ቤቱ ኢትዮጵያ ሊኖር አይችልም::

ጓድ አማረ: ጽ/ቤቱን ውጭ እንዲቀር፣ፕሬዚዳንቱ አገር ቤት እንዲሆን የሚደረገው ምንዓይነት ሎጂክ ነው::እንዴትስ አንድ ሰው የግል ሴክሬታሪያት ይኖረዋል::

ጽ/ ጽ/ቤቱ ከፕሬዚዳንቱ መገንጠሉን እንቃወማለን::

ጓድ በቀለ: ጥያቄውን እናስበብታለን:: ይመዝገብ::

'አስበውበት' ያመጡት ምንም ነገር የለም:: ያው በመጨረሻ'በኮንስቲቱሽናል ቀናርኪ' መልክ ፕሬዚዳንቱ አገር ቤት ጽ/ቤቱ ውጭ እንዲሆን ወሰኑ:: ለነገሩ ግንደኛው ህገማህበር ፕሬዚዳንቱ 'የካውንስሉ ሰብሳቢ፣ የካውንስሉ ሊቀመንበርና የጽ/ቤቱ መሪ፣የማህበሩ አፈ ጉባዔ ነው' ይላል:: ታዲያ ፕሬዚዳንቱና ጽ/ቤቱ እንደዚህ አራንባና ቆቦ ሆነው ሥራውስ ሊሰራ ይቻላል:: ዘዴው ተገኝቷል:: በቀደሞው ህገ ማህበር ያልነበረ አዲስ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሉት ሰው መጣ:: 'ፕሬዚዳንቱ ሃላፊነቱን ለማካሄድ በማይችልበትጊዜ ምክትል ፕሬዚዳንቱ የፕሬዚዳንቱን ሃላፊነት በመውሰድ ይሰራል' የሚል አንቀጽ ተጨመረ::

ማህበራችን በዚህ ለይስሙላ በተወሰደ እርምጃ እንደማይስማማና ትግሉን በዚሁ አቅጣጫ እንደሚቀጥል አስታወቀ::

ህገማህበሩ ጸድቆ እንዳለቀ በዜያ የነበር ነው የማህበራችን ደጋፊዎች አባሎቻችን ባስገኙት ዲሞክራቲክ ድል ብድግ ብለን ደስታችንን በጭብጨባ ገለጽን::



በማግስቱ የመጨረሻ መግለጫ አነበበ:: በዚህም መግለጫ በዓመቱ ውስጥ የምናደርጋቸው ትብብሮች የተያኑ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን አነሳን::በዚህም ተመርኩዘን እንድንወያይ ጠየቅን::

የፌዴሬሽኑ ጓዶች በዚህም ውይይት አልፈለጉም::ጓድ በቀለ በዓመቱ ውስጥ ይህን ይህን እንድትሰሩ በማለት አንዳንድ ነጥቦች በትዕዛዝ መልክ አቀረበ:: የኛ መልዕክተኞች የቀረቡትን ነጥቦች በመሰረቱ ባይቃወሟቸውም የትብብር ነገር ነውና እኛም ስላቀረብናቸው የትብብር ነጥቦች እንወያይ የሚል ሃሳብ አቀረቡ::

ነገር ግን አሁንም የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ስለመጪው ትብብራችን እንኳ መወያየት አልፈለጉም:: ደጋግሞ በማደላቱ ቅሬታችንን ደጋግመን የገለጽንለት ሊቀመንበራቸው ትደርብ 'አውሮፓ እንደሚሊንሽን ነው የቀረበው:: በእኩል ደረጃ አናናግራችሁም' በማለት ቦታችሁን ረሳችሁ የሚል ወቀሳ ሰነዘረብን::ጓድ ገዛኸኝም ይህን አልፈን ወደሌላ ጉዳይ እንሂድ የሚል ሀሳብ አቀረበ:: ጓድ አማረም የተብበሩን ጉዳይ በደንብ አልተነጋገርንበትም በስራ ላይ መዋሉ ያጠራጥራል በማለት ተቃውሞውን አሰማ::

ውይይቱ እዚህ ፀረ አንድነት ጉባዔ ላይ ካልተቻለ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነትና ትብብር የምንፈልገውን ውይይት በሰፊው ተማሪ መሃል እንቀጥላለን በማለት ብዙም አልተጨነቅንበት:: በዚህም በኩል ትግሉ ይቀጥላል ብለን ከጉባዔው መሳተፋችንን አከተምን:: እነሱም ተመራረጡና'ታሪካዊው' የፌዴሬሽኑ ሁለተኛ ጉባዔ ተፈጸመ::

## 6. __መደምደሚያ__

በዚህ ጉባዔ ማህበራችን የደረሰበትን ስድብና ድንፋታ ቁጥር የሌለው ወገዛ ሁሉ ችሎ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው ለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት በቅን መንፈስ ታገሏል::

የፌዴሬሽኑ ባለሥልጣኖች ሺህ ጊዜ ቢጯጯሁት ፀረ ዲሞክራቲክ ህገ ማህበራቸው ማንንም አላታለለም::በዚህም በኩል ይህንን ፀረ ዲሞክራቲክ ለአንድነታችን የማይበጅ፣ትግላችንን አዋኪ የሆነውን ህገ ማህበራቸውን ለማገባር ቀደምነት የተዋጋው ማህበራችን ነበር:: በዚህ ትግል በማህበራችን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ሰዎች ውዝግብን፣አለመግባባትን፣ በመንዛት ንቅናቄያችንን ለማዳከም ሞክረው ነበር::አናርኪ ለመንዛት፣ ማህበራችንን ለመስነጣጠቅ ሞክረው ነበር:: ለዲሞክራሲና ለአንድነት በቆራጥነት የታገሉ ወንዶቻችንና እህቶቻችንን እየነጣጠሉ በማጥቃት ሊከፋፍሉን ሞክረው ነበር:: ንቅናቄያችን አልተዳከመላቸውም::ማህበራችን አልተከፋፈለላቸውም:: እንዲያውም በዚህ ትግል ፀረ ዲሞክራቲክና ከፋፋይ በግልጽ እየተጋለጠ በአውሮፓ የኢት. ተማ. ማህበርም ከመቸውም ይበልጥ ተጠናክሮ ወጣ::

በመጨረሻ መግለጫችን እንደተገለፀው የፌዴሬሽኑን ህገ ማህበር ዴሞክራቲክ ለማድረግ በተደረገው ትግል የተገኘው የጋራ ድል ሌላ የጋራ ትግል እንደሚቀረን አያስረሳንም:: ይህም ለአንድነታችን የምናደርገው ትግል መቀጠል እንዳለበት ነው::

አሁን ደግሞ እንደዚሁ ለአንድነትና በቆራጥነት በዚህ ዴሞክራቲክ ባደረገነው ህገ ማህበር ዙርያ መሲ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነታቸውን እንዲመሰርቱ መታገል አለብን <u>ይህን ፌዴሬሽን በመምራት ላይ ካሉት ባለስልጣኖች ጋር ስላል ተስማሙ ብቻ ፌዴሬሽኑ አለ ስገባም</u> ያላቸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት አሉ:: ዴሞክራሲን በተከተለ ስነስርዐት እነዚህ ማህበራት አባል እንዲሆኑ ፌዴሬሽኑ እስካሁን እንደነበረው በስም ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የሚገኙትን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት በሞላ እንዲያቀፍ ለማድረግ መታገል ሃላፊነት አለብን::

የሌዘናው ወሪ ጓዱ በቀለ/አሁን የፌዴሬሽኑ 'ምክትል' ፕሬዚዳንት/ በዚህ በኩል ያለውን ፍልስፍና ሲያብራራልን 'ሁሉም የሚያቅፍ የሚሉት ነገር የለም' ብሎ ጮሆበን መዝግበንለታል:: ግን ምንም አይደል:: ድርውንስ ዴሞክራሲን የተ ታውቃታላችሁ ለዴሞክራሲ በተደረገው ትግል ይኸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች አሸነፉችሁ:: አሁን ደግሞ በመላው ዓለም የተሰራጩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ወደአንድነታቸውና ወደትብብራቸው በሚያደርጉት ግስጋሴ ታሪክም ያገዛቸዋልና ለትደግሟቸው አትችሉም:: በዚህም ትሸነፋላችሁ::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ለዘላለም ይኑር!

ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ!!

ህዝባዊ ዴሞክራቲክ ሪፖብሊክ ይኑር!!

ከሠይፉ አድነው



<u>በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ዲሊጌሽን ለሁለተኛው የዓለም ዐቀፍ ፌዴሬሽን ጉባዔ የተሰጠ የመደምደሚያ መግለጫ</u>

ማህበራችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ለኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል አንድነት ያደረገውን ማንም ያውቀዋል:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን በተቋቋመ ጊዜ ምንም እንኳ በአንድነት ስም ቢቀርብም ፀረ-ዴሞክራሲያዊና አጉል ማዕከላዊ ቅርጹ አንድነታችንን ያፈርሳል፣ ትግላችንን ያውካል በማለት በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባላት አልተቀበሉትም ነበር:: ይህንኑም አቋማቸውን በ13ኛው ጠቅላላ ጉባዔያቸው ገልጸዋል::

ነገር ግን አባሎቻችን የፌዴሬሽኑን ፀረ-ዴሞክራቲክ ሕገማህበር በመጣል ብቻ አልተወሰኑም::ለኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ያለባቸውን ሃላፊነትና ለነጻነት ትግል የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ጠንቅቀው በመረዳት አንድ ዓመት ሙሉ በትዕግሥት በትጋትና በቅን መንፈስ ተወያይተው የሰጡንን ሕገማህበር ይዘን ቀረብን::ይሁንና ወደሕገ ማህበር አርማት ከመምጣታችን በፊት በፖለቲካ መስመር ልዩነቶቻችን ላይ ውይይት ለማድረግ በማሰብ ከሰብቴምበር 1 እስከ 5 ለመከራከር ሞከርን:: ነገር ግን ከማውገዝ ውርጅብኝ ከስድብ ጋጋታና ከተፈጠረው የማያሰራ ሁኔታ የተነሳ የፈለግነው በጥሞና ላይ የተመሰረተ ውይይት ለማድረግ አልቻልንም:: በዚሁ ምክንያት ከዚያን ቀን ጀምሮ እስከ ሕገ ማህበር ጥናት ድረስ በተመልካችነት ብቻ እንድንቆም ተገደድን::

የሆነ ሆኖ በተሰጠን ውክልና መሰረት ተወያይተን እነሆ ሁለቱም ወገኖች በአንድ ሕገ ማህበር ላይ ተስማምተናል:: በትዕግሥትና በታላቅ ትጋት አንቀጽ በአንቀጽ እየፈለቀቁ የፌዴሬሽኑን ሕገ ማህበር ከፀረ-ዴሞክራቲክ ይዘቶቹ ሳላቀቁት በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባላት ይህ አንድ ታላቅ ድል ነው:: መላው የኢትዮጵያ ተራማጆች ሊኮሩበት ይገባል::

ይዘን የመጣነውን ማሻሻያዎች የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባዔ ተቀብሎአቸዋል:: ስለዚህም የአውሮፓ ተማሪዎች ማህበር ዲሊጌሽን በተሰጠው ውክልና መሰረት የውይይቱን ውጤት ለ15ኛ ጉባዔ ያቀርባል:: ይህንንም ለጠቅላላው ጉባዔ በሚያቀርብበት ጊዜ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የፌዴሬሽኑ አባል እንዲሆን ድጋፍ ይጠይቃል::

ለዚህም በዓመት ውስጥ የምናደርጋቸው ትብብሮች በቅን መንፈስ እንዲካሄዱ በአቋም መግለጫ መልዕክታችን ላይ ያነሳናቸውን ነጥቦች አንደገና እንደሚከተለው እንደረዝራለን:: በአቋም መግለጫችን ላይ ካቀረብናቸው ሶስት ድርድሮች ውስጥ በአንዱ ላይ አመራሩ ወደአገር ቤት እንዲገባ ጠይቀናል::ይህ ጥያቄያችን ሙሉ በሙሉ አልተፈጸመም:: አሁን በፀደቀው ሕገ ማህበር መሰረት ለይስሙላ ፕሬዚዳንቱ ብቻ አገር ቤት ገብቶ ጽህፈት ቤቱ ተገንጥሎ ውጭ የሚቀርበት አሰባች ሁኔታ ተፈጥሮአል:: በዚህ ሁኔታ አለመስማማታችንና አመራሩ ወደአገር ቤት እንዲገባ ያቀረብነው ጥያቄ ስላልተፈጸመ ትግሉን በዚሁ በኩል እንቀጥላለን::

የዓለም ዓቀፍ የሴቶች ጥናት ክበብ የፌዴሬሽኑ አባል መሆንና አለመሆን ጉዳይ በሰሜን አሜሪካ የሴቶች የጥናት ክበብና በአውሮፓ የኢትዮጵያ ሴቶች የጥናት ክበብ መሃል በተፈጠረው አለመግባባት ሁለቱ የዓለም አቀፍ የሴቶች የጥናት ክበብ አባላት ለችግሩ ዴሞክራቲክ መፍትሄ እስኪያገኙለት ድረስ እንዳቸውም በዓለም ዐቀፍ የሴቶች ጥናት ክበብ ስም በፌዴሬሽኑ

አባል ሊሆኑ ስለማይችሉ የአውሮፓ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ እንደአባል አይቆጥራቸውም:: ፌዴሬሽኑ በፀረ—ዲሞክራቲክ ውስኔ ይህን ማህበር አባል ነው ቢል ይህን አቋሙን በጥብቅ እንቃወማለን::የአህጉቻችን ዲሞክራቲክ መብትና ድርጅታዊ ነጻነት እንዳይናጋ ስለምንታገል በዚህ ፀረ—ዲሞክራቲክ ድርጊቱ ለሚፈጠረው አለመግባባት ሁሉ ተጠያቂ የሚሆነው ፌዴሬሽኑ እንደሚሆን በቅድሚያ እናስታውቃለን::

በምርብ ምስራቅና በአፍሪካ ሁለት የአካባቢ ማህበራት መፈጠራቸውንና ይህም ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ድርጅታዊ አንድነት የሚያስከትለውን ጠንቅ እናውቃለን::አስራ አራተኛው ጉባዔያችን ከሁለቱም ወገኖች በቂ ማስረጃ ባለማገኘቱ ማንኛውንም አላወቀም::ስለዚህ እነዚህ ሁለት ማህበራት በአንድነት መንፈስ ተመርተው እንዲዋሀዱ ቀሪ እያቀረበላቸው በዚህ ጉዳይ የሚፈለግበትን ትብብር ከማቅረብ ማህበራችን አይቆጠብም::ይህ ተፈላጊ አንድነት ካልተገኘ ጉዳዩን በሚገባ አጢርተን አብዛኛውን ተማሪዎች የሚወክለውን ወገን አይቶ እንዲያውቅ ለ15ኛ ጉባዔያችን እናቀርባለን::ይህ ሲሆን በፌዴሬሽኑ ጉባዔ ላይ የሁለቱም ወገኖች ወኪሎች ተገኝተው ስለነበርና ስለችግሩ ማብራራት ቢገባቸው የፌዴሬሽኑ ጉባዔ አንዱን ብቻ ተቀብሎ በማዳመጥ የሌላውን ወኪሎች ከኪራቅና ከሱዳን ድረስ የመጡትን ጓዶች ለማዳመጥ ባለመፍቀዱ በዚህ አጉሪ ፀረ— ዲሞክራቲክ ድርጊት የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ላይ ጠንቅ የሚያመጣ እርምጃ መውሰዱን ያስገነዝባል:: ስለዚህም በዚህ አካባቢ ተያይዞ በኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል ለሚፈጠረው ውዝግብ በቅድሚያ ተጠያቂ የሚሆነው ፌዴሬሽኑ ብቻ ነው:: ጉዳዩ ሳይጣራ ፌዴሬሽኑ አንዱን ወገን ብቻ ሳይቶ በአባልነት ቢቀበል ያገባውን ወገን ማህበራችን በምንም ዓይነት እንደ ፌዴሬሽኑ አባል አይቆጥረውም::

በአኢተማ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ